# መልእክተ አትናቴዎስ

በእንተ በዓለ ፋሲካ

LETTERS OF ATHANASIUS

ትርጉም
ዲያቆን ማለደ ዋስይሁን

አዲስ አበባ
2005 ዓ.ም

© ፳፻፰

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

**ALL RIGHTS RESERVED**

Email
malede2008@gmail.com

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# ይዘት

መግቢያ.....I
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አንድ.....1
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሁለት.....12
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሦስት.....20
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አራት.....30
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አምስት.....35
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ስድስት.....42
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሰባት.....54
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ዐሥር.....67
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ዐሥራ አንድ.....80
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ዐሥራ ሦስት.....96
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ዐሥራ አራት.....103
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ዐሥራ ዘጠኝ.....109
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ.....119
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ ሁለት.....122
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ አራት.....122

መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ ሰባት....................122
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ ስምንት..................123
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ ዘጠኝ......................124
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ተቆንጽሎ የተገኘ....................124
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ተቆንጽሎ የተገኘ....................125
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ከቁጥር ሠላሳ
ዘጠኝ ተቆንጽሎ የተገኘ..........................................................127
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አርባ ..........................130
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አርባ ሁለት.................130
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አርባ ሦስት..................131
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አርባ አራት..................133
መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አርባ አምስት..............133

# መግቢያ

በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ወሳኝ ጊዜያት የሚባሉ ወቅቶች ነበሩ። ቤተክርስቲያን በአገልግሎት ስኬት ያስመዘገበችበት ወይም ተፈትና እንደ ወርቅ ጠርታ የተገኘችበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። ከእነዚህ ጊዜያት አንዱ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ የነበረበት ዘመን ነው። ይህ ዘመን ቤተክርስቲያን በታሪኳ አደገኛ የሚባለው ታላቅ ፈተና ያጋጠመበት ጊዜ ነው። ይህም የአርዮሳውያንና የመንፈቀ አርዮሳውያን የኑፋቄ ዘር ያፈራበት የተስፋፋበት፣ በቤተክርስቲያንን ላይ ለመሠልጠን እጆቹን የዘረጋበት አደገኛ ጊዜ ነበር። በዚህ የፈተና ዘመናት ደግሞ በእሳት የተፈተኑ መንፈስ ቅዱስ የመረጣቸው ቅዱሳንም ይገለጣሉና በዚህ ፈታኝ ወቅት የእነዚህን መናፍቃን የጥፋት ዘመቻ ለመመከት የዘሩትን ኑፋቄ ለማምከን ተጋድሎ ከፈጸሙና ቤተክርስቲያን በታሪኳ ከማትረሳቸው አባቶች ዋነኛው ቅዱስ አትናቴዎስ ሆኗል።

ቅዱስ አትናቴዎስ በእስክንድርያ በ298 ዓ.ም ተወልዶ በዚያው አድጎ ተምሮ ለክብር የበቃ ነው። በመንበረ ጵጵስናው ከመቀመጡ በፊት በሊቀ ዲቁና መዓርግ የሊቀ ጳጳሱ እለ ጉባኤ ሆኖ በኒቂያ ጉባኤ ጭምር ተሳታፊ ነበር። ከአርዮሳውያን ጋር የተደረገውን መንፈሳዊ ትግል የሚያስቡ ሁሉ ቅዱስ አትናቴዎስ ከኒቂያ ጉባኤ ጀምሮ የነበረውን የተጋድሎ ሕይወት ያስባሉ። ከ328 እስከ 373 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በእስክንድርያ የቤተክርስቲያኒቱ ፓትርያርክ ሆኖ አገልግሏል።

ቅዱስ አትናቴዎስ አገልግሎቱን በብዙ መከራና እንግልት የፈጸመ ሲሆን ካገለገለባቸው ጊዜያት አንድ ሦስተኛ ያህሉን በመከራና በስደት ማሳለፉን ታሪክ ይመሰክራል። ለአምላኩ ክብር ቀናኢ ለቤተክርስቲያኒቱ አንድነት የሚተጋ ታላቅ የቤተክርስቲያን ሊቅ ነበር። በትምህርቱ በሕይወቱ የቤተክርስቲያን ብርሃን ነበር። ቤተክርስቲያንን ተሸክሞ በአምላኩ ረድኤት

አርዮሳውያን ካጎረፉት ጎርፍ ካነፈሱት ነፋስ በረድኤተ እግዚአብሔር ብቻውን ያሻገረ ድንቅ ቅዱስ ነበር ማለት ይቻላል።

ቅዱስ አትናቴዎስ በአገልግሎት ዘመኑ ከሚያከናውናቸው መንፈሳዊ ተግባራት አንዱ የእስክንድርያ መንበር ያደርግ የነበረውን የበዓላት ቡተለ ይም የትንሣኤ በዓል የሚከበርበት ቀን ማወጅ ነበር። ሊዚህም ዓላማ ከበዓሉ አስቀድሞ በመላው ዓለም ላሉ አብያተክተርስቲያናት የበዓሉን ጊዜ ያውጅ ነበር። ይህ ሥርዓት አስቀድሞም የነበረ ሲሆን ቅዱስ አትናቴዎስም አጠናክሮ ይፈጽመው የነበረ አባታዊ ተግባር ነበር። ቅዱስ አትናቴዎስ በሚያስተላልፋቸው በእነዚህ መልእክቶችም የበዓሉን ቀን ከማብሰር ባለፈ ስለበዓሉ አከባበር፣ ስለክርስትና ሕይወት፣ ስለቤተክርስቲያን ወቅታዊ ሁኔታ ስለ መጻሕፍት ምሥጢራት ያብራራል፤ ያስተምራል፤ ይሰብካል። በየዘመኑ በሚል ካቸው በእነዚሁ መልእክቶቹ ቀኖና ቤተክርስቲያን ሠርቶ ለሁሉም አብያተክርስቲያናት ይልክም ነበር። በመከራ፣ በስደት፣ በፈተና የነበሩትንም ያጽናናል። በእርሱ ላይ የሚደርሱ ፈተናዎችንም በመግለጽ እንዲጸልዩለት ለአብያተክተርስቲያናት ያሳስብ ነበር።

መልእክቶቹን የሚልከውም በሰላም ጊዜ ከመንበሩ ተቀምጦ ብቻ ሳይሆን በስደትም እያለ ካለበት ይልካቸው ነበር። ሁሉም ክታቦቹ ባይገኙም ተፈልገው የተገኙት ግን በያዟቸው መልእክቶች በየትኛውም ዘመን ላሉ ክርስቲያኖች የሚያንጹ በመሆናቸው በዓለም አብያተክርስቲያናት ዘንድ እስከዛሬ እየተነበቡ አገልግሎት ይሰጣሉ። ተጠርዘው በብዙ ቋንቋ ተተርጉመው በየአብያተክርስቲያናቱ አገልግሎት ይሰጣሉ።

ይህ መጽሐፍም እነዚህ መልእክቶቹ ተተርጉመው የቀረቡበት ነው። የቅዱስ አትናቴዎስ የበዓላት መልእክቶች ጳጳስ ሾሞ ቤተክህነቷን ላቀናላት ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ምእመናንንም የእነዚህ መልእክቶቹ ጣዕም እንዲደርሷቸው ማድረግ አግባብ ነው። በየደረጃው እየተጠኑ እየተስተካከሉ እየዳበሩ አዳዲስ መረጃዎችም እየተካከቱበት ወደፊት ዳብሮ የበለጠ



እንደሚዘጋጅ ቢታመንም አሁንም በተዘጋጀበት ደረጃ ቢሆን የቃሉን በረከት መቋደስ አግባብ ነው ብዬ አምናለሁ።

እያንዳንዱ መልእክት ከጥቂቶች በቀር በተሟላ ሁኔታ ከጅምር እስከ ፍፃሜ ይዘታቸው ተጠብቆ ያሉ ሲሆን በዚህ የትርጉም ሥራም በእያንዳንዱ መልእክት ከአንድ አንቀጽ በላይ ከማይሸፍነው የበዓል ቀን አዋጁ በስተቀር ለክርስቲያኖች ሕይወት በየትኛውም ጊዜ ያንጻሉ የተባሉ ሁሉም ክፍሎች ተተርጉመዋል። ቅዱስ አትናቴዎስ ጽፏቸው ሳይገኙ ከቀሩት ደብዳቤዎችና አስተዳደራዊ ሆነው በጊዜው ብቻ ጥቅም ከሰጡ መልእክቶቹ፣ የጳጳሳትን ዝርዝር ከያዙና የበዓሉን ቀን ብቻ ከማሳወቅ ባለፈ ሌላ ይዞታ ከሌላቸው ከጥቂት ደብዳቤዎች በቀር ሁሉም ተተርጉመው ቀርበዋል። ደብዳቤዎቹ ከ329 እስከ 373 ዓም ድረስ እንደተጻፉ የሚታመኑ ናቸው። የተገኙት በአጠቃላይ ከ30 የማይበልጡ ሲሆኑ የቀሩት ከተለያዩ ደብዳቤዎቹ የተወሰዱ ቁንጽሎች ናቸው።

በይዘታቸውም አብዛኞቹ በዓልን የማክበር ምስጢር አስፈላጊነት መሠረት ጥቅም ወዘተ የሚተነትኑ የሚያብራሩ የሚያመሰጥሩ ናቸው። ሌሎች ደግሞ በጊዜው በአብያተክርስቲያናት ላይ ከአርዮሳውያንና ከመንፈቀ አርዮሳውያን በኩል ይደርስ የነበረውን መከራ እያነሣ ራሱንና ክርስቲያኖችን የሚያጽናናበት፤ መከራውን አልፈው ለክብር የሚበቁበትን የቃሉን ኃይል የሚያስታጥቅባቸው ነበሩ። ከኃጠአት ከኑፋቄ ስለመጠበቅ መከራን ስለመታገስ በዓል ለተባለ ለመንግሥተ ሰማያት ለመብቃት መኖር ያለበትን ፍጹም የሆነ ይክርስትና ሕይወት ደጋግሞ ስለሚያነሣ በየትኛውም ዘመን በየትኛውም ወቅት ክርስቲያኖች ቢያነቧቸው በሕይወታቸው የሚበረቱበትን የቃሉን በረከት ያገኛሉ።

እኔም ይህንኑ በማመን ቅዱስ አትናቴዎስ በልቡ የነበረ የሃይማኖት ሐሳቡን ለማወቅ ለመረዳት ለማመን ቅዱሱን ለማክበር አርአያነቱን ለመከተል ይጠቅማል በሚል ተርጉሜ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ

ለንባብ ለማብቃት ችዬአለሁ። መልእክቶቹ የቀረቡበት ርእስ የተላኩት ክታቦች ቁጥር ሲሆን ከምንጩም በዚሁ አግባብ የቀረቡ ናቸው ስለዚህ ያልተዠት ደብዳቤዎች ያልተካተቱበት በመሆኑ በቅደም ተከተል የቀረቡት በተገኙት ደብዳቤዎች ቁጥር ነው። በየመልእክቶቹ ውስጥ የተሰጡት ንዑስ ርእሶች ግን የእኔ የተርጓሚው ናቸው እንጂ ከምንጩ የሚገኙ አይደሉም ይህም ለአንባቢ አካሔድ ሊያግዝ ይችላል በሚል እምነት ነው።

በአጠቃላይ የቅዱስ አትናቴዎስን የመልእክቱን ቃል መስማት ማንበብ ለሚወዱ እኔ ሳነባቸው የተሰማኝን ስሜት ሊጋሩ ይችላሉ ብዬ ለማስባቸው ክርስቲያኖች ያግዛል በሚል እምነት መተርጎሜን በዚሁ አጋጣሚ እገልጻለሁ። በየጊዜው በመጻሕፍት ቃል ሕይወታ ቸውን ማበርታት ለሚሹ የቃሉ ጥማት ላለባቸው ትሑታን እነሆ ስል የቅዱስ አትናቴዎስ በረከቱ በሁላችነም ላይ እንደሚያድር ተስፋ በማድረግ ነው።

ተርጓሚው





# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አንድ

## በዓላትን በጊዜያቸው ስለማክበር

ወዳጆቼ ኑ! ጊዜው በዓልን እንድናከብር ይጠራናል። ዳግመኛም የመለኮቱ ብርሃን በእኛ ላይ የሚያንጸባርቅ "የጽድቅ ፀሐይ" በዓሉን የምናከብርበትን ጊዜ ቀድሞ ያውጃል /ሚል 4፥2/። እንግዲህ ጊዜው ሳያልፍብን፣ ደስታም ሳያልፈን በወቅቱ ልናከብረው ይገባናል። አሁን በጊዜው አስበንበት ልናደርጋቸው ከሚገቡን ክርስቲያናዊ ተግባራት ቀዳሚው ነው፤ መልካም ሥራም ነውና።

ቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙሩን ሲመክር ጊዜውን እንዲያስተውል፣ እንዲጠብቅ "በጊዜውም ያለጊዜውም ጽና" ብሎታል /2 ጢሞ 4፥2/። አንዱን ወይም ሌላውን ጊዜ በውል በማወቅ ከጊዜው የሚስማሙ ነገሮችን በማድረግ እንዲሁም ከጊዜው የማይገጥሙ ነገሮችን ባለማድረግ የሚሰነዘርብህን ወቀሳ አስወግድ! ስለዚህ የሁሉ አምላክ እግዚአብሔር በጠቢቡ ሰሎሞን ምክር ነገርን ሁሉ በጊዜና በወቅቱ መፈጸምን አስተምሯል /መክ 3፥7/።

የጊዜውም ቀጠሮ በደረሰ ጊዜ በእግዚአብሔር የታዘዘው የሰው ልጆች ሁሉ ድኅነት ለሁሉም መሆን ይገባዋልና "የእግዚአብሔር ጥበብ" ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ጊዜው ሳይሆን በጊዜው ነፍሳትን ጐበኘ /1ቆሮ 1፥24/። ‹‹በየትውልዱም በጻድቃን ሰውነት ትተላለፋለች፤ የእግዚአብሔርም ወዳጆችና ነቢያቱ ታደር ጋቸዋለች›› /ጥበብ 7፥27/ እጅግ ብዙዎች ጊዜውን በመናፈቅ "ከጽዮን መድኀኒትን ለእስራኤል ማን ይሰጣል?›› እያሉ /መዝ 14፥7/ ለእርሱ

ጸሎትን ያቀርቡ ነበርና። መሽራዬቱም በመኃልየ መኃልየ ሰሎሞን ላይ እንደተጻፈው "አንተ የእናቴን ጡት እንደ ጠባ እንደ ወንድሜ ምነው በሆንህ!›› እያለች/ በናፍቆት ትጸልይ ነበር። /መኃ 8÷2/ በጊዜ ውም ሆነ። ጌታ ሆይ! አንተ የሰው ልጆችን መልክ ያዝህ፤ የሰዎችን መከራ ስለእኛ ብለህ ተሸከምክ።

እንግዲህ የሁሉ አምላክ የጊዜው የወቅቶች ሁሉ አስገኚ ከእኛም ይልቅ ስለ እኛ የሚያውቅ እርሱ መድኀኒት በሆነን ጊዜ እኛም ለተፈወስንበት ለእርሱ ለመድኀኒታችን ብቻ ለመታዘዝም በጽኑ አነሣሣን። እንግዲህ እርሱ ያለጊዜው የመጣ አልነበረም፤ በጊዜው እንጂ፤ እንዲህም አለ "በተወደደ ጊዜ ሰምቼሃለሁ በመድኀኒትም ቀን ረድቼሃለሁ›› /ኢሳ 49÷8/። በዚህ መልእክቱም ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ጊዜ እንድናስብ እንድናስታውስ "በተወደደ ሰዐት ሰማሁህ፤ በመዳንም ቀን ረዳሁህ›› ብሎ ጻፈልን /2ቆሮ 6÷2/። ስለዚህ እርሱ መድኀኒት ሆኖናልና ወደ በዓል ጠራን።

አስቀድሞ እስራኤልም በተገዙለት፣ ባከበሩት ጊዜ ወደ በዓላት ጠራቸው "በዓመት ሦስት ጊዜ በዓል ታደርግልኛለህ›› አላቸው /ዘዳ 23÷14/ ወዳጆቼ ይህ አሁን እኛ የያዝነው ከእነዚያ አንዱን ነው፤ የካህናቱም መለከት ያስተጋባል፤ እንድናከብር ያነሣሣል። መዝሙረ ኛው "በመባቻ ቀን በከፍተኛው በዓላችን ቀን መለከትን ንፉ›› ሲል እንዳዘዘው /መዝ 81÷3/ እንግዲህ ይህ ቃል በሁለቱም በመባቻና በታላቁ በዓል ቀን መለከትን እንዲነፉ ያዛል። የጨረቃ ብርሃን ሙሉ ሆና ፍፁም የምትሆንበትን ቀን ታላቅ የበዓል ቀን አደረገው።

**ስለመለከት ጥሪ**

ትእዛዝም ሁሉ እንደ መለከቶቹ ዓይነት ነው። እንደተባለውም በአንዱ ጊዜ ወደ በዓላቱ ይጠራሉ። በሌላ ጊዜ ወደ ደምና ተጋድሎ





ሕይወት ይጠራሉ። ይህ ሁሉ ያለ ታላቅነት /ክብር/ ሊፈጸም የሚችል አልነበረም። በአጋጣሚም አይሆንም። ነገር ግን እነዚሁ የመለከት ድምፆች ሰው ሁሉ ወደ ታወጀው ይመጣ ዘንድ ሊጠሩ ተሾመዋል። ይህን ልንማረው የሚገባ ነው፤ ከእኔ ብቻ ሳይሆን ከቅዱሳት መጻሕፍት። እግዚአብሔር ለሙሴ "ሁለት የብር መለከቶች አጠፍጥፈህ ለአንተ አድርግ ማኅበሩን ለመጥራት ከሰፈራቸውም ለማስነሣ ይሁኑልህ›› ብሎ እንደተናገረው እርሱን ለሚወዱ ሁሉ የሚገባ ነው። /ዘኁ10÷1-2/

እነዚህ ሁሉ በሙሴ ዘመን የሆነውን የሚገልጹ ቢሆንም ጥላው እስኪያልፍ ድረስ ሊከበሩ ይገባ ነበር። ነገሮቹም ሁሉ "እስከ መታደስ ዘመን ድረስ" የሚያገለግሉ ነበሩ /ዕብ 9÷10/። እንዲህም ተባለ "በሚገፉችሁም ጠላት ላይ በምድራችሁ ወደ ሰልፍ ስትወጡ ከፍ ባለ ድምፅ መለከቶቹን ንፉ›› /ዘኁ 10÷9/ ከዚያም በመለከቶቹ ታውጃላችሁ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ትታሰባላችሁ፤ ከጠላቶቻችሁ ትድናላችሁ። መለከቶቹ በጦርነት ብቻ የሚነፉ አልነበሩም፤ በሕጉ የበዓላትም መለከት ነበር እንጂ። ሙሴም እንዲህ አለ "ደግሞ በደስ ታችሁ ቀን በበዓላታችሁም ዘመን በወርም መባቻ በሚቃጠል መሥዋዕታ ችሁና በደኅንነት መሥዋዕታችሁ ላይ መለከቶችን ንፉ›› /ዘኁ 10÷10/።

ሕግን የሰማ ሰው ሁሉ የመለከትን ክብር ቀላልና የተናቀ ነገር አድርጎ አያስብ። እጅግ ድንቅና አስፈሪ ነገር ነው። ከሌላ ከማንኛውም ድምፅ ወይም መሣሪያ የላቀ የሚቀሰቅስና የሚያስፈራ ነው። ስለዚህ እስራኤል ባዕድ ሳይሆን ልጅ ነውና በዚህ መሣሪያ ትእዛዛትን ሁሉ ይቀበላል። ነገር ግን ትእዛዙ /አዋጁ/ የሰው ብቻ እንደሆነ እንዳይታሰብ፤ ድምፁ በተራራው ፊት እንደተንቀጠቀጡበት /እንደፈሩበት/ ንግግር ድምፅ ይመስላል፤ በዚያም የተሰጣቸውን ሕጉን ያስታውሳሉ፤ ያከብራሉ። /ዘጸ 29÷16/።

ሕጉ የተደነቀ ጥላውም እጅግ በጣም ጥሩ ነውና የሚሰሙትን ወደ ፍርሃት ሳይሆን ወደ ክብር የሚመራ፤ በተለይ በዚያን ጊዜ ኖረው መስማት ብቻ ሳይሆን ባዩትም ዘንድ እነዚህ ነገሮች እንደ ምሳሌና እንደ ጥላ የሚደረጉ ነበሩ። አሁን ግን ወደ ትርጓሜው እንለፍ፤ ምሳሌውን በርቀት እንተወው፤ ወደ አማናዊው እንምጣ፤ ወደ ሚጮኽና በአንድ በኩል ለተጋድሎ ወደ ሚጠራን ወደ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክህነታዊ መለከቶች እንመልከት።

ቅዱስ ጳውሎስ "መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር በሰማያዊውም ሥፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ›› እንዳለ። /ኤፌ 6፥12/ በሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ድንግልና ሕይወት፣ ራስን ወደ መካድ፣ ወደ ንጹሕ ጋብቻ ይጠራል። ለደናግላን የደናግላንን ነገሮች፣ መቆጠብን /መከልከልን/ በሚወዱ ደግሞ የመቆጠብን ነገር፤ ላገቡት የተከበረ ጋብቻን ነገር ያውጃል /1ቆሮ 7፥2፣5/ ለእያንዳንዱም የሚገባውን የትሩፋት ሕይወትና የጽድቅ ሥራ ዋጋ እንደሚሰጠው ያውጃል። አንዳንዴ ጥሪው ለጾም አንዳንዴ ለበዓል ይሆናል።

ይኸው ሐዋርያ መለከትን ይነፋል። እንዲህም እያለ ያውጃል፤ "አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ፤ ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና›› /1ቆሮ 5፥7-8/ ከዚህ የላቀ የመለከት ድምፅ ለመስማት የምትተጉ ከሆነ ጌታችንም እንዲህ ይላል "ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ›› ይላል /ዮሐ 7፥37/ የመለከቱን አዋጅ ለመስማትና ለመ ጽናት ብቻ የተዘጋጀን ከሆነ ጌታችን በቀላሉ ወደ ተርታ በዓል የጠራን አይደለም፤ ለታላቅ በዓል ጠራን እንጂ።





## ጾምን ስለመቀደስ

መለከትን ለሚነፉ ነቢያት የታዘዙ የተለያዩ ዐዋጆች ነበሩ። በተጨማሪም ወደ እውነት እንዲመለሱ፤ መለከትንም ለመንፋት እንዲዘጋጁ በነቢዩ አንደበት እንዲህ በማለት ተናግሯልና "በጽዮን መለከትን ንፉ፤ ጾምንም ቀድሱ" /ኢዮ. ፪፥፲፭/ ይህ የመለከት ማስጠንቀቂያ እና በምንጾምበት ጊዜ ጾምን እንቀድስ ዘንድ የተሰጠ ጥብቅ ትእዛዝ ነው።

ወደ እግዚአብሔር የተጠሩ ሁሉ እርሱን አይቀድሱም፤ እርሱን ባለመታዘዝ የሚያረክሱ አንዳንዶች አሉና። በእርግጥ የሚያረክሱት እርሱን አይደለም፤ የማይቻል ነውና፤ ስለ እርሱ ያላቸውን የራሳቸውን ሐሳብ እንጂ። እርሱ ቅዱስ ነውና በቅዱሳኑ ደስ ይለዋል። /መዝ. 16፥3/ ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር የማይታዘዙትን "ሕግ ተላላፊዎች እግዚአብሔርን ይንቃሉ።" በማለት ይወቅሳል። /ሮሜ. 2፥23/ ስለዚህ እነዚህን ከሚመስሉ ጾምንም ከሚያረክሱ መለየት እንደሚገባ ሲያመለክት "ጾምን ቀድሱ" አለ።

ብዙዎች ለጾም ሲሰበሰቡ በልባቸው ሐሳብ ራሳቸውን ያረክሳሉ፤ እነዚህም በወንድሞቻቸው ላይ ክፋን በማድረግ፤ አንዳንዴም ባልንጀራን በማታለል ለመንጠቅ የሚደፍሩ ናቸው። ሌላውን ነገር ሁሉ ሳንጠቅስ ራሳቸውን ከባልንጀሮቻቸው በላይ የሚያደርጉ ብዙ አሉ። በዚህም ታላቅ ክፋትን ያመጣሉ።

ምንም እንኳን በሳምንት ሁለት ቀናትን ቢጾምም ከቀራጩ አስበልጦ ራሱን በማየቱና በጾሙ በመመካቱ ብቻ ለፈሪሳዊው አልበጀውም። በዚሁ መንገድ የእስራኤል ልጆችም ተወቅሰዋል፤ እንዲህ ባለ የማይበጅ ጾም ውስጥ ያለፉ ነበሩና። በነቢዩ በኢሳይያስ አንደበት "እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን? ሰውስ ነፍሱን የሚያዋርደው

እንደዚህ ባለ ቀን ነውን? በውኑ ራሱን እንደ እንግጫ ዝቅ ያደርግ ዘንድ ማቅንና አመድንም በበታቹ ያነጥፍ ዘንድ ነውን? በውኑ ይህን ጾም በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን?" በማለት ይወቅሳል፤ ያሳስባል፡፡ /ኢሳ. 58፥5/

ስንጾም ምን ዓይነት ሰብእና መላበስ እንዳለብን፣ ጾማችንም በምን መልክ መሆን እንዳለበት አሁንም ደግመን እንናገር፡- "እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ በዚህ በሰባተኛው ወር ዐሥረኛው ቀን የማስተሥረያ ቀን ነው፤ የተቀደሰ ጉባኤ ይሁንላችሁ፤ ሰውነታችሁን አስጨንቁት፤ ለእግዚአብሔርም የእሳት ቁርባንን አቅርቡ" /ዘሌ. 23፥26/ ከዚያም አስከትሎ የዚህን ሕግ ሐሳብ የበለጠ ሲተረጉም እንዲህ አለ፡- "በዚያም ቀን የማይዋረድ ሰው ሁሉ ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ፡፡" /ዘሌ. 23፥39/ ወንድሞቼ ሆይ! ጾም ምን እንደሚያደርግ፤ ስንጾምም በምን መልክ /ሁኔታ/ መጾም እንዳለብን ሕጉ ያዘዘንን እናስተውል፡፡

ነፍስ ክፉውን ሐሳብ ሁሉ ባልተከተለች ጊዜ ትሑት ናት፡፡ ይልቁንም በትሩፋት የምትመላለስና የበቃች ለመሆን ክፉትን ሳይሆን መልካምን ነገር ትመገባለች፡፡ መልካም ሥራና ክፋት የነፍስ ምግቦች ናቸው፡፡ ነፍስ ባላት ነጻ ፈቃድ መሠረት ከሁለቱ አንዱን ሥራ /መልካም ሥራን ወይም ክፋትን/ ትመገባለች፡፡ ወደ መልካም ሥራ ካዘነበለች በበጎ ሥራ ታድጋለች፡፡ በጽድቅ፣ በእርጋታ በየዋሕነት፣ በጽናት ትፋፋለች፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "በእምነትና በተከተልኸው በመልካም ትምህርት ቃል የምትመገብ የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም አገልጋይ ትሆናለህ" /1ጢሞ. 4፥6/ በማለት ተናገረ፡፡ በጌታም ዘንድ ይህ እውነት ነበር፡፡ "የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው፡፡" ብሏል፡፡ /ዮሐ. 4፥34/





ይህ ካልሆነ ግን ነፍስ ወደ ውርደት ታዘነብላለች፤ በኃጢአት እንጂ በሌላ በምንም አታድግምና፡፡ የኃጥአን ምግብ የዲያብሎስን ፈቃድ መፈጸም ነው፡፡ እርሱ የኃጥአን ምግብ ነው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሰማያዊ እንጀራ በመሆኑ የቅዱሳን ምግብ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ነው "ሥጋዬን ካልበላችሁ ደሜንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም" ያለው፡፡ /ዮሐ. 6፥53/ እንዲህ ከሆነ ዲያብሎስ የብርሃን ከሆነው ነገር አንዳች የማያደርጉ፣ በጨለማም ሥራ የጸኑ የክፉዎች ምግብ ነው፡፡ ከዚህም መውጣት ይችሉ ዘንድ፤ ከክፋትም ይመለሱ ዘንድ፤ የነፍስ የሕይወት ምግብ በሆነው መልካም ሥራ እንዲያድጉ ጌታ ያዛል፡፡ እነዚህም ከልብ የሚመነጭ ትሕትና፣ ለራስ ክብርን አለመስጠት እና እግዚአብሔርን ማክበር ናቸው፡፡

እንዲህ ያለው ጾምም ለነፍስ ይቅርታን የሚያስገኝላት ብቻ አይደለም፤ ቅድስት ሆና ትጠበቃለች እንጂ፡፡ ቅዱሳንንም ከምድር ከፍ ከፍ ያደርጋል፤ ከዚያም ለክብር ያዘጋጃል፡፡ በእርግጥም የነገርኳችሁ ነገር ድንቅ ነው፡፡ አምን እጅግ ተአምራዊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ ነው፡፡ ከእውነትም ያልራቀ፤ በቅዱሳት መጻሕፍትም የሚማሩት ነው፡፡

ያ ታላቅ ሰው ሙሴ ጾምን በጾመ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገረ፤ ሕግንም ተቀበለ፡፡ ታላቁና ቅዱሱ ኤልያስም በጾመ ጊዜ ለታላቁ የእግዚአብሔር ራእይ ተገብቶ ነበር፡፡ በመጨረሻም ወደ ሰማይ እንደወጣው እንደ እርሱ ዐረገ፡፡ ዳንኤልም በጾመ ጊዜ ምንም እንኳን ወጣት ቢሆን ለታላላቅ ምስጢራት የታመነ /የተገባ/ ነበር፡፡ እርሱ ብቻውን የንጉሡን ምስጢራት ይረዳ ነበር፡፡ ስለዚህም ለታላላቅ ራእያት የተገባ ሆነ፡፡

የእነዚህ ቅዱሳን ጾም እጅግ የረዘመ፣ ቀኖቹም የበዙ በመሆናቸው

ምክንያት ማንም በጥርጥር አይውደቅ! ይልቁንም እግዚአብሔርን ማሰብ፣ ከእርሱ የሆነው ቃሉም የሚፈሩትንና በእምነት የጸኑትን ለማኖር በምግብ ሁሉ ፋንታ ብቁ ነው።

ካልሆነማ በሰማይ ያሉ መላእክት የአብንና የመድኃኒታችንን ፊት ዘወትር ባያዩ ባልጸኑ ነበር። ሙሴ ከእግዚአብሔር እየተነጋገረ ባለበት ጊዜ ሁሉ በእውነት በሥጋው በነፍሱ ጾመ፤ በመለኮት ቃል ይኖር ነበርና። ወደ ሰዎች በወረደ ጊዜ ግን እግዚአብሔርም ከእርሱ በተሰወረ ጊዜ እንደሌሎች ተራበ። በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ከተነጋገረባቸው ከአርባ ቀናት በላይ /ከተራራው እንደወረደ/ ጾመ አይባልም። በአጠቃላይ ቅዱሳን እያንዳንዳቸው ለዚህ ከፍተኛ ምግብና /ኑሮ/ የተገቡ ነበሩ።

## አማናዊውን በዓል ስለማክበር

ወዳጆቼ እንግዲህ ነፍሳችን በመለኮት ማዕድ /ምግብ/ በቃሉ፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውጫዊ ሰውነታችንም በጾም ከኀለመሰች ይህንን የሚያድን ታላቅ በዓል እናክብር። የማያውቁ አይሁድ እንኳ የፋሲካን በግ በበሉ ጊዜ ይህን አምላካዊ ማዕድ በጥላው /በምሳሌው/ ተቀበሉት። ነገር ግን ምሳሌውን /ጥላውን/ አላወቁትምና በዚህም ዘመን እንኳ የፋሲካን በግ ይበላሉ። እነርሱ ግን ስተዋል፤ ያለከተማዪቱና ያለ እውነቱ /አካሉ/ እየኖሩ ናቸውና። የይሁዳ ግዛትና ከተማዪቱ እስካሉ ድረስ ምሳሌው የፋሲካ በግ ጥላ ሆኖ ነበር። እንግዲህ ሕጉ እነዚህ ነገሮች በሌላ ከተማ እንዳይፈጸሙ አዟልና። /ዘዳ 12፥1፣13፣14/

ከዚህ በተጨማሪ ሕጉ ሁሉንም የተቃጠለ መሥዋዕትና ቁርባን ከኢየሩሳሌም ውጪ በሌላ መሠዊያ ቦታ እንዳያቀርቡ አዟል። በዚህ ገለጻ መሠረትም መሠዊያውና ቤተመቅደሱ የታነጸው በዚያች ከተማ ብቻ ነውና፤ በሌላ ከተማ እነዚህን የአምልኮ ሥርዓቶች እንዲፈጽሙ





አልተፈቀደላቸውም፤ ያቺ ከተማ ባለፈች /በጠፋች/ ጊዜ እነዚያ ምሳሌያዊ ነገሮች ይወገዱ ዘንድ።

አሁን ግን አማናዊውን በዓል እናክብር፤ እንግዲህ ጌታችን ተገልጧልና፤ ከተማዪቱ ፍጻሜዋ ሆኗል። እንግዲህ ሌላ ምስክር የምንሻ ከሆነ ዓይኖቻችን ያዩትን ማስረጃ እናድርግ፤ የአይሁድም ምድር /ዓለም/ አሁን ጠፍቷል። ይህም ለጥላው ማለፍ ፍፁም ማረጋገጫ ነው።

እነዚህን ነገሮች ከእኔ ብቻ የተማራችኋቸው አይደሉም፤ አስቀድሞም የቅዱሳን ነቢያት ድምፅ እንዲህ ሲል ይጮኻል። ‹‹እነሆ የምሥራችን የሚያመጣ ሰላምንም የሚያወራ ሰው እግር በተራሮች ላይ ነው›› /ናሆ 1፥15/ ይህ ነቢይ ያስተላለፈው ምን ዓይነት መልእክት ነው፤ እንዲህ ሊለን ሲንደረደር ነው "ይሁዳ ሆይ አጥፊው ፈጽሞ ጠፍቷልና ከእንግዲህም ወዲህ በአንተ ዘንድ አያልፍምና ዓመት በዓሎችህን አድርግ፤ ስእለቶችህን ክፈል›› /ናሆ 1፥15፤ናሆ 2፥1/ አንድ ሰው አይሁድን የምትመኩበት ጥላ ያልፋል ሊላቸው ይቻለዋል። "አጥፊው ፈጽሞ ጠፍቷልና፤ ከእንግዲህም ወዲህ በአንተ ዘንድ አያልፍምና›› የሚለው ቃል ገለጻም ያለጥቅም የተጻፈ አይደለምና። ነገር ግን እስካላለፈ ድረስ ጠፍቷልና።

እንግዲህ አይሁዶች ሆይ! እንግዲህ ይህ ያሳለፈው ማነው? ሙሴ ቢሆን /ማረጋገጫው/ ምስክርነቱ ሐሰት በሆነ። ብቸኛ የተለየ መሠዊያ ሆኖ እነዚያን ሥርዓቶች እንዲፈጸሙ ወደ ታዘዙበት ቦታ አሁን ሰዎቹ /አይሁድ/ እየመጡ አይደለምና። [ኢየሩሳሌም ጠፍታለችና አይሁድም ተበትነዋልና]። ሳሙኤል ቢሆን ወይም ሌላ ከነቢያት አንዱም ቢሆን እውነቱ በተገደፈ፣ በተዛባ ነበር። ያኔ እነዚህ ነገሮች በይሁዳ ምድር ይደረጉ ነበርና፤ ከተማይቱም ጸንታ ነበርና። ያ ጸንቶ ቢሆን ኖሮ እነዚህ ነገሮችን በዚያ መከወን አስፈላጊ ነበርና።

ወዳጆቼ ሆይ! እነዚህ ምንም እንዲሆኑ ማን አደረጋቸው:: እውነት ለመለየት የምትፈቅዱ፣ ከአይሁድም ተረት የምትጠበቁ ከሆነ፤ እነሆ ያሳለፈው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በደቀ መዛሙርቱ ፊት ላይ እፍ ያለው እርሱ "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ›› አላቸው:: /ዮሐ 20÷22/ እነዚህ ነገሮች በሆኑ ጊዜ ሁሉም ነገር አልፏል:: መሠዊያው ተሰብሯልና፤ የቤተመቅደሱ መጋረጃ ተቀዷል፤ ከተማይቱ ጠፍታለች፤ ባትጠፋም እንኳ ርኩሰት ግን በተቀደሰው ሥፍራ መካከል ሆኗል፤ ከዚያም ከተማዪቱና እነዚያ ጥንታውያን መሠዊያዎች የመጨረሻ ጥፋታቸውን ሊቀበሉ ተዘጋጅተዋል::

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከጥላዎቹ ዘመን አልፈን ተሻግረናል:: በእነርሱም ሥር የሃይማኖት ሥርዓቶች አይከወኑም:: ወደ ጌታም ተመልሰናል:: "ጌታ ግን መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ›› /2ቆሮ 3÷17/ የተቀደሰውን መለከት ሰምተናልና ምድራዊ የሆነውን በግ ከእንግዲህ አንሠዋም:: ነገር ግን የታረደውን አማናዊውን ሰማያዊውን በግ ኢየሱስ ክርስቶስን እንጂ:: "ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ›› ከአቤል ይልቅ በሚናገር በእርሱ በወርቀ ደሙ ታጥበናል /ኢሳ 53÷7/፤ እግሮቻችን በወንጌል ቃል ተጫምተዋል፤ "በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል "ያለው ያ ቅዱስ ሰው /መዝ 23÷4/ የተጽናናባቸው በትርና ምርኩዝ በእጆቻችን አሉ::

## በዓሉን በደስታ ስለማክበር

ስለዚህ በምንም አንጨነቅ፤ ምክንያቱም ቅዱስ ጳውሎስ "ጌታ ቅርብ ነው›› ብሏልና:: /ፊል 4÷5/ በፍፃሜውም በነገር ሁሉ እንዘጋጅ፣ ጌታችንም "የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና... በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን እናድርግ እንጂ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ





እርሾም አይደለም...፤ የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፣ እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ›› እንዳለ /ሉቃ 12÷40፤ 1ቆሮ 5÷8 ኤፌ 4÷22/:: በትሕትና፣ በየዋህነት፣ በንጹሕ ኅሊናም፣ ሕጉንም በቀን በሌሊት በማሰብ እንኑር:: ግብዝነትንና ማታለልን እናስወግድ፤ ትዕቢትና ሐሰትን ከእኛ እናርቅ:: ለእግዚ ብሔርና ለባልንጀራችን ፍቅርን እንያዝ:: አዲስ ፍጥረት እንሁን፤ አዲሱን ወይን መንፈስ ቅዱስን እንቀበል:: አዲሱን የእሸት በዓል እናክብር::

ዕለተ እሑድንም የሚመጣው አዲስ ዓለም ምሳሌ አድርገን እናክብራት:: ከዚያ በኋላ ዘላለማዊ ሕይወትን ገንዘብ እናደርግ ዘንድ በዚህች ዕለት ታላቅ ነገር ተደርጎልናልና:: ስለዚህ ከክርስቶስ ጋር ፍጹም በዓል እናደርጋታለን:: እንደ ቅዱሳኑም "ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ምስጋና መኖሪያ ሥፍራ እገባለሁና፤ በዓል የሚያደርጉ ሰዎች የደስታና ምስጋና ቃል አሰሙ›› እያልን እንጮኻለን/መዝ 42÷4/:: ሐዘን፣ ስቃይና ሰቆቃ ይሰደዳሉ፤ ደስታና ሐሴትም ይሆኑ ልናል፤ ለእነዚህ ነገሮች የተገባን እንሆናለን::

እንግዲህ በበዓሉ ድሆችን እናስታውስ፤ ለእንግዶችም ርኅራኄ ማድ ረግን አንርሳ፤ ከምንም በላይ እግዚአብሔርን በፍፁም ነፍሳችን በፍፁም ኃይላችን እንውደድ፤ ባልንጀሮቻችንንም እንደራሳችን እንውደድ:: ስለዚህ ዓይን ያላያቸውን፣ ጆሮ ያልሰማቸውን፣ በሰው ልብ ያልታ ሰቡትን እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጃቸውን ነገሮች እንቀበላለን:: /1ቆሮ 2/ በአንድ ልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፣ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ይሁን፤ ለዓለም ዓለም አሜን:: በተቀደሰ ሰላምታ ሰላም ተባባሉ:: ከእኔ ጋር ያሉ ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል::

# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሁለት

## ትእዛዛትን ስለማክበር

ወንድሞቼ ሆይ! በዓለ ፋሲካ /ትንሣኤ/ መጣ፤ በትውፊታችን መሠረት በቃሉ በአደግን ጊዜ በትጋት በዓሉን እናከብር ዘንድ እግዚ አብሔር እኛን ወደዚህ ጊዜ አመጣን። እንግዲህ ቀድሞ ከክርስቶስ ጋር በጽናት በቅድስና ለመመሳለስ አርአያ ምሳሌ ከነበሩ፣ ቀድሞ ይህን መሰል በዓል ካወጁ ከቅዱሳኑ ጋር ሰማያዊውን መንፈሳዊውን ደስታ ታላቁን በዓል እናክብር።

ቅዱሳኑ ወንጌልን ለመስበክ ብቻ የታመኑ አልነበሩም፤ የም ንመረምር ከሆነ እንደተጻፈው ኃይሉ በውስጣቸው ሲገለጥም እናያለን። ሐዋርያውም ‹‹እናንተም እኔን ምሰሉ›› /1ቆሮ 2/ ብሎ ለቆሮንቶስ ሰዎች ጽፏል። የሐዋርያው የቀደመ ሐሳብ እኛን ያነሣሣል። ለእነዚያ ለሰዎች በላከው ትእዛዛት ወስጥ በዚህ በበዓል ጊዜም በሰው ሁሉ ዘንድ በቦታም ሁሉ ደስታ እንዲሆን ታዟል። "እርሱ በእምነትና በእውነት ለአሕዛብም ሁሉ መምህር›› ነውና። በአጠቃላይ የቅዱሳን ሁሉ ትእዛዝ /ትምህርት/ እንዲሁ በተመሳሳይ ያነሣሣናል።

ሰሎሞንም በምሳሌው "እናንት ልጆች የአባትን ተግሳጽ ስሙ፤ ማስተዋልንም ታውቁ ዘንድ አድምጡ፤ መልካም ትምህርትን እሰጣ ችኋለሁና፤ ሕጌን አትተዉ፤ እኔም አባቴን የምሰማ ልጅ ነበርሁና በእናቴም ዘንድ እወደድ ነበር።›› እንዳለ / ምሳ 4÷1/ ፃድቅ አባት ልጆቹን ወደ መልካም ይወስዳል። በእርሱ የላቀ መልካም ሕይወት እውቀት መሠረት ሌሎችን ለማስተማር ትጉ በሆነ ጊዜ፤ የሚተቸው





ቀርቦ "አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን?" በተባለ ጊዜ አያፍርም /ሮሜ 2÷24/ ይልቁንም እንደ መልካሙ አገልጋይ ራሱን ያድናል ሌሎችንም ያተርፋል ጸጋም በእጥፍ እንዲ ፈጽም ባደረገው ጊዜ "አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ! ወደ ጌታህ ደስታ ግባ›› የሚለውን ቃል ይሰማል /ማቴ 25÷21/።

እንግዲህ ሁልጊዜም ቢሆን በተለይም ደግሞ በበዓላት ቀን ቃሉን ሰሚዎች ብቻ አንሁን! የመድኃኒታችንን ትእዛዛት ፈጻሚ ዎችም እንሁ። በሥራቸው ቅዱሳንን ብንመስል! ጊዜያዊ ያልሆነ በእውነት ለዘላለም ወደ ጸና ሰማያዊ ወደ ሆነው ወደ ጌታችን ደስታ አብረን እንገባለን።

## የክፉዎችን መንገድ መከተል እንደማይገባ

ክፉ አድራጊዎች ግን ከዚህ ዕጣ ፈንታ የላቸውም፤ የሥራ ቸውን ፍሬ ለቅሶና ሐዘን፣ ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። እነዚህ ደግሞ ምን እንደሚመስሉ እናስተውል፤ የቅዱሳንን የኑሯቸውን ፍሬ / አርአያነት/፣ ሰው ሲፈጠር የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ሆኖ ለባዊ ሆኖ የተፈጠረበትን የቀናውንም ማስተዋል አልያዙም። ማሰብ ማስተዋል ባለመቻላቸው ከእንሳሳት ጋር የሚነጻጸሩ ናቸው። ለእነርሱ በማይገቡ፣ ከሃይማኖት ሕግ ውጪ በሆኑ ደስታዎቻቸው እነርሱን መስለዋልና። ‹‹እንደ ተቀለቡ ፈረሶች ያስካካሉ›› /ኤር 5÷8/። በኃጢ አታቸው፣ በስሕተትም መንገዳቸው ሞትን ያመጣሉ።

ዮሐንስ መጥምቅም እንዳለው "እመንዝራ ትውልድ" ተብለው ተጠርተዋል /ማቴ 3÷7፤ ሉቃ 3÷7/ ስለዚህ ወደቁ፣ እንደ እባብም በትቢያ ላይ /በወርደት/ ይሳባሉ። ሐሳባቸው በዚህ ከሚታዩ ነገሮች በሻገር በሌላ ላይ አያርፍም። በእነዚህም ይመካሉ። በእነርሱም ይደ

ሰታሉ። በዚህም እግዚብሔርን ሳይሆን የሥጋቸውን ፍላጐት ያገለግላሉ።

ሰዎች እንዲህ እየኖሩ ሳለ ሰውን ወደጅ ቃል ግን የጠፋትን እነዚህን ፈልጐ በዚህ ብርቱ ምክንያት ወደ ዓለም መጣ። እነርሱን ከእነዚህ ከንቱ ነገሮች ነጻ ሊያወጣቸው /ሊገድባቸው/ ፈለገ። ሙሴ እንዲሁም አለ "በልባብና በልጓም ጉንጫቸውን እንደሚለጉሟቸው ልብ እንደሌላቸው እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ›› /መዝ 32÷9/ ክፉዎችን የሚመስሉ ግዴለሾች ነበሩና፤ ነቢዩም በመንፈስ "የሲዶና ነጋዴዎች ንገድ የሞላባችሁ ሆይ ጸጥ በሉ" ሲል ጸለየ።/ኢሳ 23÷2/።

መንፈስም በእነዚህ ቃል እንዲህ ሲል ተቃወማቸው። "አቤቱ ስትነቃ ምልክታቸውን ታስነውራለህ›› /መዝ 73÷20/ ስለዚህ ሰነፎችን ወደ መምሰል ተለውጠዋልና ወደ ተዋረደ ሐሳብ ወደቁ። ከሚገባ ውም አልፈው በማሰብ የመለኮትን ጥበብ እንደራሳቸው አስመሰሉ። የራሳቸውም የጥበብ ሥራ አስመሰሉት። ስለዚህም "ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፤ የማይጠፋውንም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ፤ ስለዚህ እርስ በእርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩስነት አሳልፎ ሰጣቸው›› /ሮሜ 1÷22-28/ ሲል ተናገራቸው። "እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ›› ያለውን / ኢሳ 40÷18/ የነቢዩን ድምፅ አልሰሙምና።

ዳግመኛም ዳዊት "የሚሠሩአቸውም የሚያምኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁኑ›› /መዝ 115÷8/ ያለውን አላስተዋሉምና እውነትን ማየት አልቻሉም። ስለዚህ ሐሳብ እንዳሌላቸው ፍጡራን ሆኑ። በነቢዩ "መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉም፤ ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም፤ እንዳይፈወሱ የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን፤





ጆሮቻቸውንም አደንቁር ዓይናቸውንም ጨፍን›› እንደተባለ /ኢሳ 6÷9/ በጨለማም ተጓዙ።

አሁንም እንዲህ ያሉት በዓልን አክባሪ ሆነው እስከዚህ ዘመን ድረስ አሉ። የበዓላትን ስም ማስመሰያ እና ማታለያ ያደርጋሉ። /1ነገ 12÷32/ ይልቁንም ከደስታ ይልቅ የሐዘንን ቀን ይገልጣሉ። /ኢሳ 48÷22/ ጥበብም "ደስታና ሐሴት ከአፋቸው ተወስዷል" እንዳለ። እነዚህ የክፉዎች በዓላት ናቸው።

## ክርስቶስን መስሎ ስለመኖር

ነገር ግን ከእነዚህ ክፉዎች በአንጻር በእግዚአብሔር የተፈጠ ረውን ሰው በእውነት የለበሱ የጌታ ብልህ አገልጋዮች /ኤፌ 4÷24/ የወንጌልን ቃል ይቀበላሉ፤ ለጢሞቴዎስም "በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን›› ተብሎ የተሰጠ ውን ትእዛዝ ያስባሉ። /1ጢሞ 4÷12/ ስለዚህ በዓልን በመልካም ያደርጋሉ። የማያምኑ እንኳን እነርሱን ሲያዩ "እግዚአብሔር በእውነት በመካከላቸው ነው›› ይላሉ /1ቆሮ 14÷25/

ስለዚህ ደቀመዝሙሩን የተቀበለ እርሱን የላከውን ይቀበላልና ቅዱሳንን የሚከተል ማንም በነገር ሁሉ ዓላማውን መድረሻውን ጌታን ያደርጋል። ጳውሎስም እርሱን የሚከተል በሆነ ጊዜ "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል" ለማለት በቃ። አስቀድሞም ጌታችን ከመለኮቱ ልዕልና የተነሣ "ከእኔ ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝ ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ።" አለ።

እንግዲህ ውሃን ወደ መታጠቢያው ቀድቶ፤ ራሱን በማበሻ ጨርቅ ታጥቆ የደቀመዛሙርቱና እግሮች ባጠበ ጊዜ "ያደረግሁላ ችሁን ታስተውላላችሁን፤ እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እን ዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ፤እንግዲህ እኔ ጌታና ምምህር ስሆን

እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና›› አለ /ዮሐ 13፥12/።

ወንድሞቼ ሆይ! የጌታችን መድኃኒታችንን የርኅራኄ ፍቅር እናድንቅ። እነዚህን ስጦታዎቹን በምን ኃይል በየትኛውስ መለከት እየጮኽን እናክብር! ከእርሱ አርአያውን የተሸከምን የያዝን ብቻ መሆን አይገባንም። ምሳሌውንና የሰማያዊውን ኑሮ መልክ ልንቀበ ልም ይገባል እንጂ። እርሱ የጀመረልንን ልንቀጥልበት ይገባል። መከራን እንቀበላለን፤ መከራ ግን በሌሎች ልናደርስ አይገባም፤ እንሰደባለን ነገር ግን ልንሳደብ አይገባም፤ የሚረግሙንን ልንመርቅ ይገባል፤ በጽድቅ ለሚፈርድ ዳኛ ለእግዚብሔር በነገር ሁሉ እንገዛ /1ጴጥ 2፥21-23/።

ስለዚህ ወደ ወንጌል ያዘነበሉና እንደ ወንጌሉም ቃል የሚኖሩ ክርስቶስን, የሚካፈሉ /የሚሳተፉ/ በኑሮም ሐዋርያቱን የሚመስሉ ይሆናሉ። ሐዋርያውም "ስለምታስቡልኝ አመሰግናችኋለሁ›› በማለት የቆሮንቶስ ሰዎችን ባመሰገነበት ቃል ለመመስገን የተገቡ ይሆናሉ።

ከዚያ በኋላ ግን ቃሉን መሣሪያ አድርገው የራሳቸውን የሥጋ ፍላጐት ብቻ መስማትን የሚመርጡ ለማሳት ደፍረው የሚመጡ ሰዎች አሉ። የሄሜኔዎስ፣ የእስክንድሮስ ተከታዮችን የመሰሉ ከእነሱም በፊት እንደነበሩ ሰዱቃውያን "በእምነት ነገር ጠፍተዋል›› እንዳለው በትንሣኤ ሙታን ምስጢር ላይ የሚሳለቁ ናቸው። ስለ እነርሱም ቀጥሎ "ይህቺን እእዛዝ አደራ እሰጥሃለሁ›› አለ /1ጢሞ 1፥20፣ 2ጢሞ 2፥18/። ያም ማለት ያስተማሩን ዋኖቻችን ከሰጡን ሌላ በእርግጥም ሌላ ማሰብ አይገባንም ሲለን ነው።





እነዚህ ክፉዎች ጌታችን እንደተናገረ የበግ ለምድ ለብሰው፣ በኖራ በዕብነ በረድ እንደተለሰነ እንደተጌጠ መቃብር በውጪያቸው የሚያስቱ ብቻ አይደሉም፤ በውስጣቸው ክፉ መሻትና ጥፋት እያለ የእግዚብሔርን ቃልም በአፋቸው ይናገራሉ እንጂ።

አስቀድሞ በአፍአ ያለ መልካም የሚመስልን ገጽታ ይዞ ያስት የነበረው የቀደመው እባብ ነበር፤ እርሱም ሔዋንን በማስመሰል ያናገራት ኋላም ያሳታት ከመጀመሪያም የክፋት አስገኚ የሆነው ዲያብሎስ ነው። ከእርሱ በኋላም የኑፋቄ አስገኚዎች ሁሉ ተከተሉት። ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያነቡ ነገር ግን ቅዱሳን የተረዱትን ምስጢራቸውን ያልተረዱ ናቸው። መጻሕፍቱንም እንደ ሰው ወግ ቆጠሯቸው። ምስጢራቸውን በሚገባ አላወቁም፤ ያላቸውንም ኃይል አልተረዱምና። /ማቴ 22፥20/

ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ካለው የጥፋት መንገድ የራቁትን የቆሮንቶስን ሰዎች በእውነት አመሰገነ፤ ምክንያቱም የእነርሱ ሐሳብ በእርሱ በመምህራቸው ሐሳብ መሠረት ነውና። ጌታችንም አይሁድን በእውነት ይወቅሳቸው ነበር "እናንተስ ስለወጋችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለምን ትተላለፋላችሁ?" /ማቴ 15፥3/ ከእግዚአብሔር የተሰጡትን ትእዛዛት ለውጠው በራሳቸው ማስተዋል የተፈጠሩትን የሰዎችን ወግ ማክበርን መርጠዋልና። ዳግመኛም ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ከዚህ አደጋ እንዲጠበቁ "ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን›› ብሎ ጽፎላቸዋል። /ገላ 1፥ 9/።

## ስለቅዱሳን ምስክርነት

በቅዱሳን ትምህርትና በሰው በተፈጠሩ ተረቶች /ወጐች/ መካከል ኅብረት የለም። ቅዱሳን የእውነት አገልጋዮች ናቸውና መን ግሥተ ሰማይን ይሰብካሉ፤ ነገር ግን በዚህ ተቃራኒ የተሰለፉ ስለ

ምድራዊ መብል ከማሰብ ባሻገር ሃይማኖታዊ ሐሳብ የሌላቸው እሉ፡፡ ፍፃሜያቸው የጥፋት ሐሳብ ነውና " ነገ እንሞታለንና እንብላ እንጠጣ" ይላሉ /1ቆሮ 15÷33/፡፡

ስለዚህ ቅዱስ ሉቃስ የሰዎችን የፈጠራ ተረቶች /ወጎች/ እንዳንቀበል አስጠንቅቋል፡፡ ስለዚህ ቅዱሳን የነገሩትን ተርኳል፡፡ በወንጌሉም መጀመሪያ እንዲህ ይላል "የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስ ተላለፉልን፣ በእኛ ዘንድ ስለተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለሞከሩ እኔ ደግሞ ስለተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ›› /ሉቃ 1÷1/ እነዚህ ቅዱሳን የሃይ ማኖትን ምስጢራት ለመመስከር ሳይበረዙ፣ ሳይከለሱ የተሰጣቸውን የሰጡ ናቸው፡፡ ስለዚህም አምላካችን ደቀመዛሙርቱ አድርጓቸዋልና አስተማሪዎቻችን መሆን ተገብቷቸዋል፡፡ ለእነርሱ ብቻ እንዲያስተ ውሉት ተሰጣቸው፡፡ ለእነርሱ ብቻ "የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው›› /1ጢሞ 1÷15/፡፡ እነዚህ ግን ደቀመዛሙርት አይደሉም፤ የሰሙት ከሌሎች ነውና፡፡ እኛ ግን የዓይን ምስክሮችና የቃሉ አገልጋዮች የሚሆኑት ከእነርሱ የሰሙ እንዳስተላለፉልን እንመሰክራለን፡፡

ስለዚህ አንዳንዶቹ በጌታችን መድኃኒታችን የተሠሩትን ገቢረ ተአምራት ነገሩን፡፡ ዘላለማዊ አምላክነቱንም ሰበኩ፡፡ ሌሎችም ከድንግል መወለዱን ጻፉ፤ ቅዱሱን የፋሲካ በዓልም "ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷል" እያሉ አወጁ፡፡

ስለዚህ በተናጠልና በጋርዮሽም ሆነን በዓለም ያለን አብያተ ክርስቲያናት "በወንጌል እንደምሰብከው ከሙታን የተነሣውን ከዳዊት ዘርም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ›› ተብሎ እንደተጻፈ እንዘከ





ረዋለን፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የገለጠውን የትንሣኤውን ነገር አንርሳ "በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው›› ብሏልና፡፡ ከእርሱም ጋር አስነሣን፡፡

ዘወትር በልባችን የሆነ በዚህ ቅዱስ የትንሣኤ ደስታም የሞትን ሰንሰለት ፈታ፡፡ በመርገም ፈንታ በረከትን አበሰረን፡፡ በሐዘንም ፈንታ ሐሴት፣ በሙሾም ፈንታ በዓልን አደረገ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ›› ብሎ እንዳዘዘው ዘወትር ደስ ይለናል /1ተሰ 5÷17/

ስለዚህ ከአባቶቻችን በተቀበልነው መሠረት ይህንን ወቅት ለማስታወስ ጊዜውን ለማወጅ ቸል የምንል አይደለም፡፡ ስለዚህ የሐዋርያት ትውፊት እንዲጠበቅ እንጽፋለን፡፡ ለጸሎት በተሰበሰብን ጊዜ አንዳችን አንዳችንን እናስብ ዘንድ በዓሉን በጋራ እናክብር፡፡ በአንድ አፍም በእውነት ለጌታችን ምስጋና እናቀርብ ዘንድ፡፡ መዝ ሙረኛው "ምላሴ ጽድቅህን ሁልጊዜም ምስጋናህን ይናገራል›› እንዳ ለው /መዝ 35÷28/ ለእርሱ ምስጋና እያቀረብን የቅዱሳንንም ፍኖት መከተል የሚገባ ነው፡፡ ስለዚህ በዓሉን በእውነት ባከበርን ጊዜ በሰማይ ለሚሆን ደስታ የተገባን ሆነን እንቆጠራለን፡፡

**ስንብት**

ከእኔ ጋር ያሉ ወንድሞች ሰላምታ ያቀርቡላችኋል፤ በተቀደሰ ሰላምታ ሰላም ተባባሉ፡፡

# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሦስት

## በዓሉን በትኩረት ስለማክበር

ዳግመኛ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ከምንም በላይ በጸሎት የምንተጋበት፤ በሕግም እንድንጠብቀው /እንድናከብረው/ ያዘዘን የበዓል ቀን ወደ እኛ ቀርቧል፤ በዝምታ ብናልፈው ለእግዚብሔር ደስ የሚያሰኝ ያልተቀደሰ ሐሳብ ይሆንብናል፡፡ እንደምታውቁት መከራ በሚያደርሱብን በእነዚያ ሥር የተገደብን ነንና፤ በእነርሱም ምክንያት የበዓሉን ጊዜ ለእናንተ ማብሰር ባልቻልን ነበር፤ ነገር ግን "በመከራ ያሉትን የሚያጽናና" /ዕብ 2÷14/ ለእርሱ ምስጋና ይሁንና በከሳሾቻችን ክፋት አልተሸነፍንም፤ ዝምም አላልንም፡፡ እንደውም አማናዊ ቃልን እያከበርን ከእናንተ ጋር በኅብረት ቆመን በበዓላችን ቀን ከፍ አድርገን ድምፃችንን እናሰማለን፡፡ የሁሉ አምላክ እግዚአብሔር "ተናገር፤ የእስራኤል ልጆች ፋሲካን ያክብሩ" ብሎ አዘናልና/ዘኁ 9÷2/፡፡

በመዝሙረኛው ቃል "በመባቻ ቀን በከፍተኛው በዓላችን ቀን መለከትን ንፉ...›› ይላል /መዝ 81÷3/፤ ነቢዩም እንዲህ እያለ ይጮኻል "ይሁዳ ሆይ በዓሎችህን አድርግ›› /ናሆ 1÷15/ ያልተማራችሁ እንደሆናችሁ አስቤ ቃልን የምልክላችሁ ሆኜ አይደለም፤ ነገር ግን ለማያውቁት ለእነሱ የተገለጠ ሆኖ እንዲገኝ በማሰብ ነው፡፡

ምንም እንኳ ሰዎች የለያዩን ቢሆንም እግዚአብሔር ግን አሁንም አንድነታችንን አጽንቷል፡፡ ስለዚህ እስከ አሁንም አንድን በዓል እናከብራለን፤ አንዱንም ጌታ ዘወትር እናመልካለን፡፡ ዓመታዊ በዓሉን የምናከብረው ቀናትን እንደሚያከብሩ ሆነን አይደለም፡፡ እንዲህ የሚያደርጉትን "ቀንና ወርን ዘመንንም ዓመትንም በጥንቃቄ ትጠብ





ቃላችሁ›› ባለው ቃሉ ገስጿልና፡፡ /ገላ 4÷10/ ይልቁንም እግዚአብሔር በየሥፍራው የምናገለግል እኛ ሁላችን በጋራ ተሰብስበን በጸሎታችን ወደ እግዚአብሔር እየተማጸንን ደስ ይለን ዘንድ የበዓሉን ቀን ልዩ /ከፍተኛ/ እናደርገዋለን፡፡

እንግዲህ ቅዱስ ጳውሎስ "ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷል" እያለ የበዓልን መቅረብ ሲያበሥረን ቀናትን እያበሰረን አይደለም፤ ስለቀኑ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ ብለን ይህንን በዓል እናከብራለን እንጂ ፡፡ እንግዲህ እርሱን ወደ ማገልገል ያቀርበን ዘንድ በቃሉ ዘላለማዊነት እንመሰጥ፡፡ በዓሉን የምናደርገው ነፍስን ለማገልገል አይደለምን፤ አገልግሎቱስ ምንድ ነው፤ ለእግዚአብሔር ብርቱ ጸሎትና የማያቋርጥ ምስጋና ማቅረብ አይደለምን፡፡

## በዓሉን አለማክበር የተሰጠን ጸጋ መናቅ ስለመሆኑ

ከዚህ በዓል የሚርቁ የማያመሰግኑ ግን ከእርሱ ከእግዚአብሔር ከሚፈልቀው ደስታ የተጐዱ ናቸው፡፡ "ደስታና ሀሴት ከአፋቸው ተወስዷል›› /ኤር 7/ ሰላም እንዲኖራቸው አልፈቀደም "ለክፉዎች ሰላም የላቸውም›› ይላል፡፡ /ኢሳ 48÷22/ በሐዘንና በስቃይ ይደክማል፡፡ በወንጌል በጌታ ዓይን እልፍ የይቅርታ መክሊት ዕዳ እንዲቀርለት የታደለው ቢሆን እንኳ የእነዚያን የእርሱን ባሮች ባልንጀሮች ዕዳ ግን እንዲከፍሉ ያስጨናቂ ሆኖ ነበር፡፡ ታላላቅ ይቅርታዎችን የተቀበለ እርሱ ታናናሾቹን ይቅር ለማለት ለመራራት ዝንጋኤ ነበረበት /ማቴ 18÷24/ ፡፡

ትክክለኛው የቀናው መንገድ ግን ርኅራኄ የተደረገለት ማንም እርሱም ለታናናሾቹ ርኅራኄን ያደርግ ዘንድ ይፈለግበታል፡፡ አንድ መክሊት የተቀበለው በጨርቅም ጠቅሎ የቀበራት እርሱ በመ ጨረሻ የማያመሰግን ሆኖ ወደ ውጪ ይጣላል "አንተ ክፉና ሀኬተኛ ባሪያ፤

ካልዘራሁበት እንዳጭድ ካልበተንሁበትም እንድሰበስብ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፤ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት፤ ዐሥር መክሊትም ላለው ስጡት›› የሚል ቃልንም ይሰማል። /ማቴ 25፥26/ በእርግጥም የእርሱ የሆነውን አትርፎ ለጌታው የሚያስረክብ የሰጪውን የርኅራኄ ምስጋና አግኝቷልና፤ የተሰጠውንም መክሊት ዋጋ ይጨምርለታል /ይሰጠዋል/።

ተሰጥቶት ያላተረፈ ግን መልካም አላደረገም። እንግዲህ ሰጪው አስቀድሞም ባይሰጠው፣መክሊቱም የማያተርፍ ሆኖ ቢሆን ለእርሱ መልካም በሆነ። በእርሱ ጥፋት /ጉድለት/ አልነበረበትም። ነገር ግን ሁለቱም ማለትም ሰጪውም መልካም፣ የተሰጠውም ነገር ትርፋማ ነበር። ስለዚህ በእምላካዊ ምሳሌያት መሠረት "እህልን የሚያስቀር ሰው በሕዝብ ዘንድ ይረገማል›› /ምሳ 11፥26/ ስለዚህ ጸጋን የሚያቃልል የሰጠውንም ያለአግባብ የሚቀብር እርሱ እንደማ ያመስግኑ እና ክፉዎች ወጥቶ ለመጣል የተገባ ነው። በዚህ ገለጸ መሠረትም "አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ›› እንደተባለው የሚያተርፉ በአንጻሩ የተመሰገኑ /ብፁዓን/ ናቸው /ማቴ 25፥23/።

ይህ ትክክለኛና ምክንያታዊ ነው። ምክንያቱም ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚነግሩት አንድ ሰው የተቀበለውን ያህል ያገኑ / የተሰጠውን/ ያህል ያተርፋል /ይፈለግበታልና/። አዎን ወዳጆቼ ፈቃዳችን ከእግዚአብሔር ጸጋ ጋር መስማማት ይገባዋል። በአጭሩ እንዳይቀጭ፤ ፈቃዳችን ከንቱ ሆኖ እንዳይቅር፤ የተሰጠንም ጸጋ እንዳይለየን፤ ጠላትም ባዶና ራቁት ሆነን እንዳያገኘንና ወደ ውስጣችን እንዳይገባ፤ በወንጌል "ቢመጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል፤





ከዚያ ወዲያ ይሔድና ከእርሱ የከፉትን ሰባት ሌሎችን አጋንንት ከእርሱ ጋር ይወስዳል ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብሰበታል›› ተብሎ እንደተቀጠቀሰው / ማቴ 12፥43/። ከመልካም ነገር መለየት ለክፉ መንፈስ መግቢያ ቦታ ይሰጣልና።

ከዚህ ተጨማሪም በተሰጠን ጸጋ የማናተርፍበት ሆነን እንዳ ንገኝ የሐዋርያት ትእዛዝ አለ። ስለ እነዚያ ነገሮች በተለይም በደቀ መዛሙሩት በኩል "በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል... ምድሩን የሚያርስ ሰው እንጀራን ይጠግባል...የታካች መንገድ እንደ እሾህ አጥር ናት›› ብሎ በጥብቅ ያዘናል /1ጢሞ 4፥14፤ምሳ 12፥ 11፤ 15፥19/። ስለዚህ መንፈስ ያን ሰው በእነርሱ ውስጥ እንዳይ ወድቅ። "ጥጋቱን እርሻ እረሱ በእሾህም ላይ አትዝሩ "በማለት ቀድሞ ያስጠነቅቀዋል /ኤር 4፥3/።

እንግዲህ አንድ ሰው የተሰጠውን ጸጋ የሚንቅ /ቸል የሚል/ በሆነ ጊዜ፣ ስለዓለምም መጨነቅ በጀመረ ጊዜ ስለዓለሙ በማሰብ የወደቀ ይሆናል፤ ለከንቱ ሥጋዊ ፍትወቱ የተሰጠ ይሆናል። በመከራ ጊዜ ይሸነፋል፤ በፍፃሜውም ፍሬ የሌለው ይሆናል። አሁን ግን ነቢዩ እንዲህ ያለውን ቸልተኝነት ፍፃሜውን "የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚያደርግ ርጉም ይሁን›› እያለ ይነግረናል። /ኤር 48፥10/

የእግዚአብሔር አገልጋይ ጥንቁቅና ትጉ መሆን ይገባዋልና። በተጨማሪም እንደ ነበልባል የሚቃጠል /የሚነድ/ በጥልቅ መንፈስ ውስጥ በሆነ ጊዜ ሁሉንም የሥጋ ፍላጐቶች አጥፍቷልና፤ እንደ ቅዱሳን አባባል "የሚበላ እሳት ወደ ሆነ ወደ እርሱ ወደ እግዚአብሔርም መቅረብ ይቻለዋል /ዘዳ 4፥24፤ ዘዳ 9፥3፤ ዕብ 12፥29/።

ስለዚህ የሁሉ ጌታ እግዚአብሔር "መላእክቱን መንፈስ የሚ

ያደርግ፤ አገልጋዮቹን የእሳት ነበልባል" /መዝ104፥4/ ከግብፅ በወጡ ጊዜ ሕዝቡን እግዚአብሔር ለእነርሱ ሕግን የሰጠበትን ተራራው እን ዳይቀርቡ ከለከለ፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ያለ ብቃት የነበራቸው አልነ በሩምና ነገር ግን በመንፈስ የበረታ፣ የማይጠገብ ጸጋ ባለቤት የሆነውን ብፁዕ ሙሴን ግን ወደ እርሱ ጠራው፡፡ "ሙሴም ብቻውን ወደ እግዚአብሔር ይቅረብ›› አለው፡፡ /ዘጸ 24፥2/ በዳመናውም ተሰወረ፡፡ ተራራውም በጨለ ጊዜ አልተጐዳም ነበር፡፡ ይልቁንም በዚያ "በምድር ላይ እንደተፈተነ ሰባት ጊዜ እንደተጣራ ብር የእግዚአብሔር ቃላት የነጹ ቃላት›› /መዝ 12፡6/ ይወርዳሉ፡፡

## የመንፈስን ጸጋ ስላለማጥፋት

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ለእኛ የተሰጠን የመንፈስ ጸጋ በቅዝቃዜ ማደግ እንደማይገባው በተማጽኖ ሲመክር "መንፈስን አታጥፉ›› /1ተሰ 5፥10/ ብሏል፡፡ አስቀድሞ የተሰጠንን ጸጋ እስከፍፃሜው አጽንተን ብንገኝ ከክርስቶስ ተሳታፊዎች ሆነን እንጸናለን፡፡ "አታጥፉ" ብሎ ሲናገር የመንፈስ ጸጋ በሰዎች ኃይል ውስጥ ሲያድር በእነርሱ አንጻች ስቃይ ወይም ጤና የሚያመጣ ሆኖ አይደለም፡፡ ነገር ግን ክፉዎችና የማያመሰግኑ ሰዎች በግልጽ እርሱን ለማቀዝቀዝ የሚመኙ ናቸውና ነው፡፡ Cኩስ የሆነውን /ያልተቀደሰውን/ ይወዳሉ፤ ባልተቀደሰ ግብራቸው መንፈስን ያሳድዳሉና ነው፡፡ "ተግሳጽን የሚገልጽ መንፈስ ቅዱስ ክፉውን ትምህርት ያርቃልና ከሰነፎች ልቡና ድል ነሥቶ ይሔዳልና በሚመጣም ጊዜ ክፉውን ይዘልፈዋል›› /ጥበብ 1፥5/፡፡ አሁን ከማስተዋል ውጪ ሆነው አታላዮች፣ ኃጢአትን ወዳጆች ናቸውና አሁንም ገና በጨለማ ይጓዛሉ፡፡ "ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር›› /ዮሐ1፥9/ የተባለው ብርሃን የላቸውምና፡፡





## ስለቃሉ እሳትነት

ነቢዩ ኤርምያስ "በአጥንቶቼ ውስጥ እንደገባ እንደሚነድ እሳት ያለ በልቤ ሆነብኝ ደከምኩ መሸከምም አልቻልኩም›› /ኤር 20፥9/ እንዳለው እንዲህ ያለው ኤርሚያስ የተሸከመው እሳት ቃሉ ነው፡፡ መልካምና ሰው ወዳጅ የሆነ እርሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ቃሉን በምድር ላይ አመጣ፡፡ "የነደደ ከሆነ ዘንድ ምን እፈልጋለሁ›› አለ፡፡ /ሉቃ 12፥49/

በነቢዩ ሕዝቅኤል እንደተመሰረከው እርሱ የሰውን ከሞቱ ይልቅ መመለሱን ይሻል፡፡ /ሕዝ 18፥23/ ስለዚህ ክፉው ሁሉ ከሰዎች ውስጥ ተቃጥሎ እንዲጠፋ ነፍስም ወደ ንጽሕና ደርሳ ፍሬን ታፈራ ዘንድ፤ በእርሱም ላይ የዘራው ዘር ሠላሳም ስድሳም መቶም ያማረ ፍሬ /ማር 4፥20/ ያፈራ/ ዘንድ ነው፡፡ ለምሳሌ እነ ቀለዮጳ በመጀመሪያ ከማስተዋል ዕጦት የተነሣ ቢደክሙም በኋላ ግን በመድኀኒታችን ቃል ልባቸው ይቃጠል ነበር፡፡ ከዚያ የእርሱን የትምህርቱን ፍሬ አፈሩ፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ከሥጋና ደም ሳይሆን ከጸጋ በሚመነጭ በዚህ እሳት በተያዘ ጊዜ የቃሉ ሰባኪ ሆነ፡፡

## ስለምስጋና ሕይወት

ነገር ግን እነዚያ ከለምጻቸው የነጹት ዘጠኙ ከለምጽ በነጹ ጊዜ የፈወሳቸውን ጌታ የማያመሰግኑ ነበሩ፡፡ የሐዋርያነት ዕጣ የደረሰው የጌታም ሐዋርያ ተብሎ የተጠራ የአስቆሮቱ ሰው ይሁዳ፤ በመጨረሻ ‹‹እንጀራዬን የበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ›› /መዝ 41፥9/ የተባለው ከማያመሰግኑ አንዱ ሆነ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ የስን ፍና ሥራቸውን ዋጋ ያገኛሉ፡፡ የማያመሰግኑ ሆነው በመገኘታቸው ምክንያት የሚጠብቃቸው ነገር ከንቱ ይሆናል፡፡ ለማያመሰግኑ ተስፋ

የለምና፡፡ እንግዲህ የመለኮትን ብርሃን ለናቁ ለእነዚያ ለሰይጣንና ለመላእክቱ የተዘጋጀው የመጨረሻው እሳት ይጠብቃቸዋል፡፡ በዚያን ጊዜ የማያመሰግኑ ሁሉ ፍፃሜ ይሆናል፡፡

ነገር ግን ጌታችን እርሱን እስከ ዘለዓለም የሚያመሰግንን፣ ውዳሴንም የሚያቀርብ ታማኝ አገልጋይን ይወዳል፡፡ እንዲህ ያለው ሰው የሚኖርበት ዘመንና ሁኔታ ክፉም ሆነ በጎ የጊዜውን ነገሮች ሳያማርር የምስጋና መስዋዕትን ሲያቀርብ ይገኛል፡፡ ለጊዜያት ሁሉ ባለቤት ለእግዚአብሔር በመገዛት ይጸናል እንጂ፡፡

አስቀድሞ ከሰው ሁሉ በላይ የትዕግስት ባለቤት የሆነው ኢዮብ እነዚህን ነገሮች በብልጽግናው በመልካሙ ዘመኑ ያሰባቸው ነበር፤ ስለዚህ በመከራና በችግር ዘመኑ በትዕግስት ጸና፡፡ መከራን እየተቀበለ ያመሰግን ነበርና፡፡ ገርና ትሑቱ ክቡር ዳዊት በመከራው በስደቱ ዘመን የምስጋናን መዝሙር ‹‹እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ›› እያለ ይዘምር ነበር /መዝ 34፥1/፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም በሁሉም መልእክቶቹ ውስጥ እግዚአብሔርን ማመስገንን አልተ ወም፡፡ በምቹ ጊዜ ምስጋናን ሳያደርግ አልተወም፤ በመከራውም ጊዜ ጌታውን ያከብራል "መከራ ትዕግስትን እንዲያደርግ ትዕግስትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደረግ እያወቅን በመከራችን ደግሞ እንመካለን›› ይላል /ሮሜ 5፥3/፡፡

እንግዲህ የእነዚህ ቅዱሳን ሰዎች ተከታይ እንሁን! ለምስ ጋና የሚሆን ጊዜን አናሳልፍ፤ ይልቁንም አሁን መናፍቃን በእኛ ላይ በሚሳለቁበት በመከራ ጊዜ "ይህ ሁሉ በእኛ ላይ ደረሰ አልረ ሳንህም›› በማለት የቅዱሳንን ቃል እየተናገርን ጌታን እናመሰግ ነዋለን፡፡ /መዝ 44፥17/ አይሁድም ከኤዶማውያን ድንኳኖች /ያዕ 5 ፥13/ በሚመጣ ጥቃት መከራ የተቀበሉ ቢሆንም፤ በኢየሩሳሌም





በክፉ ጠላቶች የተጨቆኑ ቢሆንም አልጠፉም፤ እጅግ አብዝተው እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር፡፡

እንግዲህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ! የጌታን ቃል እንዳንናገር ቢያደናቅፉንም የበለጠ ለማወጅ እንነሣለን፤ መከራ ቢደርስብንም መዝሙራቱን እንዘምራለን፤ ለመናቅ የተሰጠን ሆነን ተቆጥረናልና፡፡ ስለ እውነትም በመጨነቅ እንደክማለን፡፡ በጽኑ ሐዘን የተያዝን ብንሆንም እናመሰግናለን፡፡

ዘወትር ማመስገን ሥራው የሆነ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዚሁ መንገድ ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ " በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር  በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አሳውቁ›› እያለ /ፊል 4፥6/ ያነሣሣናል፡፡ በተቸገርን ጊዜ መውጫውን መንገድ /መፍትሔ/ እንደሚሰጠን መመስከራችንን እንቀጥላለን፡፡ "ሳታቋርጡ ጸልዩ በሁሉ አመስግኑ›› /1ተሰ 5፥17/ ምክንያቱም በሚያመሰግኑና "በአንተ ከጥፋት እድናለሁና በአምላኬም ቅጥሩን እዘላለሁ›› /መዝ 18፡29/ ብለው ቅዱሳን እንደተናገሩት የጠላትን ቅጽር ተሻግረው በሚዘምሩ ጊዜ የበለጠ ጽኑ እንደሆኑ አውቀን ዘወትር ጸንተን እንቁም፡፡ ይልቁንም አሁን ብዙ መከራ እየተቀበልን፣ ብዙ መናፍ ቃን በእኛ ላይ በተነሡብን በዚህ ጊዜ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ "የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁ›› /1ጴጥ 1፥13/ ወደ እኛ የቀረበ ውን ቅዱስ በዓል በምስጋና እናክብረው፡፡

## ስለበዓለ ፋሲካ አከባበር

"የወገቡ መታጠቂያ ጽድቅ የጎኑም መቀነት ታማኝነት ይሆናል›› ተብሎ እንደተጻፈለት እያንዳንዳችን ከእሴይ ሥር በወጣ በትር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ  /ኢሳ 11፥5/ እጆች ውስጥ ነን፡፡ እግሮቻችንም ለወንጌል በመዘጋጀት ተጫምተው የቆሙ ነንና በዓሉንም

ቅዱስ ጳውሎስ "በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን እናድርግ እንጂ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ እርሾም አይደለም›› እንዳለው እናክብር /1ቆሮ 5÷8/፡፡ እኛን ባሮቹን አክብሮን በክርስቶስ እንደታ ረቀን በእርሱም ላይ ባለ እምነት አንድ ሆነን እናክብር፡፡ ለእውነት እንግዳ በሆኑ ቃላቸውና ፈቃዳቸው ባዋረዳቸው መናፍቃን ሥራ አንርከስ፤ ነገር ግን በመከራችን ደስ ቢለን፤ ከብረት አጥርና ከጨለማ ሰብረን እንወጣለን፤ አስፈሪውን ባሕረ ኤርትራን ያለጉዳት እናልፋለን፡፡

እንዲሁም የመናፍቃንን መታወክ ባየን ጊዜ ከነቢዩ ሙሴ ጋር ሆነን ያንን ታላቅ የውዳሴ መዝሙር ‹‹በክብር ከፍ ከፍ ብሏልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ›› እያልን እንዘመራለን /ዘጸ 15÷1/፡፡ ይህንን የውዳሴ መዝሙር ስንዘምር በውስጣችን ያለ ኃጢአት ወደ ባሕሩ ይጣላል፡፡ በበረሃውም መካከል እናልፋለን፡፡ በአርባ ቀናቱ ጉዞም በጾም በጸሎት በመታዘዝ በመልካም ሥራ እንጸናለን፡፡ በኢየሩሳሌምም ሆነን ቅዱሱን ፋሲካ መብላት ይቻለናል፡፡

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ በዚህ ረዘም ባለ የጾም ወራት በጾም በጸሎት በማስተዋል በመቃኖቻችን ወርቀ ደሙን እንቀበላለን፡፡ ከዚያም ከሚያስፈራው ጠላት እናመልጣለን፡፡ /ዘጸ12÷7-23/ ስለዚህ በዕለተ ቀዳሚት ምሽት ‹‹ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈል ጋላችሁ? ተነሥቷል እንጂ በዚህ የለም›› የሚለውን የመላእክት አዋጅ /ቃለ ብሥራት/ እንሰማለን፡፡ ከዚያም ለእኛና ለባልንጀሮቻችን ሁሉ ጸጋና ሰላም የሰጠበትን ታላቁን ዕለተ ትንሣኤ እሑድን እንቀበላለን፡፡ እንግዲህ እርሱ ለዚህ ካደረሰን በዓሉን እንደፈቃዱ ልናከብር ይገባል፡፡





## ስንብት

ዘወትር ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እናመስግን፡፡ በእርሱም ለአብ ክብርና ኃይል ለመንፈስ ቅዱስም ይገባል፤ ለዓለም ዓለም አሜን፡፡ እርስ በእርሳችሁ በተቀደሰ ሰላምታ ሰላም ተባባሉ ከእኔ ጋር ያሉ ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል፡፡ የምወዳችሁ የምናፍቃችሁ ወንድሞቼ ጤናም ትሆኑ ዘንድ፣ በጌታም ታስተውሉ ዘንድ እጸልያለሁ፡፡

# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አራት

## በዓሉን ስለማብሠር

ወዳጆቼ! ይህን መልእክት ከተገቢው ጊዜ አዘግይቼ ላክሁላችሁ ለማዘግየቴ ይቅርታ እንደምታደርጉልኝ አምናለሁ። አጅግ በረዘሙ ጉዞዎችና በደዌ ሥጋ በመፈተኔ ምክንያት ነው። በእነዚህ ምክንያቶች እንቅፋት ቢያገኘኝም፣ ከወትሮው ይልቅ የጸኑ የመከራ ማዕበላት ቢከሰቱም ሳልጽፍላችሁ መቅረት ግን አላሰብሁም። ረጃጅም ጉዞዎቼን እና የጸና ሕመሜን መቋቋም ቢሳነኝም የበዓልን ማስታወሻ ለእናንተ መላኬን አልረሳም። ስለዚህ በተሰጠኝ ሓላፊነት /ግዴታ/ መሠረት በዓሉን አሁን አበስራችኋለሁ። ምንም እንኳ መልእክቱ የተጻፈበት ጊዜ ማብሠር ከለመድንበት ጊዜ የዘገየ ቢሆንም አሁንም በሚገባው ጊዜ ውስጥ እንደሚደርሳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

## በዓሉ የድል በዓል ስለመሆኑ

ወዳጆቼ! ጠላቶቻችን እኛን የሚያሳድዱበት ምክንያት ሳይኖራቸው ያለማቋረጥም ያሳድዱናልና አፍረዋል፤ በቤተክርስቲያንም የተወገዙ ሆነዋል። ስለዚህ የበዓልን መዝሙር መዘመር ይቻለናል፤ በፈርዖንም ላይ የድልን መዝሙር "በክብር ከፍ ከፍ ብሏልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ፤ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባህር ጣለ» እያልን እንጮኽበታለን / ዘጸ 15÷1/።

ወዳጆቼ ሆይ! እንግዲህ ከበዓል ወደ በዓል መራመዳችን መልካም ነው። ዳግመኛም የበዓል ጉባኤያት፣ ትግሐ ሌሊትም ሐሳባችንን ያነሣሣልና፤ ይህንኑ ትጋት ጠብቀን መሔዳችን መልካ ሙን ወደ





ማሰብ፣ በእርሱም ወደ መመሰጥ ያደርሰናል። እነዚህን ቀናት እንደ ሐዘንተኞች ሆነን ልንፈጽማቸው አይገባም፤ በመንፈሳዊ ማዕድ መደሰትን፣ የሥጋ መሻታችንን ለነፍሳችን ማስገዛትን መሻት አለብን። በእነዚህ መንገዶች እንደ ቅድስት ዮዲት የሚገዳደሩንን ማሸነፍ ይቻለናል /ዮዲ 8÷8/ እርሷ በጾም በጸሎት አስቀድማ በተጋች ጊዜ ጠላቶቿን ማሸነፍ ሄሎፎርኒስን መግደል ችላለችና።

ቅድስት አስቴርም በወገኖቿ ላይ ጥፋት በመጣ ጊዜ፣ እስራኤልም ለጥፋት በተሰጠች ጊዜ የዚያን ጨካኝ ገዢ /የንጉሥ ባለሟል/ የክፋት ሤራ ያሸነፈችው በሌላ መንገድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት በነበረው ጾም ጸሎት ነበር። የወገኖቿን ጥፋት ወደ ልማት /ድኅነት/ ተለወጠ። /አስቴ 4÷16/ እነዚህ ጊዜያት እንግዲህ ለእስራኤል ወገን ሁሉ በዓላቱ ናቸው።

አስቀድሞም ጠላት የተረታበት፣ ሤራ የተሰበረበት፣ እስራኤል የዳነበት ጊዜ ሁሉ በዓላት ሆነው ተሠርተዋልና። ስለዚህ በዘመነ ብሉይ ብፁዕ መሴም እናከብረው ዘንድ ታላቁን የፋሲካን በዓል ሠራልን። ምክንያቱም ፈርዖን ተገድሏልና ሕዝቡም ከባርነት ነጻ ወጥቷልና። እንዲህ ያሉ ጨካኝ ገዢዎች የተረቱበት የተሸነፉበት ጊዜ ሁሉ በዓላት /የተቀደሱ ቀናት/ ሆነው ይከበሩ ነበር።

ወዳጆቼ አሁን ግን የዓለሙ ጨካኝ ጠላት የሆነው ዲያብሎስ ተረቷልና በዓሉን ለጊዜው ሳይሆን ዘላለማዊና ሰማያዊ አድርገን እናከብራለን። የምናከብረው በጥላው ውስጥ ሆነን አይደለም፤ በአካሉ በእውነቱ ውስጥ ሆነን እንጂ። በእግዚአብሔር በግ ሥጋ ተሞልተናልና በዓሉ ፍጹም ሆኗል። የበሮቹ መቃን በደሙ ተቀብተዋልና ጠላትን ለማሸነፍ ረድኤት ሆኗል። አሁን ግን የአብን ቃል በመብላት የልባችን መቃኖች በሐዲስ ኪዳን ደሙ ታትመዋል /ማቴ 26÷28/።

መድኃኒታችን “እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ሁሉ ኃይል ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ›› ብሎ የሰጠንን ጸጋ አውቀናል /ሉቃ 10÷19/። ከእንግዲህ ሞት አይገዛንም። በሞትም ፈንታ እርሱ ሕይወታችን ሆነ። ጌታችን “እኔ ሕይወትም ነኝ›› እንዳለ /ዮሐ 14÷6/ "እግዚአብሔር ነገሠ፤ ምድር ደስ ይበልሽ" ተብሎ እንደተጻፈ ፍጥረት ሁሉ በደስታና ሐሴት ተሞልቷል። ሞት በነገሠበት ዘመን ግን “በባቢሎን ወንዞች አጠገብ በዚያ ተቀመጥን፤ ጽዮንንም ባሰብናት ጊዜ አለቀስን›› /መዝ 117÷1/ በምርኮው ጽናት የተነሣ አዘንን። አሁን ግን ያ የሞትና የዲያብሎስ አገዛዝ ተወግዷል። ነገር ሁሉ ፍጹም በደስታና በሐሴት ተሞልቷል። እግዚአብሔርም በይሁዳ ብቻ ሳይሆን በዓለሙ ሁሉ ሥራው ታወቀ። “ድምፃቸውም ወደ ምደር ሁሉ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ›› እንደተባለ /መዝ 137÷1፤ 19÷4/ ።

## አማናዊው ፋሲካ ኢየሱስ ክርስቶስ

ወዳጆቼ! እርሱን ተከትሎ የመጣው ነገር የታወቀ ነው፤ ይህ በቆሸሸ እራፊ ሳይሆን አእምሮአችንን ባለበሰ ንጹሕ ጨርቅ ወደ ተጌጠ በዓል ቀረብን። በዚህም ክርስቶስን እንለብሰው ዘንድ እንሻለን። በዓሉን ከእርሱ ጋር እናከብር ዘንድ። እንግዲህ መልካም ሥራን ትሩፋትን በወደድን ጊዜ፣ ክፋትን በጠላን ጊዜ፤ ራሳችንን መግዛት በለመድን ጊዜ፣ ፍትወተ ሥጋን በገታን ጊዜ፣ በበደል ፊት ጽድቅን በመረጥን ጊዜ፣ ኑሮዬ ይበቃኛል ማለትን በተማርን ጊዜ፣ የመንፈስን ጥንካሬ ገንዘብ ባደረግን ጊዜ፣ ድሆችን ባልረሳንና በራችን ያለ አድልዎ ለሁሉ በተከፈተ ጊዜ፣ ትዕቢትን በጠላን ትሑት ሰብእና ያላቸውንም በደገፍን ጊዜ እርሱን ክርስቶስን ለብሰነዋል።

የቀደመቺዪቱ እስራኤል ጠላቶቿ ላይ ባገኘችው ድል ወደ





በዓል ቀረበች፤ እነዚያ በዓላት ግን ጥላና ምሳሌ ነበሩ። ነገር ግን ወዳጆቼ እኛ የጥላውን አካል /ፍፃሜ/ ይዘናል። ምሳሌዎቹም አማናዊ ሆኑ /ተፈጸሙ/። ስለዚህ ከእንግዲህ በዓላችን ምሳሌ እንዲሆን አናስብም። እንደ አይሁድ እዚህ ዝቅ ዝቅ ካለች ከታችኛዪቱ ኢየሩሳሌም የፋሲካን በግ ልንሠዋ አንሔድም፤ ነገር ግን ሐዋርያት እንዳዘዙን ከእነዚህ ምሳሌያት ባሻገር እንሒድ፤ አዲሱንም ዝማሬ /ቅኔ/ እናቅርብ።

ይህን በመገንዘብ ከእውነት ጋር አንድ ላይ ሲሰባሰቡ መድኃኒታችንን “ፋሲካን ትበላ ዘንድ ወዴት ልናሰናዳልህ ትወዳለህ?›› ለማለት ይቀርባሉ። /ማቴ 26÷17/ ነገር ግን እኒህ ነገሮች በታችኛዪቱ ኢየሩሳሌም ብቻ የሚደረጉ አልሆኑም። በዓሉ በዚያ ብቻ የሚከበር አልሆነም፤ እግዚአብሔር በወደደበት በፈቀደበት ሥፍራ ሁሉ እንጂ። አሁን በሁሉም ሥፍራ እንዲሆን ፈቅዷል። ምክንያቱም “በየሥፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ›› ተብሏልና /ሚል 1÷2/

በታሪክም እንደተመዘገበው በዓለ ፋሲካ በኢየሩሳሌም የተወሰነና በሌላ በየትም ሥፍራ የማይከበር እንደነበር ቢታወቅም አሁን ግን በዚያን ጊዜ ይሆኑ የነበሩት ነገሮች ፍፃሜ አግኝተዋል፤ በጥላው ዘመን የነበሩት አልፈዋል። የወንጌልም ቃል በሁሉም ሥፍራ ደርሷል፤ በእርግጥም ወንጌልን በሁሉም ሥፍራ ያደረሱ ሐዋርያት “ፋሲካን ትበላ ዘንድ ወዴት ልናሰናዳልህ ትወዳለህ?›› ብለው ጌታን ጠይቀውታል። /ማቴ 26÷17/። መድኀኒታችንም ምሳሌውን ወደ አማናዊ /መንፈሳዊ/ ለውጦታልና የፋሲካን በግ ሥጋ ከእንግዲህ እንደማይበሉ ቃል ገባላቸው። በቃሉም እንዲህ አለ “እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው፣...ደሜ ይህ ነው›› /ማቴ 26÷26-28/ ስለዚህ

ወዳጆቼ በእነዚህ ነገሮች የምናድግ /የምንጽናና/ ስለሆነ ታላቁን የፋሲካ በዓል እናክብር።

## ስንብት

እንግዲህ የሚመጣውንም ዓለም እያሰብን ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም አብረን እንሆን ዘንድ፤ በክርስቶስም እግዚአብሔርን በምልዓት እናመሰግን ዘንድ ፋሲካን በጊዜው እናክብር፤ ያንንም ተከትሎ የሚመጣውን በዓለ ሃምሳንም እናክብር፤ እርስ በእርሳችሁ በተቀደሰ ሰላምታ ሰላም ተባባሉ። ከእኔ ጋር ያሉት ሁሉም ወንድ ሞች ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። ይህንን ደብዳቤ ከቤተመንግሥት በዚያ ባለ እግዚአብሔርን በሚፈራ አንድ መኮንን አማካኝነት ተላከ። እኔ በንጉሠ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ተጠርቼ በቤተመንግሥት እገኝለ ሁና። ነገር ግን በዚያ ያሉ የሚሊጦስ ተከታዮች በቅናት ይመላለሱና በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ጥፋታችንን ይሻሉ። ይሁን እንጂ ያፍራሉ።።





# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አምስት

## በዓላችን ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ስለመሆኑ

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ! ከበዓላት ወደ በዓላት፣ ከጸሎት ወደ ጸሎት ከትጋት ወደ ትጋት እንራመዳለን፤ ከጾም ወደ ጾም፣ ከቅዱስ ቀን ወደ ቅዱስ ቀን እንገሰግሳለን። የአዲስ ዘመን ጅማሬን ወደ እኛ የሚያቀርበው ጌታችን የተሠዋበት የፋሲካም የብሥራት ጊዜ ደረሰ። እርሱን እንደ ሕይወት ማዕድ /ምግብ/ እንበላለን፤ ዘወትር እርሱን ከወርቀ ደሙ ምንጭ በመጠማት ነፍሶቻችን ሐሴት ያደርጋሉ። ለተጠሙት የተዘጋጀ ነውና ዘወትር በጥብቅ እንሻዋለን። እርሱን ለተጠሙት ከፍቅሩ ርኅራኄ የሚመነጭ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ›› ብሎ በበዓሉ ቀን የተናገረው የመድኀኒታችን ቃል አለ /ዮሐ 7፥37/። እንግዲህ ማንም ቢሆን ወደ እርሱ በቀረበ ጊዜ ይህን ብቻ ሳይሆን ጥማቱን ይፈውሳል / ፍጹም ያረካል/።

ማንም በፍቅር የሚፈልገው በሆነ ጊዜ ወደ ጌታ መድረስ የሚያስችል ነጻነት አለ። የበዓሉም ግርማ ለአንድ ጊዜ የተወሰነ አይደለም፤ ያማረ ብርሃናዊነቱ አይደበዝዝም። በእውነት እርሱን ለሚፈልጉት ዘወትር ሊያበራ የቀረበ ነው። በመዝሙር "ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሔደ፤ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፤ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ፤ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፤ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል›› ተብሎ እንደተናገረ ልባ ቸው የበራላቸው የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል ቀንና ሌሊት ለሚያ ነቡ ለእነዚያ በዚያ ውስጥ የላቀ ትሩፋት ይኖራቸዋል። ደስታቸው

በጌታ ሕግና ትእዛዝ ነው። ሕጉንም ቀንና ሌሊት ያስባሉ። /መዝ 1፥1-2/ ለእነርሱ የሚያበራላቸው ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ወይም የከዋክብት ስብስብ አይደለም፤ ከእግዚአብሔር ታላቅ ብርሃን የተነሣ ያንጸባርቃሉ እንጂ።

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ! አስቀድሞም በዓልን የሠራልን በየዓመቱ የሚከበርበትን ጊዜ የሚያበሥረው እግዚአብሔር ነው። እርሱ ሁለቱንም አደረገልን፤ የሚወደው ልጁን ሠዋ፤ ለበዓሉም ምክንያትን አመጣልን። እያንዳንዱም ዓመት ለዚህ ነገር ምስክር ይሆን ዘንድ በየወቅቱ በዓሉ ይታወጃልና። ይህ ደግሞ መስቀሉን ተሸክመን በዓለሙ ውስጥ አልፈን ከእኛ በፊት ወደ ነበረችው መንግሥቱ ይመራናል። በዚያም እግዚአብሔር የድኅነታችንን ደስታ ያዘጋጃል። ይህን ወደ መሰለ ጉባኤ ይደምረናል፤ በሁሉም ቦታ በመንፈስ አንድ መሆንን ለሁላችን ይሰጣል። ከበዓሉ የተነሣ በጽኑ ጸሎትና በጽኑ ጸጋ ላይ ያሠለጥነናል። ይህ የእርሱ የርኅራኄ ፍቅር የሚደነቅበት ነውና ርቀው የነበሩትን፣ በአካል /በሥጋ/ ተለይተው የነበሩትን በመንፈስ አንድ ይሆኑ ዘንድ በአንድ ሥፍራ ሰበሰባቸው።

## ከእግዚአብሔር የተሰጠ በዓል ስለመሆኑ

ወዳጆቼ! እንግዲህ ይህ በዓላችን ከእርሱ የተሰጠን ጸጋ መሆኑን አታውቁምን? ለዚህ ቸር ጌታችን የምንመልሰለት ሊኖር አይገባምን? አውቃለሁ፤ ለእግዚብሔር የምንመልስለት የምንከፈልው የበቃ ነገር እንደሌለን እርግጥ ነው። ነገር ግን ይህን ታላቅ ስጦታውን የማናውቅ የማንረዳ ከሆነ ለእኛ በደል ነው። የምንሰጠው እንደሌለን፣ የማይቻለንም ደካሞች መሆናችንን ተፈጥሮ /ባህርያችን/ ራሱ ይናገራል፤ ነገር ግን የማናመሰግን ብንሆን ደግሞ የራሳችን ፈቃድ ይገስጸናል።





ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ስጦታ /ጸጋ/ ታላቅነት ሲያደንቅ "ለዚህም ነገር የሚበቃ ማን ነው›› /2ቆሮ 2፥17/ ብሏል። በመድኃኒታችን በንጹሕ ደሙ ዓለሙን ነጻ አውጥቷልና፤ ሞትና መቃብርን በሞቱ አዋርዷልና። ሊመላለሱበት ለፈቀዱ ወደ ሰማይ በሮች የሚያደርሰውን መንገድ ያለዕንቅፋት እንዲሆን አቅንቷልና። ስለዚህም ይህንን ውለታ መክፈል የማይቻለው ደካማ መሆኑን የተረዳና ስለተሰጠው ታላቅ ጸጋ የተገነዘበ ታላቁ ክቡር ሰው ዳዊት "ስላደረገልኝ ሁሉ ለእግዚአብሔር ምንን እመልሳለሁ›› አለ /መዝ 116፥12/። በሞት ፈንታ ሕይወትን፣ በባርነት ምትክ ነጻነትን በመቃብር /ሲዖል/ ፈንታም መንግሥተ ሰማያትን ተቀብሏልና። አስቀድሞ ሞት ከአዳም እስከ ሙሴ ገዝቷልና፣ አሁን ግን የመለኮት የቃሉ ድምፅ "ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ" ይላል።

ስለዚህ ይህን የተረዱ ቅዱሳን "እግዚአብሔር የረዳኝ ባይሆን ነፍሴ ለጥቂት ጊዜ በሲኦል ባደረች ነበር›› አሉ። /መዝ 94፥17፤ ሮሜ 5፥14፤ ሉቃ 23፥43/ ውለታን ለመመለስ የማይችል አቅም የለሽ ቢሆንም ጸጋውን ግን ያውቃል፣ ያደንቃል፣ ያከብራል፤ በፍፃሜውም "የመድኀኒትን ጽዋ እቀበላለሁ፤ የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ፤ በሕዝቡም ሁሉ ፊት ስእለቴን ለእግዚአብሔር እፈፅማለሁ፤ የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው›› አለ። /መዝ 116፥13፣15/።

ስለእኛ ስለሚቀበላት ጽዋም ጌታ አለ "እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ ትችላላችሁን?›› ደቀመዛሙርቱም ዝም ባሉ ባዘኑም ጊዜ ጌታችን ዳግመኛ እንዲህ አለ "ጽዋዬንስ ትጠጣላችሁ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው›› /ማቴ 20፥22፣23/ ስለዚህ ወዳጆቼ ውለታውን መክፈል የማይቻለን ቢሆንም

የተሰጠንን ጸጋ ታላቅነት ግን እንረዳ። የሚቻለንን ግን እናድርግ፤ ባሕርያችን ውለታ ለመመለስ የማይቻለው ቢሆንም እርሱን በማክበር ውስጥ ተወስነን ምስጋናን እናቅርብለት። ከማክበርም በላቀ ለሰው ልጆች ባለው ፍቅር ጸጋውን ያደለንን እግዚአብሔርን በማወቅ ከእርሱ ጋር መኖር እንዴት ይቻለናል የሚለውን እናስብ። ስለዚህ ለሕጉ በመታዘዝ ትእዛዛቱንም ልንጠብቅ ይገባል፤ ጌታ የሚያመሰግኑትን ይወዳልና። እኛ እንደ ቅዱሳን ራሳችንን ለእግዚአብሔር በሰጠን ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል›› ባለ ጊዜ እንዳደረገው /ገላ 2÷20/ እኛ ሁላችን ለራሳችን ሳይሆን ስለእኛ ለሞተው ለጌታችን ራሳችንን ሕያዋን እናድርግ።

## ለውለታው ምን እንመልስለታለን

ወንድሞቼ! ሕይወታችን ራሳችንንና የሥጋ የሆኑትን ነገሮች በመካድ ውስጥ ነው፤ የመድኀኒታችን በሆኑት በእነዚያ የተቀደሱ ነገሮች ውስጥ በጽናት መቀጠል ነው። ስለዚህ ወቅቱ እነዚህን ቃላት ለመናገር ብቻ ሳይሆን ቅዱሳንን መስለን እንድንገኝ ይጠራናል። ነገር ግን ስለ እኛ የሞተውን እርሱን ባወቅን ጊዜ እነርሱን መስለን እንገኛለን፤ እንዲሁም ለራሳችን የማንኖር ነገር ግን ክርስቶስ በእኛ የሚኖር እስከሆነ ድረስ ነው።

ምንም እንኳ ለእርሱ ውለታ ስንመልስ የምንሰጠው የእኛ የምንለው ነገር ባይኖርም እነዚያን ቀድመን ከእርሱ የተቀበልናቸው የእርሱን ልዩ ልዩ ጸጋዎች ከእኛ ይፈልግብናል። እርሱም "መብሌን ለእኔ ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን በእሳት የተደረገውን ቁርባኔን መባዬን በየጊዜው ታቀርቡልኝ ዘንድ ጠብቁ›› ባለን ጊዜ ራሱ ምስክር ይሆን ብናል። /ዘኁ 28÷2/። እነዚያ የተሰጡን ጸጋዎች ሁሉ የራሳችን





አይደሉም። የሰጪው የእግዚአብሔር ጸጋዎች ናቸው። ስለዚህ ሁሉንም መልካም ነገር ሁሉ ለጌታ እንስጥ። እንዲሁም ከእነዚያ እርሱ ለእኛ ከቀደሳቸው ነገሮች ጋር በዓሉን በማክበር ለእርሱ እንጠብቅ።

በእርሱ እንደ ታዘዘው በቅዱሱ ጾም ውስጥ ጸንተን እንገኝ። በእርሱም የእግዚአብሔርን መንገድ እናገኛለን። እንደ ሰነፎች፣ እንደ አላዋቂ አይሁድ፣ እንደ መናፍቃን፣ መለያየትን እንደሚወዱ እንደዘመናችን ሰዎች አንሁን። ሰነፎች የበዓል ክብሩ በመብል መጠጥ ብዛት እንደሆነ ያስባሉ፤ አይሁድ ደግሞ በጥላና በምሳሌው በመሳት እስከ አሁንም እንዲሁ የሆነ ይመስላቸዋል፤ መለያየትን የሚወዱ ደግሞ ይህን በሌላ በተለየ ሥፍራ በከንቱ ሐሳብ ውስጥ ሆነው ይጠብቁታል። ወንድሞቼ እንግዲህ ከሰነፎች የተሻልን እንሁን፤ በዓሉን በነፍሳችን ቅድስና፣ በሰውነታችን ንጽሕና እናክብር። አይሁድም የሚያስቡትን ምሳሌና ጥላ እንደ እነርሱ ሆነን በመቀበል ሳይሆን በእውነት ብርሃን ድንቅ ሆኖ የተገለጠ የጽድቅ ፀሐይንም ትኩር ብለን በመመልከት ልንበልጣቸው ይገባል። መለየትን እንደሚወዱ ወገኖች ደግሞ የክርስቶስን ልብስ በመቅደድ አይደለም። በአንድ ቤት በአንዲት ኩላዊት ቤተክርስቲያን ውስጥ እንሁን። የጌታን ፋሲካም እንብላ። እኛን በቅዱስ ሕጉ በማሠልጠን ወደ መልካም ሥራ ይመራናል።

## ፋሲካ ከኃጢአት የመጠበቅ በዓል ስለመሆኑ

በእርግጥም ፋሲካ ከኃጢአት መታቀብ /መቆጠብ/ መልካም ነገርንም መፈጸምን መልመድ ነውና ከሞትም ወደ ሕይወት መሻገር ነውና። ይህንን ደግሞ ከቀደሙ ምሳሌያት እንማራለን። እነርሱ በትኩረት ከግብጽ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሻገር ደከሙ፤ አሁን ግን ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገርን። ስለዚህ ከፈርዖን ወደ ሙሴ ታደምን። ከዲያብሎስ ወጥተን ለክርስቶስ ለመድኃኒታችን ታደምን። ታዲያ

በዚያም ዘመን እስራኤል የድኅነት በዓል በየዓመቱ እንደነበራቸው እኛም አሁን የድኅነታችን መታሰቢያ የሆነ በዓል አለን፡፡ በዚህም የሥጋ ሞታችንን እያሰብን በመንፈስ ሕይወት መኖር እንችላለን፤ ያንንም ሕይወት እንጠባበቃለን፡፡ እንደ ሐዘንተኞች አይደለም፤ ሙሽራውን ቀድመው ገብተው እንደሚጠባበቁ ጌታን የምንጠብቅ ሆነን፤ እርስ በእርሳችንም ለማሸነፍ እንደሚሽቀዳደሙ እንወዳ ደራለን፡፡ በሞት ላይ የተገኘውን ድል ለማብሰር እንፈጥናለን፡፡

ስለዚህ ወዳጆቼ በቃሉ እንደታዘዝነው በጊዜያቱ ሁሉ ፍጹም ራሳችንን ልንገዛ ይገባል፤ የእግዚአብሔንም ድንቅ ሥራ ሳንረሳ ከመልካም ሥራ ሳንለይ እንኑር፡፡ የሐዋርያት ሐዋርያዊ ድምፅም "ከሙታን የተነሣውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ›› በማለት እንደሚ ያነሣሣን እርሱን ለማሰብ የተወሰነ ወቅት አንሰጥም፤ ዘወትር በሐሳባችን ሊኖር ይገባልና /2ጢሞ 2፥8/፡፡ ነገር ግን በብዙዎች ስንፍና ምክንያት ከዕለት ወደ ዕለት እንዘገያለን፡፡ እንግዲህ በእነዚህ ቀኖች እንጀምር፡፡ እንግዲህ በቀሪዎቹ ቀናት በመልካም የጽድቅ ሥራዎች ውስጥ እንጠበቅ፤ በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ለውድ ቀት ተዳርገንም ቢሆን ንስሐ መግባት ግዴታችን ነው፡፡ ማንም ቢሆን ከበደል የነጻ አይደለምና፡፡ ምንም እንኳ መንገዱ የቀና ቢሆን ኢዮብ እንዳለው ምድር ላይ ለአንድ ሰዓት ቢቆይ እንኳ ሰው ቅጽርን ይጥሳልና፡፡ ነገር ግን "ከርኩስ ነገር ንጹሕን ሊያወጣ ማን ይችላል አንድ እንኳ የሚችል የለም›› /ኢዮ 14፥14/፡፡

ፋሲካን ሳይገባን እንዳንበላ እንጸልይ፡፡ ለጥፋት እንዳንሰጥ፡፡ ነገር ግን በዓሉን በንጽሕና ለሚያከብሩ ፋሲካ ሰማያዊ ማዕድ ነው፡፡ ነገር ግን በንቀት ለሚመለከቱት እና በስላቅ ለሚያይ አደጋና ተግሣጽ ነው፡፡ "ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ





ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት›› ተብሎ እንደተጻፈ/1ቆሮ 11፥27/፡፡

ስለዚህ እንዲሁ ብቻ የበዓላትን ሥርዓት አንፈጽም፤ ወደ እግዚአብሔር በግ ለመቅረብ እንዘጋጅ፤ ወደ ሰማያዊው መዓድ ለመድረስ፡፡ እጆቻችንን እናጽዳ፣ ሰውነታችንን እናንጻ፤ አእምሮአችንንም ሁሉ ከአታላይነት፣ ከቅናት፣ እና ከፍትወተ ሥጋ እንጠብቅ፤ ራሳችንን በጌታችን እና በሃይማኖት ትምህርቱ ሙሉ በሙሉ እናስይዝ፤ ቃሉን እንሳተፍ፣ እኛ ሁላችን አንድ ሆነን ንጹሕ እንሆን ዘንድ፡፡

ስንብት

በጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛ የመንግሥቱ ወራሾች እንሆናለንና በእርሱ ለአብ ክብር ዕዘዝ ለዘላለም ይሁን አሜን፡፡ ከእኔ ጋር ያሉ ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል፡፡ እርስ በእርሳችሁ በተቀደሰ ሰላምታ ሰላም ተባባሉ፡፡

# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ስድስት

## እግዚአብሔር ወደ በዓሉ ይጣራል

ወዳጆቼ፣ እግዚአብሔር የታላቁን በዓል ጊዜ ወደ እኛ አምጥቷል። በፍቅሩና በርኅራኄው ብዛት ለእርሱ /ለበዓሉ/ ለመሰብሰብ ደርሰናል። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ እንደጠራ አሁንም እንኳን በዚህ ጊዜ ወደ በዓሉ ይጠራናል። በነቢዩ ሙሴ አማካኝነት "የአቢብን ወር ጠብቅ፤ የአምላክህንም የእግዚአብሔርን ፋሲካ አድርግበት" /ዘዳ. 16፥1/ እንዲሁም ደግሞ በነቢዩ "ዓመት በዓሎችህን አድርግ" ስእለቶችህን ክፈል" እንዳለ። /ናሆ. 1፥15/ እንግዲህ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ በዓሉን ከወደደ፣ ወደ እርሱም ከጠራን፣ ወንድሞቼ ሆይ መዘግየት ወይም በግዴለሽነት ማየት የሚገባ ነገር አይደለም። ነገር ግን በንቃት እና በቅንአት ወደ እርሱ ልንቀርብ ይገባል። እነሆ በዚህ ደስተኞች መሆን እንደጀመርን የሰማያዊውን በዓል ቅንነት /እውነተኛ መገለጥ/ እንቀበላለን። በዚህ ሳለን በዓሉን በትጋት የምናከብር ከሆነ በሰማይ ያለውን ፍጹም ደስታ እንደምንቀበል አንጠራጠርም፤ ጌታም እንዲህ እንዳለ "ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህን ፋሲካ ልበላ እጅግ እመኝ ነበር እላችኋለሁና፤ በእግዚአብሔር መንግሥት እስኪፈጸም ድረስ ወደ ፊት ከዚህ አልበላም።" /ሉቃ. 22፥15/

## ስለበዓሉ አከባበር

እንግዲህ የበዓሉን ምክንያት ካስተዋልን፣ ሰጪውንም ካመሰገንን አሁን ፋሲካን በልተናል። ቅዱስ ጳውሎስ "በቅንነትና በእውነት የቂጣ በዓልን እናድርግ እንጂ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ እርሾም አይደለም።" እንዳለ /1ቆሮ. 5፥5/ በሰጠን ጸጋ መሠረት የሚገባውን





እናደርጋለን። ጌታ በመቃብር በቆየባቸው በእነዚያ ቀናት የሞትን ሥራ ልንሠራ አይገባም። ሕይወቱን ሰጥቶናልና ራሳችንን ከዲያብሎስ ወጥመዶች ልንጠብቅ ይገባል።

ምን ያህል ይደንቅ! ቃል ሥጋ ሆነ። እንግዲህ በሥጋ ፈቃድ ልንኖር አይገባም። ነገር ግን መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን በመንፈስ ልናመልከው ይገባል። እንዲህ በደግ መንገድ የማያይ ቀኖቹን በማይገባ መንገድ ያከብራል፤ በዓሉንም አይጠብቅም። ሌላው ደግሞ ማመስገን እንደማይወድ ሰው በዚህ ጸጋ ውስጥ ስሕተትን ይፈልጋል። ቀኖቹንም ከልክ በላይ /ለራሱ ፍትወት/ ያከብራል። ነገር ግን በእነዚያ ቀናት ያዳነውን ጌታ ምሕረትን አይለምንም። በዓላቱን የጠበቀ ይምሰለው እንጂ ወደ በዓሉ አልደረሰም። እንዲህ ያለው ሰው በየትኛውም መንገድ ቢሆን "ቀንና ወርን ዘመንንም ዓመትንም በጥንቃቄ ትጠብቃላችሁ፤ ምናልባት በከንቱ ለእናንተ ደክሜያለሁ ብዬ እፈራለሁ።" ተብሎ የተነገረውን ሐዋርያዊ ቃል ሊሰማ የሚገባው ነው። /ገላ. 4፥11/ በዓልነቱ ስለእኛ መከራን ስለተቀበለ ስለጌታ እንጂ ስለ ቀኖቹ አይደለምና፤ እርሱን እናከብራለን፤ "ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና" /1ቆሮ. 5፥7/

## ፋሲካው የእግዚአብሔር ስለመሆኑ

ሙሴ እንኳን እስራኤልን ባስተማረ ጊዜ በዓሉን ስጌታ እንጂ ለቀኖቹ እንዳያስቡ "እርሱ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው" በማለት ተናግሯል። /ዘዳ. 12፥2/ አይሁድ ፋሲካን ማክበራቸውን ባሰቡ ጊዜ ጌታን ገድለውታልና፤ በዓሉ ለእነሱ ጥቅም የለውም በራሳቸው ምስክርነት /መሐላ/ መሠረት የጌታን ስም አይሹክሙምና /አይቀበሉም/። ስለዚህ ፋሲካቸው የጌታ አይደለም፤ የአይሁድ ፋሲካ እንጂ። ወንድሞች ሆይ! ስለዚህ ፋሲካው "የአይሁድ ፋሲካ" ተብሎ በአይሁድ ስም

ተጠራ። ምክንያቱም የፋሲካውን ጌታ ክደዋልና። በዚህ መሠረት ጌታ ከእነርሱ ትምህርት /እምነት/ ፊቱን መለሰ፤ "መባቻችሁንና በዓላቶቻችሁን ነፍሴ ጠልታለች" በማለት እንደተናገረ /ኢሳ. 1፥14/።

**በዓሉ የምስጋና በዓል ስለመሆኑ**

እንግዲህ አሁን ፋሲካን በእንግዲህ ያለው መንገድ የሚጠብቁትን ጌታ በእነዚያ በነጹ ለምጻሞች እንዳደረገው በድጋሚ እነዚህንም ይገሥጻቸዋል፤ ለምስጋና የተመለሰውን ያንን ባመሰነገ ጊዜ በእነዚያ ባላመሰገኑት ተቆጥቶ ነበር። ምክንያቱም ፈውስ ሰጪውን አላመሰገኑምና፤ ከፈወሳቸው ከእሱ ይልቅ ከለምጽ ስለመዳን ብቻ አስበዋልና። "ከእነርሱም አንዱ እንደተፈወሰ ባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ፤ እያመሰገነውም በእግሩ ፊት በግንባሩ ወደቀ። እርሱም ሳምራዊ ነበር። ኢየሱስም መልሶ ዐሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ? ከዚህ ከልዩ ወገን በቀር እግዚአብሔርን ሊያከብሩ የተመለሱ አልተገኙም አለ።" /ሉቃ. 1፥15/ ስለዚህም ከሌሎቹ ይልቅ ለእርሱ ብዙ ተደረገለት። ከለምጽ ስለመን በጸቱም ሁኔታ ከጌታ ቃል ሰማ "ተነሥና ሒድ፤ እምነትህ አድኖሃል" ተባለ። የሚያመሰግኑ እና የሚያከብሩ ለተቀበሉት ጥቅም /ቸርነት/ የረዳቸውን በሚያመሰግኑበት ነገር ውስጥ እነርሱ የዝምድና ስሜት አላቸው።

ሐዋርያውም ሰዎችን ሁሉ "በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" በማለት ያሳስባል። /1ቆሮ. 6፥20/ ነቢዩም እንዲህ በማለት ያዛል "ለእግዚአብሔር ክብርን ስጡ" /ኢሳ. 12፥12/።

**ጌታችን ስለእኛ መከራ ስለመቀበሉ**

በእነዚያ ጊዜያት /በሰሙነ ሕማማቱ ቀያፋ በመድኃኒታችን ላይ ምስክሮችን ቢሰበስብም /ማቴ. 26፥25/፤ በአይሁድ ፊት ጌታ





እንደከንቱ ሆኖ ተቆጥሮ የነበረ ቢሆንም፣ በጲላጦስም የተፈረደበት ቢሆን፣ እጅግ ከፍ ከፍ ያለው፣ ኃያልም የነበረው ወደ እርሱ የመጣው "አከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ" በማለት የተናገረው የአብ ድምፅ ነበር። /ዮሐ. 12፥28/ ስለእኛ መከራን የተቀበለባቸው እነዚያ ነገሮች ሁሉ አልፈዋል፣ እንደ አዳኝነቱ የእርሱ የሆኑት ነገሮች ሁሉ ግን ለዘለዓለም ይኖራሉ።

እነዚህን /የማዳኑን ነገር/ በማሰባችን ውስጥ ግን በሥጋ አንያዝ /ሥጋን በመብላት አንጠመድ/ ጌታን እናክብረው እንጂ። ስለእኛ ሞትን ለተቀበለ ለእርሱ እንደ እብድ እንሁንለት። ቅዱስ ጳውሎስ "እብዶች ብንሆን ለእግዚአብሔር ነው፤ ባለአእምሮዎች ብንሆን ለእናንተ ነው። ይህን ስለቆረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል። አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ እንዲያስ ሁሉ ሞቱ፤ በሕይወት ያሉት ስለ እርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ።" እንዳለ። /2ቆሮ. 5፥13-15/ ከእንግዲህ ለራሳችን ልንኖር አይገባም፣ ለጌታ አገልጋይ እንደመሆናችን እንጂ፤ ጸጋውን በከንቱ ልንቀበል አይገባም። የጌታችን ዕለተ ሞት ቢሆን እንኳን ጊዜው የተወደደ ሰዓት፤ የማዳንም ቀን እንደመጣልን አድርገን እናክብረው።

ሙስና መቃብር የሌለበት የእግዚአብሔር ቃል ስለእኛ ከሰማይ ወረደ። ስለሁላችን መዳንም ሙስና መቃብር ያለበትን ሥጋ ለበሰ። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ በታላቅ መተማመን እንዲህ አለ "ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ፤ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።" /1ቆሮ. 15፥53/

ስለፈሰሰ ደሙ በከንቱ የተሳተፉትን ሁሉ ግን "ወደ ጥፋት ብወርድ በደሜ ምን ጥቅም አለ?" በማለት አንድ ጊዜ በአንድ ቦታ ፍጹም ወቅሷል። /መዝ. 30፥9/ በእግዚአብሔር ቃል /በአማኑኤል/ ሥጋ

ራሳቸውን ደስ አላሰኙምና። ይህ ማለት ግን የጌታ መውረድ ያለጥቅም ነበር ማለት አይደለም፤ እርሱ በደሙ ዓለሙን ሁሉ ገዝቷልና። ነገር ግን እርሱ መከራን ከተቀበለልን በኂላ ኃጥአን ግን እርሱ /በሰጠን ጸጋ/ ከማትረፍ ይልቅ እርሱን በመተው መከራን ይመርጣሉ። ጌታችን ግን መዳናችንን እንደ ደስታና ልዩ ትርፍ ያየዋል። በአንጻሩ ጥፋታችንን ደግሞ እንደ ኪሳራ /ማጣት/ ያየዋል።

## በጸጋ ስለማትረፍ

በወንጌል ውስጥም የተሰጣቸውን ጸጋ በእጥፍ የጨመሩትን የተሰጣቸውን አምስቱን መክሊት ዐሥር፣ ሁለቱንም አራት ያደረጉትን ሁለቱንም እንዳመሰገነ እንደ እነዚያ እንዳተረፉት ያላቸውን ጸጋ በመልካም የለወጡትንም አመስግኗል። ነገር ግን መክሊቱን የቀበረ ውን ሌላውን ግን ለጥፋት ተወው እንዲህም አለው። "አንተ ክፉና ሐኬተኛ ባሪያ ካልዘራሁበት እንዳጭድ፣ ካልበተንሁበትም እንድሰበ ስብ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፤ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር፤ ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት ዐሥር መክሊትም ላለው ስጡት፤ ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና፤ ይበዛለትማል። ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳን ይወሰድበታል። የማይጠቅመውንም ባሪያ በውጪ ወዳለው ጨለማ አውጡት። በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።" / ማቴ. 25፥26/

የተቀበልነውን ጸጋ ፍሬ የማናፈራበት እንዲሆን እርሱ ፈቃዱ አይደለም። ቅዱስ ጳውሎስ "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት እምነት፣ የዋሃት፣ ራስን መግዛት ነው" በማለት እንደነገረን። የሰጠንን የራሱን ፍሬዎች በብዙ ድካም ሠርተን ለራሱ እንድናቀርብ ይፈልግብናል። /ገላ. 5፥22/





እርሱ በወይን አትክልቱ ባለቤት ፍሬውን ሊቀበሉ ወደ ገበሬዎቹ እንደተላኩ ባሮች ነው። /ማቴ. 21፥33/ ሰዎች ሁሉ የሥራቸውን ውጤት እንዲያስረክቡ ያሳስባልና። እስራኤል ግን ናቁ፤ አላስረከቡም ነበርና። ያም ብቻ አይደለም፤ መልእክተኞቹን ገደሉ፤ በወይን አትክልት ቦታው ባለቤት በጌታ ፊት አለማፈራቸው ብቻ አልነበረም፤ እርሱም በእነርሱ ተገደለ እንጂ። እውነት እላችኋለሁ ወደ እነርሱ በመጣ ጊዜ፣ ፍሬም ባጣባቸው ጊዜ "ለዘላለሙ ፍሬ አይገኝብሽ" በማለት በበለሷ ውስጥ ረገማቸው /ማቴ. 21፥19/።

በለሲቱም ያንጊዜውኑ ደረቀች፣ ፍሬቢስም ሆነች። ደቀ መዛሙርቱም ይህን አይተው ተደነቁ። ያን ጊዜም በነቢዩ "ከእነርሱም የእልልታን ድምፅና የደስታን ድምፅ የወንድ ሙሽራን ድምፅና የሴት ሙሽራን ድምፅ፣ የወፍጮንም ድምፅ፣ የመብራትንም ብርሃን አስቀራለሁ። ይህቺም ምድር ሁሉ ባድማና መደነቂያ ትሆናለች" ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ።/ኤር. 25፥10/ ሁሉም የሕግ አገልግሎት ከእነርሱ ተወስዷልና፤ ከዚያም ለዘለዓለም ያለ በዓል ቀሩ። የሚያከብሩት ፋሲካን አይደለም፤ እንዴትስ ይችላሉ? ዘላቂ /የጸና/ ቦታ የላቸውም፤ በየቦታውም ይንከራተታሉ። የፋሲካውን በግ አስቀድመው መሠዋት ባለመቻላቸው ምክንያት ቂጣውን ሲበሉ እንዲያደርጉ እንደታዘዘው ከሕጉ በተቃራኒ ያልቦካ ቂጣ ይበላሉ። በየቦታው ሕግን ይተላለፋሉ። የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚፈላለ ጋቸው በራሳቸው ሲገልጹ ከደስታ ይልቅ የሐዘን ቀናትን ያከብራሉ። እነሆ በእነርሱ ላይ ለሆነው ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ የጌታ መገደል ነበር፤ አንድያ ልጁን አላከበሩም ነበርና።

በአሁን ዘመንም ያሉ መናፍቃንና ዕውቀት ያጡ ከፋፋዮች በጌታ ላይ እንዲሁ ናቸው፤ አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል እንደገደሉ

እንደ አይሁድ ሲገድለው ሌላው ደግሞ ልብሱን ይቀዳል። እነርሱም ደግሞ ከበዓሉ የተሰደዱ ናቸው። ምክንያቱም ከፈቃደ እግዚአ ብሔር፣ ከዕውቀት ውጪ ሆነው ይኖራሉ። በወንበዴው በበርባን ጉዳይ ላይ በጌታ ፈንታ እርሱን የፈለጉበት /እንዲፈታ የጠየቁበት/ በአይሁድ የታየውን ተግባር ይመስላል። ስለዚህም ጌታ በበለሷ አምሳል ረገማቸው። አሁንም ገና በፍቅርና ርኅራኄ ሥራቸው ተነቅሎ ፍጹም እንዳይጠፋ አቆይቷቸዋል። "ለዘለዓለም ማንም ፍሬ አያግኝብሽ" አላት እንጂ ስሯ እንዲጠፋ በለሷን አልረገማትምና። ይህን ባደረገ ጊዜ ትደርቅ ዘንድ ጥላውን አጠፋባት፤ ስሯን ግን ጠበቀ፤ በዚያ ላይ ታቀጥል /ታቆጠቁጥ/ እንደሆነ፤ "እነዚያም ደግሞ በአለማመናቸው ጸንተው ባይኖሩ በዛፉ ውስጥ ይገባሉ" እንደተባለ። /ሮሜ. 11፥23/ እነሆ እግዚአብሔር በቸልተኝነታቸው ምክንያት በረገማቸው ጊዜ አዲስን መባቻ፣ አማናዊውን በግ እና አማናዊውንም ፋሲካ ከእነርሱ ወሰዷል።

## ክርስቲያኖች በበዓሉ መደሰት እንደሚገባቸው

ለእኛ ግን መጥቶልናል፤ በመለከትም ድምፅ ወደ በዓሉ የምንጠራበት ታላቅ ቀን መጥቷል። በምስጋናም ራሳችንን ለእግዚአ ብሔር እንለይ! እንደ ራሳችንም በዓል እናስበው! ለእኛ ሳይሆን የእኛን ሐዘን በተሸከመ፣ "ነፍሴ እስከሞት አዘነች" ባለ በጌታ እንድን ደስት እንገደዳለን። "ማቴ. 26፥38/ ለእምነታችን እንግዳ የሆኑና አረመኔዎች በዓላትን እንደራሳቸው ፈቃድ ይጠብቃሉ። ሰላምም የላቸውም። በእግዚአብሔር ላይ ክፉን ያደርጋሉና። ቅዱሳን ግን ለእርሱ ይኖራሉ። በዓላትንም ለእርሱ ያከብራሉ "በማዳንህ ደስ ይለኛል" "ነፍሴ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይላታል" /መዝ. 9፥14፣ 35፥9/ እንደተባለ። "በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ" የሚለው ትእዛዝ





ግን ለሁሉም የተሰጠ ነው። /መዝ. 33፥1/ በመሆኑም በታወቀውን በተከበረው በዓሉ መዝሙር ሊዘምሩ ይሰበሰባሉ። እነሆ ኑ ደስ ይበለን በራሳችን ሳይሆን በእግዚአብሔር።

## ስለ ይስሐቅና የእግዚአብሔር በግ

አብርሃም አባት የራሱን ቀን ሳይሆን የጌታን ቀን ሊያይ ሐሴት አድርጎ ነበር። ወደፊትም አየ /ተስፋ አደረገ/፣ "አየም፣ ደስም አለው" / መዝ. 94፥1፣ ዮሐ. 8፥56/ በእምነቱም በተፈተነ ጊዜ ቃል ኪዳን የተቀበለ አንድ ልጁን ይስሐቅን ሰጠ፤ ለመሥዋዕትም አቀረበ። ልጁን ለእግዚአብሔር በማቅረብ ውስጥም ጌታን በፍጹም አመለከ፤ ለእርሱም ተገዛ። ልጁ ይስሐቅን ከመሠዋት በተገታ ጊዜም በእርሱ ፋንታ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ባቀረበው በበጉ ውስጥ መሲህን አየው። /ዘፍ. 22፥15/

አባታችን ይስሐቅን ባይሠዋውም በእርሱ ውስጥ እምነቱ ተፈተነ፤ ነገር ግን ነቢዩ ኢሳይያስ "ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፣ በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም።" በማለት የነገረን ግን እውነተኛው መሥዋዕት ነበር። /ኢሳ. 53፥7/ እርሱ የዓለምን ኃጢአት አስወገደ። ስለዚህም ምክንያት አብርሃም እጁን በልጁ ላይ እንዳይዘረጋ ተገቶ ነበር፤ አይሁድ ይህን የይስሐቅን መሥዋዕት ምክንያት አድርገው በመውሰድ ስለጌታ ሁሉንም በተለይም መዝሙረኛው "መሥዋዕትንና ቁርባንን አልወደድህም፤ ሥጋን አዘጋጀህልኝ" በማለት የተናገረውን የነቢዩን ቃል ሳይቀበሉ እንዳይቀሩ ነበርና። / መዝ. 40፥6/ እነዚህንም ቃላት ሁሉ ስለአብርሃም ልጅ ስለይስሐቅ እንደተነገረ በተረጎሙት ነበር።

መሥዋዕቱም የአቅራቢውን የአብርሃምን እንጂ ቀጥተኛ የይስሐቅን ፈቃድ በአግባቡ ያያዘ አልነበረም። በዚያ የተፈተነው

አብርሃም ነውና። ስለዚህም እግዚአብሔር የአቅራቢውን ፈቃድ ተቀበለ። መሥዋዕት የቀረበውን ግን ከለከለ። /በፈቃዱ በተቀበለው/ በመገረፉ ቁስል ሁላችን የምንፈወስበት የመድኃኒታችን ብቻ እንጂ የይስሐቅ ሞት ዓለምን ነጻ አያወጣምና። /ኢሳ. 53፥5/ እርሱ በፈቃዱ የወደቁትን አንሥቷል፤ የታመሙትን ፈውሷል፤ የተራቡትን አጥግቧል፤ የጐደላቸውን ድሆች ሞልቶላቸዋል። እጅግ የሚደንቀው ደግሞ ሁላችንንም ከሞት አስነሥቷልና። የሞትንም ሥልጣኔ አጠፋ። እርሱ ሁላችንንም ከመከራ ከጭንቀት ወደ ዕረፍትና ወደዚህም በዓል ደስታ አመጣን፤ እስከ ሰማይም ወደሚደርስ ደስታ።

## በበዓሉ ሰማያት ሁሉ ደስ ስለመሰኘታቸው

ደስታ የተሰማን እኛም ብቻ አይደለንምና፤ በእርሱ ምክንያት ሰማያትም ከእኛ ጋር ደስ ይሰኛሉ። በሰማይም የተጻፉ የበኩራት ማኅበር በአንድነት ሐሴትን ያደርጋሉ። በነቢይ ቃል "ሰማያት ሆይ እግዚአብሔር አድርጎታልና ዘምሩ። እግዚአብሔር ያዕቆብን ተቤዥቶአልና፤ በእስራኤልም ዘንድ ይከብራልና። አንተ የምድር ጥልቅ ሆይ ጮኽ፤ እናንተም ተራሮች፣ አንተም ዱር፣ በአንተም ያለ ዛፍ ሁሉ እልል በሉ" እንደተባለ። /ኢሳ. 44፥27፣ ዕብ. 12፥23/ እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ሕዝብን አጽናንቷልና፤ ለችግረኞችም ራርቷልና፣ ሰማያት ሆይ! ዘምሩ፤ ምድር ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ ተራሮች ሆይ! እልል በሉ።" እንተባለ /ኢሳ. 49፥43/ ፍጥረት ሁሉ በዓሉን ያከብራል። ወንድሞቼ መዝሙረኛው ስለጠላት ጥፋት፣ ስለመዳናችንም ነገር በተናገረ ጊዜ "እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን" እንዳለ። /መዝ. 150/

በእርግጥም በአንድ ኃጢአተኛ ንስሓ በሰማይ ታላቅ ደስታ የሚደረግ ከሆነ ስለሁላችን ኃጢአት መደምሰስ ስለሙታን ትንሣኤማ





እንዴት የበለጠ አይሆን! አቤት! በሰማይ የሚደረግ በዓል ምን ዓይነት፣ እንዴትስ ታላቅ ይሆን?! ዘወትር በምስጋና የሚተጉ የሰማይ ሠራዊት በእኛ ጉባኤ የሚደሰቱ ወደ እኛም የሚያዩ ከሆነ በተለይ በበዓለ ትንሣኤ ደስታና ፈንጠዝያቸው እንዴት የግድ አይሆን!

ወደ ክፋት በሔዱ ጊዜ ፊታቸውን የነሷቸው፣ ቀድመው መጠን የለሽ በሆነ ፍትወተ ሥጋ የነበሩ ኃጥአን አሁን ግን ራሳቸ ውን በጾምና ራስን በመግዛት አኑረው ትሑት ሆነው ንስሐ ሲገቡ ሲያገኙአቸው ደግሞ ወደ እነርሱ ያያሉና።

በመጨረሻም በተዳከመው፣ በድንም በሆነው፣ እጅና እግሩ በተያዙበት በእርሱ በጠላታችን ላይ እናፌዝበት "ሞት ሆይ! መውጊያህ የት አለ?" እነሆ የድልን መዝሙር ለጌታ እንዘምር /1ቆሮ. 15፥55/።

እንግዲህ ወደዚህ ወደ መላእክት ኅብረት የሚመራን ማነው? ነቢዩ "ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ምስጋና መኖሪያ ስፍራ እገባለሁ፤ በዓል የሚያደርጉ ሰዎች የደስታና ምስጋና ቃል አሰሙ።" ይላል። /መዝ. 42፥4/ በፍላጐት ወደዚህ ሰማያዊ በዓል፤ ወደ መላእክትም ቅዱስ ቀን /የደስታ ቀን/ የሚመጣ ማነው? በዚህ ጉዞ ቅዱሳንም "ኑ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ።" በማለት ያበረታቱናልና። /ኢሳ. 2፥3/

## በዓሉ የንጹሐን ስለመሆኑ

ነገር ግን በዓሉ ለረከሱት አይደለም፤ ለኃጥአንም የሚወጡበት / ከፍ ከፍ የሚሉበት/ አይደለም፣ ለመልካሞችና ለትጉኀን፣ በቅዱሳን ዓላማ ለሚኖሩ ለእነዚያ እንጂ። "ወደ እግዚአብሔር ተራራ ማን ይወጣል? በቅድስናውስ ስፍራ ማን ይቆማል? እጆቹ የነጹ፤ ልቡም ንጹሕ የሆነ ነፍሱን ለከንቱ ያላነሣ፤ ለባልንጀራውም በሽንገላ

ያልማለ..." መዝሙረኛው አክሎ እንደነገረን "እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከትን፣ ከመድኃኒቱ አምላክም ምሕረትን ይቀበላል" /መዝ. 23፥4/ እነሆ ጌታችን እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ... የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ" በማለት በቀኙ ለሚቆሙት የሚሰጣቸው ይህን እንደሆነ የተረዳ ነው። /ማቴ. 25፥34/

ሐሰተኛ የሆነ ልቡ ንጹሕ ያልሆነ እሱ፣ ንጹሕ የሆነውንም ያልያዘ /የሌለው/ በእውነት እንግዳ /መጻተኛ/ ይሆናል። ከቅዱሳን ወገንም የተለየ፣ ከፋሲካው ለመብላት የማይገባ ሆኖ ይቆጠራል፣ "ከእርሱ እንግዳ ሰው አይብላ" ተብሏልና። /ዘጸ. 12፥43/

እንግዲህ ይሁዳ ፋሲካን ያከበረ መሰለው። ምክንያቱም በመድኃኒታችን ላይ የሐሰት ሤራን አዘጋጅቶ ነበርና /አላከበረውምና/ ለታላቂቱ ከተማ፣ ለሐዋርያትም ኅብረት ራሱን እንግዳ አደረገ፡ ሕጉ ፋሲካን የሚያከብሩት ብቻ እንዲበሉ አዟልና፤ ፋሲካን በበላ ጊዜ ወደ ነፍሱ ገብቶ ለነበረ ሰይጣን ተላላፎ ተሰጠ /ተገዢ ሆነ/። /ሉቃ. 22፥3/

በምድራዊ መንገድ በዓሉን አናክብር! መላእክት በሰማይ በዓሉን እንደሚያከብሩ እንጂ። ጌታን በንጽሕና፣ በጽድቅ፣ በመልካም ሥራዎቻችን ሁሉ እናክብር።

በራሳችን ሳይሆን በጌታ እንደሰት! ከቅዱሳን ጋር ወራሾች እንሆን ዘንድ በዓሉን እንደ ሙሴ እናክብር። በቀን ለሰባት ጊዜያት፣ በእኩለ ሌሊትም ለእግዚአብሔር እውነተኛ ፍርድ ምስጋናን ባቀረበ በዳዊት መንገድ እንሂው። እርሱ "በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ፤ በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ፤ እጠብቃለሁም" በማለት እንደነገረን በማለዳም እንነሣ! /መዝ. 5፥3/

እንደ ዳንኤልም እንጹም። ቅዱስ ጳውሎስም እንዳዘዘን ያለማ





ቋረጥም እንጸልይ። ሁላችንም ለጸሎት ጊዜያት አጽንኦት እንስጥ! በተለይ በክብር በንጹሕ ጋብቻም ያሉ ሁሉ፤ በዓሉን የሚጠብቁ፣ ለዚህ ነገር ምስክር የሆኑ ልጆችን ይወልዱ ዘንድ። በመንግሥተ ሰማያት ወደ ክርስቶስም ደስታ እንገባለን። እስራኤል ወደ ኢየሩሳሌም በተጓዙ ጊዜ በመጀመሪያ በበረሐ ውስጥ መንጻትን ፈጽመዋል። የግብጻውያንን ልማድ መርሳትን ተለማምደዋል።

የአብ ቃልም /ጌታ/ የዐርባ ቀናት ቅዱስ ጾምን ለእኛ ምሳሌ በመሆን ሰጥቶናል። አስቀድመን ንጽሕናን እንልበስ! ክርክሰትም እንንጻ! በምንጓዝበት /ከዚህ በምንለይበት/ ጊዜ በጾም የተጠነቀቅን እንሆናለን። ከጌታ ጋር ወደ ሰገነቱ እንወጣለን /ከፍ ከፍ እንላለን/፣ ከእርሱም ጋር ራት እንበላለን፤ በሰማይም ባለው ደስታ ተካፋይ እንሆናለን። የአርባ ቀናቱን ጾም ካላከበርን በሌላ በማንኛውም መንገድ ወደ ኢየሩሳሌም መጓዝ፣ ፋሲካንም መብላት አይቻልም።

በዚያም ቀን /በበዓለ ትንሣኤ/ ዕረፍት አድርገን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደስታ ትንሣኤውን እናክብር፤ በእርሱም ለአብ ክብር፣ ምስጋና ይሁን፤ ለዓለም ዓለም አሜን። ከእኔ ጋር ያላችሁ ወንድሞቼ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል፤ በተቀደሰ አሳሳም እርስ በእርሳችሁ ሰላም ተባባሉ።

# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሰባት

## ክርስቶስ መከራን ስለመቀበሉ

ብሩክ የሆነው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ የክርስቶስን ሞት በሰውነቱ እንደተሸከመ ትምክህቱም ይህ እንደሆነ ገልጿል። ይህንንም ሲገልጽ ግን ትምክህቱ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለቆሮንቶስ ለነበሩት ክርስቲያኖች እና ለእኛም ጭምር እንዲሆን አስቦ ጽፎት ነበር። ስለዚህም ወንድሞቼ ለእኛ የክርስቶስ ተከታዮች ለመሆን ለምንፈልግ ይህንን መልእክት ጽፎታል። ወንድሞቼ ሆይ! ይህን ትምክህት የሁላችን እና የሁልጊዜ መለያችን እናድርገው።

ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ይህንን ሲመሰክር "ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ እንገደላለን፣ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጥረን" አለ /መዝ. 43፥22/። ይህ ትንቢት ለኛ የተነገረ ነው። በዚህ የፋሲካ ዋዜማ በዐቢይ ጾም ደግሞ በይበልጥ የጌታችን ሞት መታሰቢያ በሚደረግበት ይህ የትንቢት ቃል በኛ ላይ በግልጽ ይፈጸማል። ሞቱንም በመሰለ ሞት እርሱን ክርስቶስን የሚመስለው ሰው ደግሞ በበጎ ሥራዎችም የበረታ ነው።

በምድር ላይ ሲኖር ብልቶቹንም ገድሏልና /ቆላ. 3፥5/። ሥጋንም ከምኞቱ ጋር በመስቀል ላይ ሰቅሏል። ስለዚህ በመንፈስም ሆኖ ይመላለሳል። እግዚአብሔርንም ሁል ጊዜ ያስባል፣ አይረሳውምም። ስለዚህ ደግሞ የሞት ሥራዎችን አይሠራም /ገላ. 5፥25/።

ስለዚህ እኛም የክርስቶስን ሞት በሰውነታችን ሁል ጊዜ እንሸከም ዘንድ የተባረከው ጳውሎስ ከላይ ካየነው ጥቅስ ቀጥሎ "አመንሁ





ስለዚህ ተናገርሁ" ተብሎ እንደተጻፈ ያው አንዱ የእምነት መንፈስ ስላለን እኛ ደግሞ ስለዚህም እንናገራለን በማለት ይህንን ያስረዳናል። /2ቆሮ. 4፥13/። በዚህ ዕውቀትና በመልካም እምነት ሆነው ቅዱሳን ይህንን እውነተኛ ሕይወት ስለሚያገኙ ያለጥርጥር በሰማያት ያለውን ደስታ ይቀበላሉ።

## ኃጥአን ለሥጋቸው በማሰብ ብቻ የሚኖሩ ስለመሆናቸው

ኃጥአን ግን ለእዚህ ዓይነት ሕይወት ስለማይጨነቁ በረከትን ይከለከላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንንም ሲመሰክር "ለኃጢአተኛ ሞገስ ቢደረግለት ጽድቅን አይማርም፤ የእግዚአብሔርን ግርማ አያይምና በማለት" መስክሮአል። ምንም እንኳ ዓለሙ ሁሉ የሚሰማውን አዋጅና እንደ ቃል ኪዳኑ የሰጠውን "አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ" /ኤፌ. 5፥14/ የሚለውን ቃል አስተውለው ለመመለስ ግን የዘገዩ ናቸው። ወደ ገነት በመምጣት በሩን እያንኳኩ "ክፈትልን" /ማቴ. 25፥11/ ቢሉም ጌታ "አላውቃችሁም" በማለት ይገሥጻቸዋል።

እራሳቸውን እርሱን በማመን አላበረቱምና "ኃጥአን ወደ ሲኦል ይመለሳሉ፥ እግዚአብሔርን የሚረሱ አሕዛብም ሁሉ እንዲሁ ይሆናሉ።" በማለት መንፈስ ቅዱስም ተናግሮባቸዋል /መዝ. 9፥17/ እኛም ብንሆን ኃጥአን ምውት ናቸው እንላለን። ነገር ግን በምድራዊ ሕይወትና ለኃጢአት ምውት እንዳልሆኑ እናውቃለን። እንደ ቅዱሳኑም በሚፈርሰው ሥጋቸው ሞትን አልተሸከሙም። ይልቁንም ነፍሳቸውን በኃጢአትና በክፋት ቀብረዋል። ይሄ ደግሞ ከሙታን ጋር አመሳስሎአቸዋል። ነፍሳቸውንም በኃጢአት እየገደሉ ከከፍተኛ ቦታ ለሚነሡ ለንስሮች ወይም በድንን ለመመገብ ለሚቸኩሉት አጋንንት እራሳቸውን ያመቻቻሉ። በመጽሐፍም ምሳሌያዊ በሆነ አገላለጥ "ንስርንም ሆነ በድንን የሚበላውን ሌላውን አሞራ

ሁሉ እንዳትበላ እነርሱ ለአንተ ርኩስ ናቸው" ተብሎ ተገልጿል /ሌዋ. 11፥13/። እንዲህ ዓይነቱን እንስሳ የበላ ሰው ሁሉ "ረክሷል" በማለት የኦሪቱ ሕግ ይደነግግ ነበር። ኃጥአን ግን ነፍሳቸውን በክፉ ምኞታቸው ይገድላሉ። ሁል ጊዜም "ዛሬ እንብላ እንጠጣ ነገ እንሞ ታለን" ይላሉ /ኢሳ. 22፥33/ በእግዚአብሔር ፊትም መራራ የሆነ ፍሬ በማፍራት ምኞትንና የሥጋ ፈቃድን ብቻ ለተከተሉትም "ይህ ሥራችሁ በእግዚአብሔር ፊት ተሰምቷልና በዚህ ኃጢአት ምክንያት እስክትሞቱ ድረስ ይህ በደል በእውነት አይሰረይላችሁም" በማለት ገስጾአቸዋል /ኢሳ. 22፥14/።

በእርግጥም በሕይወት ሳሉ ሀፍረት ያገኛቸዋል፤ ምክንያቱም ሆዳቸው አምላካቸው ሆኖ ኖረዋልና። በሞቱም ጊዜ ደግሞ ዳግም ይሰቃያሉ። እንዲህም ያለውን ሞት በሕይወት ሳሉ ተመክተ ውበታልና። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ሲመሰክር "መብል ለሆድ ነው ሆድም ለመብል፤ እግዚአብሔር ግን ይህንንም ያንንም ያጠፋ ቸዋል" ብሎ ጽፎአል /1ኛ ቆሮ. 7፥13/። ስለእነርሱም መለኮታዊው ቃል ሲገልጽ «ኃጢአተኞችን ይገድላቸዋል። ጻድቃንንም የሚጠሉ ሁሉ ይጸጸታሉ" ብሏል /መዝ. 34፥21/። ኃጢአተኞች በእርግጥ አስጨናቂ የሆነ ትልና ድቅድቅ ጨለማን ይወርሳሉ።

## ቅዱሳን የሥጋን ሥራ በማሸነፍ የሚኖሩ ስለመሆናቸው

ቅዱሳንና በጎን ሊሠሩ የሚፈቅዱ ሁሉ በምድር ያሉትን ብልቶቻቸውን ይገድላሉ። ከመዳራትም፣ ከርኩስ ምኞትና ከክፉ ኀሊና ይጠበቃሉ። ከዚህም የተነሣ ያለ ነቀፌታ ንጹሕ ናቸው። አዳኛችን ክርስቶስ ባስተማረውና ተስፋ በሰጠን ቃል መሠረት "ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታል" እንደሚል በቅዱሳኑ ሕይወት ይህ የተስፋ ቃል ተገልጧአል። ለዓለሙ ሙት በመሆናቸውና





የዓለሙንም ፈቃድ ባለመፈጸማቸው የተከበረ ሞት በእግዚአብሔር ፊት ይኖራቸዋል። በመጽሐፍ ቅዱስም "የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው" በማለት ይህንን ያረጋግጥልናል /መዝ. 115፥15/። በተጨማሪ በቃለ እግዚአብሔር እንደተማርነው ሐዋርያት "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል" እያሉ የኖሩትን ሕይወት ሌሎች ቅዱሳንም በመድገም ሐዋርያትን መስለዋል /ገላ. 2፥20/።

ይህ ዓይነቱ ሕይወት ሰው በክርስቶስ ሕያው ሆኖ የሚኖረው እውነተኛ ሕይወት ነው። ቅዱሳኑ ለዓለሙ ሙት ሆነው ሲኖሩ፣ ታላቅና ሰማያዊ የሆነውን ነገር በማሰብ በገነት ሕያው ሆነው ተመሳልሰዋል። ይህንን የመሰለውን ኑሮ የሚወደው ሐዋርያው እንዳለው በምድር ላይ ብንመላለስም "አገራችን ግን በሰማይ ነው" በማለት ይጽናናሉ /ፊል. ፫፥፳/። በዚህ መልክ የሚኖሩትና የዚህ ምግባር ተካፋይ የሆኑት ብቻ አምላክን እንዲህ ባለ ሕይወታቸው አክብረውታል።

## የቅዱሳን ሕይወት በዓልን ለማክበር የተገባ ስለመሆኑ

እንደዚህ ዓይነቱ ሕይወት መጪውን በዓልም በእውነት እንዲገለጥ ያደርገዋል። ምክንያቱም በዓል ማለት የደመቀ ጨዋታ ያለበት ማዕድ ብቻ አይደለም፤ ወይም የከበረ ልብስንም ተጎናጽፎ መብላት ብቻ አይደለም። ነገር ግን ለአምላክ ምስጋና በማቅረብ ነው። የምስጋና ሕይወት ለቅዱሳኑ ብቻ የተሰጠ ነው። በመጽሐፍም ይህ "አቤቱ፥ ሙታን የሚያመሰግኑህ አይደሉም ወደ ሲኦልም የሚወርዱ ሁሉ፤ እኛ ሕያዋን ግን ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እናመሰግንሃለን" በማለት ተጽፎአል /መዝ. 113፥25/።

ከሞት የዳኑ ክቡራን ነቢያትም እግዚአብሔርን "በሞት የሚያስብህ

የለምና፤ በሲያልም የሚያመሰግንህ ማነው?...›› ብለውታል። /መዝ 6፥5/ ‹‹ከሞትም ጋር ያደረጋችሁት ቃል ኪዳን ይፈርሳል፤ ከሲያልም ጋር የተማማላችሁት መሐላ አይጸናም” የሚልም ቃል ተነግሯል /ኢሳ. 28፥18/። እግዚአብሔርን ማመስገን የሚቻለው በክርስቶስ ለሚኖሩት ብቻ ነው። ይህንንም በማድረጋቸው ወደ በጉ በዓል ይሄዳሉ። የፋሲካውም በዓል ለአሕዛብና ለአይሁድ አይደለም። የፋሲካው በዓል እውነትን በክርስቶስ ለተቀበሉት ነው። ይህንንም ቃሉን እንዲናገር የተላከው ሐዋርያ “ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና” በማለት አረጋግጦታል /1ኛ ቆሮ. 5፥7/።

ምንም እንኳ ኃጢአተኞች በዓሉን ለማክበርና እግዚአብሔርን ለማመስገን በቅዱሳን ወደ ተሞላችው ቤተ ክርስቲያን ቢመጡም እግዚአብሔር ግን “ምስጋናዬን ለምን ትነግራለህ” በማለት ያሳፍረዋል። መንፈስ ቅዱስም "ከኃጢአተኛ አፍ ግን ክፋት ይፈልቃል" በማለት ይገሥጸዋል /ምሳ. 15፥28/። በእውነት ኃጢአት ከእግዚአብሔር ምስጋና ጋር አንድ የሚያደርገው ነገር የለም፤ ኃጢአተኛው ክፋትን የሚናገር አፍ አለውና።

በእርግጥም ንጹሕ ባልሆነ አንደበት እግዚአብሔርን ማመስገን እንዴት ይቻላል? ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች አብረው መኖር እንደማይችሉ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ላይ ቅዱስ ጳውሎስ “ብርሃንና ጨለማ ምን ኅብረት አላቸው” በማለት ይህንን እውነት ያረጋግጥልናል /2ኛ ቆሮ. 7፥14/። ስለሆነም ከአሐቲ ቤተ ክርስቲያን በመለየት የተወገዙ መናፍቃን እግዚአብሔርን ከማክበር የተለዩ ናቸው። ጻድቅ ግን ምንም እንኳን በዓለም ባሉት የሞተ ቢመስልም በንግግሩ ደፋር ሆኖ “አልሞትም በሕይወት እኖራለሁ እንጂ፤ የእግዚአ ብሔርንም ሥራ እናገራለሁ” ይላል /መዝ. 110፥17/። እግዚአብሔር





አመላካችንም እንደዚህ ላሉት አምላካቸው ተብሎ ሲጠራ አያፍርባቸውም በምድር ያሉትን ብልቶቻቸውን ገድለው በክርስቶስ ኖረዋል /ቆላ. 3፥5/። እግዚአብሔርም የሕያዋን እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም። እርሱም በሕያው ቃሉ ሰዎችን ሁሉ ይጠራል። ቃሉንም ለቅዱሳን ምግብና ሕይወት እንዲሆናቸው ሰጥቷቸዋል። ጌታችን ስለዚህ ሲናገር “እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ” በማለት ገልጾታል /ዮሐ. 6፥35/ ። አይሁድ ለማስተዋል ደካሞች ስለ ነበሩና በመንፈስም ስለማይ መረምሩ ይህንን ቃል መረዳት ተስኖአቸው ነበር። ጌታችንም “ለሰው ሁሉ ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ” ስላለ አንጎራጉረውበታል /ዮሐ. 6፥55/።

## ስለኃጢአት ማዕድ

ጌታችን ይህን የተናገረው ኃጢአት የእርሷ የሆነ ሌላ ዓይነት እንጀራ ስለ አላት ነው። ማስተዋል የሚጎድላቸውና ተድላ ደስታን ማድረግ የሚፈልጉትን እንዲሁም ለሞት የተጠሩትን “የስርቆት ውኃ ይጣፍጣል የተሸሸገም እንጀራ ደስ ያሰኛል። እነዚህንም የሚነካ ከኃጢአቱ ጋር ከምድር ላይ አብሮ እንደሚጠፋ የማያውቅ ነው” ብሏቸዋል /ምሳ. ፱፥፲፯/። ኃጢአተኛው ያንን ኅብስት በልቶ ተድላ ደስታ አገኛለሁ ብሎ ቢያስብም በመጨረሻ የሚኖረው ውጤት ግን መልካም አይደለም።

ዳግመኛም በእግዚአብሔር የሆነች ጥበብ “የሐሰት እንጀራ ለሰው የጣፈጠ ነው። ከዚያ በኋላ ግን አፉ ጭንጫ ይሞላል።” አለች። በኋላ አያይዞም “ከጋለሞታይቱ ሴት ከንፈር ማር ይንጠባጠባል፤ አፍዋም ከቅቤ የለሰለሰ ነው። ፍጻሜዋ ግን እንደ እሬት የሚመር ነው ሁለት አፍም እንዳለው ሰይፍም የተሳለ ነው /ምሳ. 5፥4/ በማለት ይመክረናል። ኃጢአተኛውም ለጊዜው ይበላል፤ ተድላ

ደስታንም ያደርጋል፤ ነፍሱን ካጠፋ በኋላ ግን ያጣዋል። ማስተዋል የጎደለው ሰው ከእግዚአብሔር ሲለይ እንደሚጠፋ አይረዳምና።

በነቢያትም አፍ ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ ሌላ የተነገረ ትንቢታዊ ተግሣጽ አለ። እርሱም በግብጽ ወንዝ ዳር ምን ታደርጋላችሁ? የጊዮንን /ዓባይ/ ውኃ ለመጠጣት ነውን? ደግሞም በአሶር መንገድ ምን ታደርጋላችሁ? የወንዞቻቸውን ውኃ ለመጠጣት ነውን? ከእግዚአብሔር የሆነ ጥበብም እንደእነዚህ ያሉትን ሥራዎች እንዳይሠሩ እንዲህ በማለት ይከለክላቸዋል። "ቶሎ ከዚያ ቦታ ሽሽ፤ በዚያም አትቆይ፤ ዐይንህንም በእርሱ ላይ አታድርግ፤ እንግዳ ከሆኑም ውኃዎች ተለይተህ ትሄዳለህ።"

## ጥበብ ስላዘጋጀችው ማዕድ

እንደገናም ይህችው ከእግዚአብሔር የሆነች ጥበብ እንዲህ በማለት ሰዎች ወደ እርስዋ እንዲቀርቡ ትጠራለች። "ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሰሶዎች አቆመች፤ ፍሪዳዋን አረደች የወይን ጠጅዋን ደባለቀች፤ ማዕድዋን አዘጋጀች። ባሪያዎችዋን ልካ በከተማ ይቱ ከፍተኛ ሥፍራ ላይ ጠራች አላዋቂ የሆነ ወደዚህ ፈቀቅ ይበል፤ አእምሮ የጎደላቸውንም እንዲህ አለች፡- ኑ እንጀራዬን ብሉ የደባለቅሁትንም የወይን ጠጅ ጠጡ" /ምሳሌ 9፥1-5/

ከዚህስ ውጭ ምን ተስፋ አለ? "አላዋቂነትን ትታችሁ በሕይወት ኑሩ በማስተዋልም መንገድ ሂዱ" እንደተባለ ይህንን ማድረግ ከሰው ይጠበቃል /ምሳሌ 9፥6/። የጥበብ እንጀራም ሕያው ፍሬ የሆነና ጌታችንም "ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፣ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል" ያለው ነው /ዮሐ. 6፥51/። እስራኤላውያንም በምድረ በዳ የበሉት መና ምንም እንኳ መልካም እንጀራ ቢሆንም ከሞት ግን አላዳናቸውም። የበሉትም





ለዘላለም ሕያው ሆነው አልኖሩበትምና ስለዚህ "አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፤ ሞቱም፤ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ" /ዮሐ. 6፥51/። ኃጥአን እንደዚህ ያለውን እንጀራ ይራባሉ።

## የጻድቃን እንጀራ

ጻድቃን ግን ለመብላት የሚገባቸው ሆነው ተገኝተዋል፤ ተዘጋጅተውማል። "እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ፤ ክብርህን ሳይ እጠግባለሁ›› እያሉ በሚበሉት እንጀራ ይረካሉ /መዝ. 16፥15/። መለኮታዊ እንጀራ ከሆነው የሚበላም ሁሉ በፈቃዱ የማያልቀውን የእግዚአብሔር ጸጋ ይመኛል። በመጽሐፍ ቅዱስም "ጌታ የጻድቁን ነፍስ በረኀብ አይቀስፍም" ይላልና፤ በመዝሙርም እንዲህ ሲል ቃል ገብቶላቸዋል "በረከትዋን አብዝቼ እስኪትረፈረፍ እባርካለሁ፤ ድሆች ዋንም በእንጀራ አጠግባለሁ"።

ጌታችንና አዳኛችንም በወንጌል "ጽድቅን የሚራቡ የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና" /ማቴ. 5፥6/ በማለት ነግሮናል። በእውነት ቅዱሳንና በክርስቶስ ያለውን ሕይወት የሚያፈቅሩት ሁሉ ይህንን እንጀራ ቢናፍቁ አያስገርምም፡ በጽናትም የሚለምኑት "ውኃን ዋላ እንደሚጠማ እንዲሁ ነፍሴ አንተን ተጠማች፤ መች እደርሳለሁ? እግዚአብሔርን ፊቱን መቼ አየዋለሁ" በማለት ነው /መዝ. 41፥1/። እንዲሁም "አምላኬ በማለዳ አንተን እፈልጋለሁ ነፍሴ አንተን ተጠማች በምድረ በዳም ተቅበዘበዠች ፊትህም በጽድቅ ቆምኩ ክብርህንና ኃይልህን አይ ዘንድ" በማለት ይጸልያሉ።

እነዚህ ነገሮች እንዲህ በመሆናቸው በምድር ያሉትን ብልቶቻችንን እንግደል /ቆላ. 3፥5/። በሕያው እንጀራም እንጎልብት በእምነትና ለእግዚአብሔር ባለን ፍቅር ወስጥ ሆነን እንብላው። ያለ

እምነት ይህንን እንብላ። ያለ እምነት ይህንን እንጀራ መብላት አይቻልምና። መድኃኒታችንም ሰዎችን ሁሉ ወደ እርሱ በሚጠራበት ጊዜ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣ" በማለት አስተምሮ አቸዋል /ዮሐ. 7፥37/። በዚህም ትምህርቱ ሰው ያለ እምነት ሊበላው ስለማይችለው እንጀራ አስተምሮአል። "በእኔ የሚያምን መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል" / ዮሐ. 7፥38/ በማለት እርሱን የሚያምኑትን ደቀ መዛሙርት በቃሉ እየመገባቸው በመለኮታዊ ቅርበቱም ሕይወትን እየሰጠ አኑሮአቸዋል።

ከነናዊቷ ሴት ግን ከሚያምኑት ወገን ስላልነበረች ምንም እንኳን ምግበ ነፍስን ከእርሱ ብትሻም ከእርሱ የሚሰጠውን ነገር ሁሉ ለማግኘት ማመን የሚገባ መሆኑን ለማስረዳት መልስ እንኳን ሊመልስላት አልወደደም ነበር። ይህንን ጌታችን ያደረገው ከንቀት አይደለም። /እርሱ ጌታችን ሰውን ሁሉ እኩል የሚወድ ስለመሆኑ ብዙ ጥቅስን ማቅረብ ይቻላል። ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው ጢሮስና ሲዶና ድረስ እየሄደ አሕዛብን ማስተማሩና መፈወሱ ነው። ነገር ግን የቅዱስ ቃሉን በረከት ካላገኙ /ከሌላቸው/ ወገኖች የመጣች በመሆኗ በእምነት ውስጥ ስትመላለስ ስላልኖረች ለከነናዊቷ ሊመልስላት አልወደደም። አምላካችንም ይህንን እንደሚገባው ለጽድቅ እንደሚሆን አድርጎላታል። ምክንያቱም እርሷ ከማመንዋ በፊት ምልጃ ማቅረቧ ምንም ጥቅም የሌለው ነው። በእምነት ሆና ግን ምልጃ ማቅረቧ ተቀባይነት ያስገኝ ነበር። "ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሐር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና" /ዕብ. 11፥6/። በማለት ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሮናል። ከማያምኑት ወገን በመሆንዋ ከርኩሰት ሳትለይ መኖሯንም ለማመልከት "የልጆችን





እንጀራ ለውሾች መስጠት አይገባም" በማለት ጌታችን ተናግሯታል። እርሷም በኃይለ ቃሉ ተረዳች። እምነትዋን ፍጹም አደረገች፤ እምነ ትንም ጨመረች፤ አምላካችንም እንደ ውሻ ሳይሆን ለሰብአዊ ፍጡር የሚገባውን ክብር ሰጥቷታል። በመጨረሻም "አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው" በማለት መስክሮላታል /ማቴ. 15፥28/። የእምነቷንም ፍሬ "አንቺ ሴት እንደ ወደድሽ ይሁንልሽ በማለት በረከቱን እንድትቀበል አድርጓል። በዚያም ሰዓት ውስጥ ልጅዋ ተፈውሳላታለች።

ጻድቅ ሰው በእምነት የሚበረታና የሚታደስ በመሆኑ በእውቀትና እግዚአብሐርን በማምለክ ነፍሱ ጤናማ እንድትሆን ያደርጋል። በመጽሐፍም እኛ ኃይለኞች የመሆንን የደካሞቹን ድካም እንድንሸክም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል" የሚለውን ትእዛዝ ይተገብራል / ሮሜ. 15፥1/። ቃለ እግዚአብሔር ደካማው በሚመገብበት ጊዜ ጠንካራ የሆነውን አጥንት ለመብላት አይችልምና እንደዚህ ዓይነቱ ትምህርት ሊሰጠው አይገባም። ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንኳን እንዲህ ያለውን ሊበሉ አልተቻላቸውም። በመንፈስ ግን ሕፃናት በመሆናቸው ልክ እንደ ሕፃን የቃሉን ወተት እንዲጠጡ ሥርዐት ተሠርቶላቸዋል /1ኛ ቆሮ. 3፥15/። ሐዋርያው ለጢሞቴዎስ በላከለት የመጀመሪያ መልእክቱም ላይ "በእምነት በተከተልከው በመልካም ትምህርት ቃል የምትመገብ የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም አገልጋይ ትሆናለህ ይለዋል /1ኛ ጢሞ. 4፥6/። በድጋሚም "በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነትና ፍቅር አድርገህ፥ ከእኔ የሰማኸውን ጤናማ ቃል ምሳሌ ያዝ" በማለት ጽኑ ትእዛዝን ሰጥቶታል /2ኛ ጢሞ. 1፥13/።

ይህን ጻድቃን የሚመገቡትን እንጀራ ወይም ክቡር ሥጋውንና ቅዱስ ደሙን በምድር ላይ የምንመገበው ብቻ አይደለም። በሰማያት ጭምር የምንመገበው እንጀራ ነው። እርሱም ለመንፈሳውያን መላእክትና

ለቅዱሳን ነፍሳት ጌታችን ያዘጋጀው ምግብ ነው። ስለዚህ "የሰማያት ሠራዊትም ሁሉ ደስታ ነው" ብሎ ተጽፎአል። ለሁሉም ቢሆን እርሱ ሁሉ ነገር ነው። ለፍጥረትም ሁሉ ፍቅርና ደግነት ያለው እርሱ ጌታችን ብቻ ነው። ጌታችንም አስቀድሞ የመላእክትን እንጀራ ሰጥቶናል። እርሱ ባሳየው መንገድ ለሚጓዙ "አባቴ እኔን እንደሾመኝ እኔ ደግሞ በመንግሥቴ ከማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ በዐሥራ ሁለቱም በእስራኤል ነገድ ልትፈርዱ በዙፋኖች ትቀመጡ ዘንድ ለመንግሥት እሾማችኋለሁ" በማለት ቃል ገብቷል /ሉቃ. 22፥29/። ወንድሞቼ ይህ ሰማያዊ ማዕድ ምንኛ አስደሳች ይሆን? በዚያም ለሚበሉት እጅግ ብዙ ደስታና ኅብረት አላቸው።

ቅዱሳን ተስፋ አድርገው ለዚህ ደረጃ የበቁት ደግሞ ጠፊ ለሚሆነው መብል ሳይሆን ዘላለማዊ ሕይወትን ለሚያሰጠው መብል ስለተጋደሉ ነው። በዚያ የተቀደሰ የሐዋርያት ማኅበር ውስጥ ለመግባት የሚበቃ ሰው ማን ነው? በመጽሐፍም "በእግዚአብሔር መንግሥት እንጀራ የሚበላ ብፁዕ ነው" ያለው ከዚህ የተነሣ ነው /ሉቃ. 14፥15/።

የመንግሥተ ሰማያትን ርስት ለመውረስ ተጠርቶ ሳለ፤ በዚህም ጥሪ ከተቀደሰ በኋላ ቸልተኛ በመሆን እራሱን አርክሶ የቃል ኪዳኑን ደመ መሥዋዕት እንደ ርኩስ ለቆጠረ ሁሉ በመጨረሻው ቀን "ወዳጄ ሆይ የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ?" በመባል ከተቀደሰው ማዕድና እልፍኝ ይወገዳል /ማቴ. 22፥11/። የቅዱሳን ማዕድ ያለ ነውርና ነቀፋ ንጹህ ነውና፤ለጥቂቶች ንጹሐን የተገባ ነው። መጽሐፉ ይህንን "የተጠሩ ብዙዎች የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው" በማለት ያረጋጋጥልናል /ማቴ. 22፥14/። ይሁዳም በቅዱሱ ማዕድ ላይ ተገኝቶ ነበር፤ ነገር ግን ስለናቀውና ስለ





አቃለለው ከጌታችንም መለየትን ስለመረጠ ከፊቱ ተነሥቶ ሄደ።

በዚህም ይሁዳ ሕይወቱን ጣለ፤ በገመድም ታንቆ ሞተ /የሐዋ. 1፥13/። ከመድኅን ዓለም ክርስቶስ ጋር የዘለቁት ሐዋርያት ግን በማዕዱ ደስታን አግኝተዋል።

ከዚህ ጋር የሚያያዝ ሌላ ታሪክም አለ። ይህም እርሱም "እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ እሄዳለሁና! አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ! ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከሙያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ" አለ ይላሉ /ሉቃ. 15፥17/። እንዲህ ብሎ በመጸለይም ከጸሎቱ በላይ በረከትን እንዲያገኝና ልጅ እንዲባል በቅቷል። አባቱም እንደ ሞያተኛና እንደ እንግዳ ሳይሆን ልጄ እያለ ስሞታል። በተቀደሰው ማዕድ ላይም ለመገኘት የሚገባው ነው ብሎ ፈርዶለታል። በአባቱም ቤት የመሰንቆ ድምፅ፣ ዘፈንና ደስታ ሆኖአል።

ይህ የአባቱን ፍቅርና ደግነት የዋህነትም የሚገልጽ ነው። ከሞት ድኗል በማለት ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስና በጸጋው የሚከብር በጎ ሰው አድርጎታል። ስለዚህ ከሚያልቅ ልብስ ይልቅ የማያልቅ እራቁቱን ሸፍኖታል። በረኀብም ከመሰቃየት ይልቅ የሰባውን ፍሪዳ አርዶለታል። ወደ እሩቅ ጉዞ እንዲሄድ ከማዘዝ ይልቅ ለእግሮቹም ጫማ አድርጎለታል። ከዚህ ሁሉ የሚበልጠውን ቀለበት በጣቶቹ ላይ አድርጎለታል። እነዚህ በቅዱሱ አባት የሚሰጡ ስጦታዎች በእርሱ ለሚኖሩትና በንስሐ ለሚመለሱት የሚያድላቸው ናቸው። እርሱም የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም በማለት ቃል ገብቶአል /ዮሐ. 6፥35/። እኛም ጭምር በእነዚህ ስጦታዎች እንድንከብር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ከእርሱም ጋር ከሆንን ለእነዚህ ስጦታዎች የቲገባን እንሆናለን።

## ስንብት

ጾም እንዳለ ሁሉ የፋሲካ ቀኖችም አሉ፡፡ በእነዚህ የፋሲካ ቀኖች በቅድስና እንደ ተመላለስን ሁሉ ንጹሕ ሆነን እንዲሁም ሕይወታችንን በሙሉ በዓል እንደሆነ ብንቀበል ወደ እርሱ በመቅረብ "ጌታ ሆይ ካንተ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም የሕይወት ቃል አለህ?" ልንለው ይገባል፡፡ በዓለም ያለነው በንስሐ እንመለስ፤ የሥጋንም ሥራ እንግደል /ሮሜ. 10፥13/፡፡ መጀመሪያ ነፍሳችንን ከመገብን ከመላእክት ጋር በዚያ ሰማያዊ ማዕድ እንቀመጣለን፡፡ እንደነዛ ሰነፍ አምስቱ ልጃገረዶችም አንሆንም /ማቴ. 25፥1-12/፡፡

ነገር ግን እንደ ልባሞቹ ልጃገረዶች መብራታችንን አብርተን ሙሽራውን በመውደድ እናገልግል፡፡ እንዲሁም የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን በመኖር ከእርሱ ከአምላካችን ዘላለማዊ መንግሥቱንና ሕይወትን እንወርሳለን /2ቆሮ. 4፥10/፡፡

ጾሙን ካሳለፍን በኋላ በተቀደሰው በፋሲካ ቀን ያውም በእሑድ ወይም በጌታ ቀን በሚባለው በዓል ላይ ዕረፍት እናድርግ፡፡ ከዚያም በኋላ የተቀደሰውን በዓለ ሃምሳን እናክብር፡፡ በዕድሜያችን ሁሉ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችንን እናምልክ፡፡ ክብርና መንግሥት ለዘላለሙ ለእርሱ ይሁን፤ አሜን፡፡ ወንድሞቼ ይህንን መልእክቴን ስፈጽም እናንተን እጅ እየነሣሁ፤ እርስ በእርሳችሁ በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ትሰጣጡ ዘንድ እለምናለሁ፡፡





# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ዐሥር

## ስለተቀበለው መከራ

ምንም እንኳ ከእናንተ ርቄ ተጉዤ የምገኝ ቢሆንም ወንድሞቼ ሆይ ከእናንተ ያገኘነውን በአባቶቻችን የተሰጠንን ከእናንተ ያገኘነውን ልማድ የዓመቱን የተቀደሰ በዓል የሚከበርበትንም ጊዜ ሳላውጅ በዝምታ አልፍ ዘንድ አልረሳም፡፡ ምንም እንኳን በእኔ ላይ በሆኑ ታላላቅ መከራዎች ከእናንተም ርቄ በመገኘቴ ብንለያይም፤ የእውነት ጠላቶችም መንገዳችን እየተከታተሉ በክሳቸውም ምክንያት እንክርዳድ እየዘሩ በቁስላችን ላይ ሕማም ቢጨምሩብንም እግዚአብሔር ግን አበረታን፡፡ ከመከራችንም አጽናናን በእነዚህ መከራዎችና እና ሤራዎች መካከል ሆነንም እንኳ የዳንበትን ትንሣኤ በዓል ከምድር ዳርቻ ሆነን ለማብሠር አንፈራም፡፡

ለእስክንድርያ ካህናት በጻፍኩላቸው ጊዜ ጠላቶች ያሳደሩባቸውን ፍርሃት ባውቅም በእነርሱ አማካኝነት ሊልኩላችሁ እንደሚችሉ በመንገር አነሣሡኝ፡፡ ነገር ግን ቅዱሳን ሐዋርያት ለመናገር የነበራቸው ድፍረት እንዲሁም "ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስደት ወይስ ራብ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን?›› /ሮሜ 8፥35/ ማለታቸውን እንዲያስቡ አነሣሣቸዋለሁ፡፡ ስለዚህ እኔ በዓሉን በጉጉት እንደምጠብቅ እናንተም እንዲህ እንድትሆኑ እመኛለሁ፤ ወዳጆቼ በዓሉን ልናከብር ይገባናልና፡፡ እንዲሁም ይህንን የማብሠሩ ሓላፊነት ከእኔ የሚጠበቅ ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን ሓላፊነቴን ለመወጣት አልዘገይም፤ በቅዱሳን ሐዋርያት ጉባኤ እንዳልወገዝ እፈራለሁና፡፡ "ለሁሉ የሚገባውን

አስረክቡ›› /ሮሜ 13፥7/ እንደተባለ።

እንግዲህ የእኔን ጉዳዮቼን ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰጥቼ በእኔም በእናንተም መካከል ያለውን ርቀት ሳላስብ በዓሉን ከእናንተ ጋር ለማክበር እጨነቃለሁ። ምንም እንኳ ቦታ ቢለያየንም እርሱ በዓልን የሚሰጥ በዓላችንም የሆነ ጌታ፣ እርሱ ራሱ መንፈስን የሚያድል ጌታ አንዳችን ለአንዳችን ጸሎትን ባቀረብን ጊዜ ምንም በቦታ ብንለያይም፤ አንድ ያደርገናል እንጂ። እርሱ “ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ›› /ማቴ 18፥20/ ብሎ ቃልኪዳን በሰጠን ጊዜ በቦታ ሁሉ ያሉትን በመንፈስ ተገኝቶ አንድ እንደሚያደርገን በአንድ ላይ በቅርበት እንዳለን አድርጐ የሁሉንም ጸሎት እንደሚቀበል አንድ ሆነን “አሜን” ብለን እንደምንጮኽም አድርጐ የሁሉንም ድምፅ እንደሚሰማ ግልጽ ነው። እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በጻፍኩላችሁ ጊዜ የጠቀስኩላችሁን መከራ ፈተናዎችም ሁሉ እየተቀበልሁ ነው።

## ለሚያድን ለእግዚአብሔር ምስጋናን ስለማቅረብ

እንግዲህ በፍጹም ልናስጨንቃችሁ አንሻም። አሁን ብቻ ግን በአጭሩ እነዚህን ነገሮች እናስታውሳችሁ። ምክንያቱም በመከራ በሕማም ውስጥ ያለፈ ማንም በሰላሙ ጊዜ ስቃዩን ሊረሳው አይችልም። እንዲህ ቢሆን እንደማያመሰግን ሰው ከመለኮት ኅብረት /ጉባኤ/ ይለያልና። ከመከራ ከወጣበት ከተሻገረበት ከዳነበት ጊዜ በላቀ ሰው በታላቅ ደስታ እግዚአብሔርን ሊያመሰግን የሚችልበት የተሻለ ጊዜ የለውም። ከፈተናም ዕረፍት ካገኘበት ጊዜ በተሻለ አምላኩን እግዚአብሔርን አያመሰግንም። ሕዝቅያስ አሦራውያንን በጠፉ ጊዜ እግዚአብሔርን እንዳመሰገነው፣ ሠለስቱ ደቂቅም በባቢሎን ከእሳት በዳኑና እሳቱ በፊታቸው ውርጭ በሆነ ጊዜ አመሰገኑ። "የአባቶቻችን





ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን፤ የተመሰገነ ነው። ለዘላለሙ የከበረ ነው" አሉ /መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ 25-28/

ይህ በሐሳባችሁ ዘወትር እንዲኖር እኔም እንደ እነርሱ እጽፍላችኋለሁ። በአሁንም ዘመን ቢሆን እግዚአብሔር ለሰዎች ማድረግ የማይቻላቸውን ማድረግ ይቻለዋል። በሰዎች ፈቃድ ሊሆን የማይቻለወን እኛን ወደ እናንተ የማምጣትንም ነገር በእግዚአብሔር ፊት ለመከወን እጅግ ቀላል ነው። ሊውጡን ለሚፈልጉ ለእነዚያ ታዳኝ /ሰላባ/ አድርጐ አይሰጠንምና። ቤተክርስቲያን፣ እምነትና መልካምነት በክፋትና ክፉዎች የሚሸነፉ አይደሉምና።

መልካም የሆነው እግዚአብሔር ግን የርኅራኄ ፍቅሩን በእኛ ላይ አበዛ። ይህ ለሁሉም ሰው በአካላዊ ቃሉ ማዳንን በሰጠበት ጊዜ ብቻ የሆነ አይደለም። አሁንም ጠላቶች በሚያሳድዱን ሊይዙን በጥብቅ የሚፈልጉበት ጊዜም ነው እንጂ። ቅዱስ ጳውሎስ ፍፃሜ ስለሌለው ስለ እግዚአብሔር ብልጽግና በጻፈ ጊዜ “እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን እንኳ ሙታን በሆን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን›› ብሏል። /ኤፌ 2፥4-5/ የሰውና የፍጥረት ሁሉ ኃይልና ጥበብ ደካማና ባዶ ነውና። ነገር ግን ከሰው በላይ የሆነውና ያልተፈጠረው ኃይል የበለጸገና ፍፃሜ የሌለው ነውና። መጀመሪያ ያለው ዘላለማዊ ነው። እርሱ መፈወስን ብቻ የሚያውቅ አንድ መላ /ዘዴ/ ያለው አይደለም። ፍጹም ባዕለጸጋ ነው እንጂ።

## ቃሉ ለድኅነታችን የተሰጠ ስለመሆኑ

ከእኛ ጋር ለመገኘት ወሰን በሌለበት በማይደናቀፍ በእርሱ በቃሉ አማካኝነት ለድኅነታችን በተለያየ መንገድ ይሠራል። እርሱ ባዕለጸጋና ባለ ብዙ ዕጥፍ የሚሰጥ ስለሆነ ለእያንዳንዱ ነፍስ እንደ

አቅሟ በሚሰጠው ጸጋ ልዩ ልዩ አድርጐ ስጦታውን ያቀርባል። እርሱ ክርስቶስ ቃሉና ኃይሉ ስለሆነ የእግዚአብሔርም ጥበብ ነው። ሰሎሞንም ስለዚህ ሲመሰክር ‹‹አንዲት ስትሆን ሁሉን ማድረግ ትችላለች፤ራሷም እየኖረች ሁሉን ታድሳለች፤ በየትውልዱም በጻድቃን ሰውነት ትተላለፋለች፤ የእግዚአብሔርም ወዳጆችና ነቢያቱ ታደርጋ ቸዋለች›› ብሏልና። ነገር ግን ለእነዚያ እውተኛውን ፍጹሙን መንገድ ላልደረሱበት /ላላገኙት/ ወተት እንደምትሰጥ የዋሕ በግ ሆነ። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጽ "ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኂችሁ›› እንዳለው ነው። /1ቆሮ 3÷2/

ለእነዚያ ለአዋቂዎች ከሕፃንነት ወራት ላለፉት ስለ ፍጽምና ሲነሣ ደካማ ቢሆኑም እርሱ እንደ አቅማቸው ምግባቸው ነው። ይህም በቅዱስ ጳውሎስ ሲገለጽ "ደካማው ግን አትክልት ይበላል » /ሮሜ 14÷2/ የተባለው ነው። ነገር ግን ሰው ፍጹም መንገድ መጓዝ እስከጀመረ ድረስ ቀድሜ የጠቀስኩላችሁን ብቻ አይመገብም ለእንጀራ የሚሆን ቃል አለው፤ ለምግብ የሚሆን ቃል አለው "ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፋውን ለመለየት በሥራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው›› ተብሎ እንደተጻፈ። /ዕብ 5÷14/ በተጨማሪም ቃሉ ሲዘራ በዚህ የሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ አንድ ዓይነት መጠን ምርት /ፍሬ/ አይገኝም፤ ልዩ ልዩና ብዙ ነውና። አንዱ መቶ አንዱ ስድሳ አንዱ ሠላሳ ያፈራልና። ጸጋን የሚዘራ የመንፈስም ሰጪ መድኅኔዓለም እንዳስተማረው። /ማቴ 13÷8/

ይህ የሚያጠራጥር ጉዳይ አይደለም፤ ማንም ቢሆን ማረጋገጫ አይፈልግባትም። ይህ በእኛ ኀይል /ሥልጣን/ ሥር ያለ በእርሱ የተዘራውን የምናይበት መስክ ነው። ቃሉ ዕጥፍ የሆነባት ብዙውን በምታፈራ ቤተ ክርስቲያን የሆነ ነውና። በዚሁ መስክ የሚያጌጡበት





ደናግላን እንዲሁም መነኮሳት ብቻ አይደሉም። በክብረ ጋብቻ እና በንጽሕና ሕይወት ውስጥ ያሉትም ናቸው እንጂ። ምሕረትም ለፍጹማን ብቻ የሆነ አይደለም፤ ለማእከላውያንና ለወጣንያንም በየመዓርጉ ላሉትም ተልኳል። ስለዚህ ሁሉንም የሰው ልጆች በማዳኑ ታድጓቸዋል።

## ወደ እግዚአብሔር ደጅ ስለመግባት

በዚህም ዓላማ ከአባቱ ጋር ብዙ ማደሪያን አዘጋጀ /ዮሐ. 14÷2/ ምንም እንኳ ማደሪያዎቹ በየመዓርጉ ልዩ ልዩ ቢሆኑም በመልካ ምነት ብቃት ላይ ለደረሱም ሆነ ለእኛ ለሁላችን በቅጽሩ ውስጥ ገብተናል። ጠላትም ተጥሏል፤ ሠራዊቱም ሁሉ ተሰዷልና። ከብርሃን ተለይቶ ጨለማ፣ ከበረከት ተለይቶ ርግማን አለ። ዲያብሎስም ከቅዱሳን ዓለም ተለይቷል። «ሂድ አንተ ሰይጣን» /ማቴ. 4÷10/

እኛን ግን «በጠበበው ደጅ ግቡ» ዳግመኛም «እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ፣ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ» አለን። /ማቴ. 7÷13፣ ማቴ 25÷34/ መንፈስም አስቀድሞ በመዝሙር እንዲሁ እያለ ጮኸ። «ወደ ደጆቹ በመገዛት ፣ወደ አደባበዮቹ በምስጋና ግቡ» /መዝ. 100÷4/ ሙሴ እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ ጥቅጥቅ ወፍራም ደመና እንደገባ ሰው በበጎ ሥራው ወደ እግዚአብሔር ይገባልና።

በክፋት ሥራ ግን ሰው እግዚአብሔር ካለበት ወጥቶ ይጣላል። ቃየን ወንድሙን በገደለ ጊዜ ከእግዚአብሔር ፊት ሸሽቶ ወደ ፈቀደበት ተቅበዘበዘ። መዝሙረኛው ግን «ወደ እግዚአብሔር መሠዊያ ኀልማሳነቴን ደስ ወዳሰኛት ወደ አምላኬ እገባለሁ» እያለ ይገባል። /መዝ. 43÷4/

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዲያብሎስም ከእግዚአብሔር ፊት መጣሉን ይመሰክራሉ። በቁስል በተመታው በኢዮብ ላይ እንደሆነው ግን /ኢዮ. 2÷7/ አማኙን ማቁሰልና ማሳደድ ግን ከእምነት ወጥተው የሚጣሉ የክፉዎች ጠባይ ነው። ቅዱሳን ግን ወደ እነርሱ ይቀበላሉ።

እንደ ባልንጀራም ያያሉ:: ክቡር ዳዊት እንደተናገረው «ከእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ ዓይኖቼ በምድር ምእመናን ላይ ናቸው» አለ:: /መዝ. 101÷6/ ቅዱስ ጳውሎስ ግን በእምነት የደከሙትን ወደ እኛ እንድንቀበላቸው አነሣሣን::

## ስለፍቅርና ጥላቻ

ሁለት ተቃራኒ ጠባይ እንዳላቸው ሰዎች ዓይነት መልካም ሥራ /ጽድቅ/ የፍቅር ቸርነት ሥራ ሲሆን የኃጢአት ሥራ ደግሞ ጥላቻ ነው:: ሳኦል ክፉ በመሆኑ ዳዊትን አሳደደው፣ ዳዊት ግን ለመግደል ዕድል ቢያጋጥመውም ሳኦልን አልገደለውም:: ዔሳውም ያዕቆብን አሳደደ፤ ያዕቆብ ግን በየዋህነት የእርሱን የክፋት ሥራ አሸነፈ:: እነዚያም ዐሥሩ አንዱ ዮሴፍን ሸጡት፤ ዮሴፍ ግን በፍቅሩ ርኅራኄ ለእነርሱ አዘነላቸው::

ብዙ ቃላት መናገር ለምን ያስፈልገናል? ጌታችን መድኃኒታችን ራሱ በፈሪሳውያን መከራ በተቀበለ ጊዜ ስለጥፋታቸው አለቀሰ:: እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ለደፈሩት አዘነላቸው:: እርሱ ጌታ ስለሰው መከራን ተቀበለ፤ ነገር ግን ሰዎች ናቁት፤ ከእነርሱም አውጥተው ሕይወትን፣ ብርሃንን፣ ጸጋን ገፍተው ጣሉ:: እነዚህ ነገሮች ግን ስለእኛ መከራን በተቀበለው በመድኃኒታችን በኩል የእኛ የሆኑ ነበሩ:: ስለዚህ ስለእነሱ ጨለማና ዕውርነት አለቀሰ:: ነገ

በመዝሙር መጽሐፈ የተጻፈውን አስተውለው ቢሆን መድኃኒታችንን ለመቃወም ባልደፈሩ ነበር:: መንፈስም እንዲህ አለ «አሕዛብ ለምን ያጉረመርማሉ ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ» /መዝ. 2÷1/ የተጻፉትን ነገሮች በማስተዋል ቢመረምሩ በእነርሱ ላይ የተነገሩትን ትንቢቶች ባልሆኑባቸው ነበር:: አሁን ግን ከተማቸው ጠፋች፤ ጸጋ ከእነርሱ ተነጠቀ፤ እነርሱ ራሳቸው ያለ ሕግ የሚመላለሱ ሆኑ፣ ከእንግዲህ መጻተኞች እንጂ ልጆች ተብለው አይጠሩም:: አስቀድሞ መዝሙረኛው «የባዕድ ልጆች አረጁ በመንገዳቸውም





ተሰናከሉ» ኢሳይያስም «ልጆችን ወለድሁ አሳደግሁም እነርሱም ዐመፁብኝ» አለ:: /መዝ 18÷45፣ ኢሳ ፩÷2/ ከእንግዲህ የእግዚአብሔር ሀገርና ሕዝብ ተብለው አይጠሩም የሰዶም ገዢዎችና የገሞራ ሕዝብ እንጂ::

በበደላቸው የባሱ ሰዶማውያን እንኳ ነቢዩ እንዳለው «ከሰዶም ኃጢአት ይልቅ የወገኔ ሴት ልጅ ኃጢአት በዛች» /ሕዝ. 16÷45፣ሰቆ 4÷6/ በመላእክት ላይ በጭካኔ ተናገሩ፤ እነዚህ ግን በሁሉ አምላክና ንጉሥ በጌታችን ላይ በጭካኔ ተናገሩ:: እነዚህ ግን የመላእክትን ጌታ ለመግደል ደፈሩ፤ በእነርሱ የተገደለው ሕያው ክርስቶስ መሆኑን አላወቁምና::

## በጊዜያዊ የኃጢአት ሥራ ዘላለማዊውን ማጣት እንደማይገባ

እነዚያ በክርስቶስ ላይ ተንኰልን ያሰቡ አይሁድ ሞቱ፤ በእነዚህ ጊዜያዊ ነገሮች እጅግ ጥቂት ደስታ አድርገው ዘለዓለማዊ ከሆነው ግን ተጣሉ:: ሕያው የሆነው ቃልኪዳን ዘለዓለማዊ ለሆኑት ነገሮች ተስፋ እንጂ ጊዜያዊ ለሆነው ደስታ ክብር እንደሌለው ይህንን አያውቁም ነበር፤ በብዙ መከራ ድካምና ሐዘን ቅዱስ ሰው ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባልና::

በመከራ የተፈተነው ኢዮብ በኋላ የእግዚአብሔር ባለሟል እንደሆነው ቅዱስ ሰው ሐዘን ጭንቀት ሰቆቃ በደረሰበት ጊዜ በፊቱ ግን የደስታ ዕረፍት አለው:: ነገር ግን ጊዜያዊ ምግብ እንዳታለለው እንደ ዔሳው የሥጋን ደስታ በመውደድ ጥቂት ጊዜ የሚደሰቱ በኋላ የሐዘን ሕይወት ለዘለዓለም ይኖራቸዋል::

ለዚህም የእስራኤል ልጆችና የግብፅ ሰዎች ከግብፅ ያደረጉትን ጉዞ እንደ ምሳሌ እንውሰድ:: ለግብፃውያን በእስራኤል ላይ በሚያደርሱት በደል የሚያገኙት ጊዜያዊ ደስታ ነበር:: በኋላ ለመጓዝ በወጡ ጊዜ ግን ወደ ጥልቁ ወረዱ:: ለጊዜው በመከራ የተመቱትና የቆሰሉት ሕዝበ እግዚአብሔር ግን በአሠሪዎቻቸው ግፍ ምክንያት ከግብፅ በወጡ ጊዜ ባሕሩ ሳይጎዳቸው ቋሻገሩ:: ምድረ በዳውንም እንደምቹ

ሥፍራ ተጓዙበት፡፡ ምንም እንኳ ቦታው በሰው ያልተዘወተረ በረሃ ቢሆን በሕጉ የጸጋ ስጦታ በመላእክት ረድኤት እንደ በረሃ አልነበረም፡፡ ኤልያስም በምድረ በዳ ብቻውን እንደሆነ ባሰበ ጊዜ እርሱ ግን ከመላእክት ጋር ነበር፡፡ ሕዝቡም አስቀድሞ በምድረ በዳ ቢፈተንም ታምነው የተገኙ ጥቂቶች ብቻ ግን የቃል ኪዳኗን መሬት ወረሱ፡፡

በተመሳሳይ በዚህ ዓለም ጊዜያዊ መከራ የሚደርስባቸው በኋላ ይጽናናሉ፡፡ ዘለዓለማዊ ደስታን ይሳተፋሉ፡፡ እነዚያ በዚህ ዓለም መከራ የሚያደርሱ ግን በእግር ጫማ ሥር ይወድቃሉ፡፡ ወንጌል እንደሚያመለክተን ባዕለጸጋው በዚሁ ዓለም በደስታ ለጊዜው ቢኖርም በዚያኛው ዓለም ግን ተራበ፡፡ በዚህ አብዝቶ ቢጠግም በዚያ ግን በእጅጉ ተጠማ፡፡ አልዓዛር ግን ከዚህ ዓለም ነገሮች የተጎዳ ቢሆንም በሰማይ ግን ዕረፍት አገኘ፡፡ የበቆሎ ቂጣ ተርቦ የነበረ እርሱ በዚያ ግን ከመና የጣፈጠውን /የላቀውን/ ወደ ምድር የወረደው ጌታችን «ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ሰው ከዚህ እንጀ ራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል» ካለው እንጀራ ጠገበ፡፡ /ዮሐ. 6፥51/

የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ! ከጌዳታችን ደስታና መጽናናትን የምናገኝ ከሆነ ዕረፍትም ከድካም ከሆነ፣ ጤናም ከሕማም ከሆነ፣ ሕይወትም ከሞት ከሆነ እንግዲህ በሰዎች ሁሉ ላይ በሚያርፈው በጊዜያዊ ሕማማት መጨነቅ ተገቢ አይደለም፡፡ በእኛ ላይ በሚወድቅ ፈተና የምንዋደድ ልንሆን አይገባም፡፡ በመልካምነት ላይ የሚነሡ የክርስቶስ ተቀዋሚ የሆኑ ዝርተ ዐመፃ የሚነሡብንም ቢሆን መፍራት የሚገባ አይደለም፤ ይልቁንም አብልጠን በእነዚህ ነገሮች እግዚአብሔርን ማስደሰት፣ እነዚህንም ነገሮች በጽድቅ ሕይወት ውስጥ ለመመላለሳችን ብቃታችን እንደሚገለጥበት ፈተና ማሰብ ይገባል፡፡

**መከራን በመቀበል ክብርን ስለማግኘት**

እንግዲህ ሐዘንና ድካም ባይኖር ትዕግሥትን ስለምን እንፈልጋለን? ከጠላቶች የሚመጣ ጥቃት ከሌላ ምሽግስ እንዴት





ይፈተናል? የክርስቶስ ተቃዋሚ የሐሰት ክስ ሳይደርስ ጽኑ ስቃይ እንዴት ይታሰባል? የክፉውስ በደል አስቀድሞ ሳይገለጥ ሰው እንዴት ድንቅ ሥራን በዓይኖቹ ፊት ይዞ ይገኛል? ስለዚህ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን በእኛ ፊት መጣ፡፡ መከራ መቀበልን ለሰዎች አሳየ፡፡ ሲመቱት በትዕግሥት ተቀበለ፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፤ ሲጎዱት እነርሱን ግን አልጎዳም፡፡ ጀርባውን ለገራፊዎቹ ሰጠ፤ በጥፊ ለሚመቱ ጉንጮቹን ሰጠ፡፡ ከርኩስ ምራቃቸውም ፊቱን አልመለሰም፡ /1ኛ ጴጥ. 2፥23፣ ኢሳ. 50፥6/ በመጨረሻም ሕያውና ጻድቅ የሆነ እርሱ አርአያና ምሳሌውን እንይዝ ዘንድ በፈቃዱ ወደ ሞት ተመራ፡፡ ከእነዚህም ምሳሌዎች እኛ ራሳችንን እንማር ዘንድ፤ በእውነት እባቡንና ጊንጡን ሁሉ የጠላትንም ኃይል እንረግጥ ዘንድ ነው፡፡

ክርስቶስ መስሎ የኖረው ጳውሎስ እንዲህ አለን «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እናንተም እኔን ምሰሉ» አለ /1ኛ ቆሮ. 11፥1 / በዚህ መንገድ በዲያብሎስ ፈተና ላይ ሠለጠነበት፡፡ «ሞት ቢሆን ሕይወትም ቢሆን መላእክትም ቢሆኑ ግዛትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ኃይላትም ቢሆኑ ከፍታም ቢሆን ዝቅታም ቢሆን ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ» አለ /ሮሜ. 8፥38፣30/

ጠላት በመከራና በፈተና በድካምም በነገርም ሁሉ ሊያጠፋን ወደ እኛ ይቀርባል፡፡ በክርስቶስ ውስጥ ያለ ማንም ቢሆን ግን በተቃራኒ ያሉ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ይመክታል፡፡ መከራን በመቀበል፣ በየዋህነት በጽድቅ ሥራ ድልን ይቀዳጃል፡፡ «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» ይላል፡፡ አሁንም ዳግመኛ «በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን» ይላል፡፡ /ፊል. 4፥13፣ ሮሜ. 8፥37/ ይህ የጌታ ጸጋ ነው፡፡

እነዚህ ጌታ ሰዎችን የሚቀድስበት መንገዶች ናቸው፡፡ ስለእርሱ

መከራ የሚቀበሉትን ከመከራ የሚድኑበትን ነጻነት ለማዘጋጀት መከራ ተቀብሏልና፡፡ እኛን ከፍ ከፍ ያደርግ ዘንድ እርሱ ዝቅ ዝቅ አለ፡፡ እርሱ ያልተወለደውን መውደድ እንድንችል የመወለድን ፈተና ተቀበለ፡፡ ወደ ሙስና መቃብር ወረደ፤ ያ ሙስና መቃብር ግን ሕያውነትን የሚያለብስ ነው፡፡ ስለ እኛ ደካማ ሆነ፤ እኛ በኃይል እንነሣ ዘንድ ወደ ሞት ወረደ፤ በእኛ ላይ የሕያውነትን ጸጋ ሊለብስ፤ ለሙታንም ሕይወትን ይሰጥ ዘንድ፡፡ በመጨረሻም ሰው ሆነ እኛ እንደሰውነታችን የምንሞት ዳግም ሕያዋን እንሆን ዘንድ ያም ሞት ከእንግዲህ ዳግመኛ እንዳይገዛን፤ «በሕይወት እንደምንኖር እናምናለን» ብሎ የቅዱሳን ሐዋርያት ቃል እንደሚያውጀው፡፡ /ሮሜ. 6÷9/

**ስለመናፍቃን**

ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ባለማሰባቸው ምክንያት መንፈቀ አሪዮሳውያን የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ሆነዋል፡፡ ስለዚህ መናፍቃን እንደበታቸውን የሠራላቸውን ረዳታቸውን እርሱን ሰደቡት፡፡ ነጻ ያወጣቸውን እርሱን ሰደቡት፡፡ ሁሉንም ዓይነት እርሱን መድኀኒታችንን የሚቃወም ልዩ ልዩ ሐሳብ ይዘው ተገኙ፡፡

ስለሰው ልጅ ወደዚህ ዓለም ወርዶ በመምጣቱ ምክንያት የባሕርዩ አምላክነቱን ካዱ፡፡ ከድንግል ተወልዶ በዚህ ዓለም ስላዩት እርሱ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ተጠራጠሩ፡፡ በጊዜ የተወሰነ ሥጋዌም ያለው እንደሆነ በማሰብ ዘለዓለማዊነቱን ካዱ፡፡ ስለእኛ መከራ መቀበሉን በማየታቸው እርሱ ከሕያው አብ የተገኘ ሕያው ወልድ መሆኑን አላመኑም፡፡ በፍፃሜውም ስለ እኛ ሕማማትን በመታገሱ ምክንያት ዘለዓለማዊ ባሕርዩን የሚመለከቱ ነገሮችን ሁሉ ካዱ፤ የማያመሰግኑ መሆንን ፈቀዱ፡፡ መድኀኒታችንን ናቁ፡፡ ጸጋውን በማመስገን ፈንታ ስድብን አቀረቡለት፡፡

ስለዚህ ለእነሱ እነዚህ ቃላት ይገባቸዋል፡፡ አንተ የማታመሰግን የክርስቶስ ተቃዋሚ፣ ፍፁም ክፉ፣ የጌታው ገዳይ፣ በአእምሮ እውር የሆንክ፣ በሐሳብህ አይሁዳዊ የሆንክ ሆይ! መጻሕፍትን አታስተውልምን





«ብርሃንህንና እውነትህን ላክ» ያሉ ቅዱሳንንስ አትሰማምን? /መዝ. 43÷3/ ወይም ዳግመኛ «ፊትህንም አብራ እኛም እንድናለን» /መዝ. 80÷7/ የተባለውንስ ቃል ዘነጋህን? ጌታስ ስለ እኛ እንጂ ስለራሱ ወደዚህ ዓለም የመጣ አለመሆኑን አታውቅምን? በዚህም ምክንያት የርኅራኄ ፍቅሩን ባደነቅህ ነበር፡፡

አብስ ምን እንደሆነ ወልድስ ምን እንደሆነ ብታውቅ ወልድን ሊለወጥ የሚችል ባሕርይ እንዳለው አስበህ ባልሰደብከው ነበር፡፡ ለእኛ ያለውን የርኅራኄ ፍቅር ብታስተውል ኖሮ ወልድን ከአብ አትለየውም ነበር፡፡ እኛን ከአብ ጋር ያስታረቀ እርሱን እንግዳም አድርገህ አታስበውም ነበር፡፡

እነዚህ ቃላት ከክርስቶስ ጋር ለተጣሉት ብቻ ሳይሆን መለየትን ለወደዱም ከባድ እንደሆኑ አውቃለሁ፡፡ እነርሱ የርኅራኄ ስሜት እንዳላቸው ሰዎች በኅብረት አንድ ናቸውና፡፡ የማስመሰል ካባ አንግበው መታየት ተምረዋልና፡፡ የማይከፋፈለውን ወልድ ከአብ መለየታቸውን እንደ እንግዳ ትምህርት /ነገር/ አያስቡትም፡፡

እነዚህ ነገሮች በተነገሩ ጊዜ ካገበራቸው ከዲያብሎስ ጋር በእኛ ላይ ጥርሳቸውን እንደሚያፏጩ በእርግጥ አውቃለሁ፡፡ ቤዛ መድኀኒታችንን በተመለከተ ምስክር በሆንለት እውነተኛ ክብሩ ተጨንቀዋልና፡፡

ነገር ግን ጌታ በዲያብሎስ ላይ ዘወትር ይሳለቅበታል፤ እርሱ አሁንም በተመሳሳይ ደግሞ «እኔ በአብ አብም በእኔ» ይላል፡፡ /ዮሐ. 14÷11/ በአብ ውስጥ የሚገለጽ በእርሱም ውስጥ አብ የሚገለጽበት ጌታ ይህ ነው፡፡ በእውነት አማናዊ የአብ ልጅ የሆነ በመጨረሻም ስለ እኛ ሥጋን የተዋሐደ /ሰው የሆነ/ ስለእኛም ራሱን ለአብ የሰጠ በእርሱ መሥዋዕትና ቤዛነት ያዳነን እርሱ ነው፡፡ የቀደሙ ሕዝቦችን ከግብፅ ያወጣ፤ በኋላ እኛን ሁላችን ያዳነ፤ ይልቁንም የሰውን ዘር ሁሉ ከሞት ያዳነ፤ ከመቃብር ያወጣ እርሱ ነው፡፡

በቀደመው ዘመን እንደጠቦት በግ መሥዋዕት የነበረ፣ በጠቦቱም ይመሰል የነበረ፣ በኋላም «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና»

እንደተባለ ስለ እኛ የታረደ እርሱ ነው። ከአዳኞች ወጥመድ፣ ከክርስቶስ ተቃዋሚዎች፣ መለያየትን ከሚወዱ እኛን ያዳነን፣ ቤተ ክርስቲያኑን የጠበቀ እርሱ ነው። እንግዲህ አሁንም የሐሰት ሥራ ሰለባዎች ሆነናልና አሁንም እርሱ በራሱ ይታደገናል።

ወንድሞቼ ስለእነዚህ ነገሮች እኛ ምን ልናደርግ እንችላለን፧ የሁሉን አምላክ እግዚአብሔርን ማመስገንና እርሱንም ማወደስ ነው እንጂ። አስቀድመን በዳዊት የመዝሙር ቃል አድንቀን እንጮኽ «ለጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገን እግዚአብሔር ይባረክ» /መዝ. 124÷6/

**ስንብት**

በሰማይ ያለውን ታላቁን በዓል ከቅዱሳን መላእክት ጋር ሆነን እናከብር ዘንድ የትንሣኤን በዓል እርሱ ለእኛ መዳን እንደተጋ ሁሉ በዚያ መንገድ በትጋት እናክብር። ስለዚህ አስቀድሞ የእስራኤል ወገኖች ከመከራ ወጥተው ወደ ዕረፍት በደረሱ ጊዜ በዓልን አደረጉ፤ ላገኙት ድልም ውዳሴን አቀረቡ። መዝሙርን ዘመሩ። ለጊዜ ትንሣኤም የደረሱ ሕዝቦች ከሞት አዋጅ ነጻ ወጥተዋልና በዓልን ለጌታ ያደርጋሉ፤ ለጌታ ውለታ ምስጋናን ይመልሳሉ። የነበሩበት ሁኔታ ተለውጧልና ውዳሴን ለእርሱ ያቀርባሉ።

ስለዚህ ስእለታችንን ለእግዚአብሔር እናስገባ፤ ኃጢአታችንን እንናዘዝ፣ ያልተወንን፣ ያዳንን ጌታ በማመስገን በቃልም በመልካም ሥራም፣ በመንፈሳዊ ሕይወትም በዓልን ለጌታ እናድርግ /እንጠብቅ/። እኛ ለእናንተ፣ እናንተም ለእኛ በልማዳችን መሠረት ደብዳቤዎች ለመላክና ለመቀበል እንችል ዘንድ የክርስቶስ ጠላቶች ሆነው በግብር ከተሰለፉብን የታወቁ አሳቾች አወጣን። በምድረ በዳ ያለን ያህል አስቦ ስለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ብሎ ከብዙ ፈተናና መከራ አሳለፈን። ስለዚህ ነገር እኔ ራሴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እናንተም ከእኔ ጋር ስለ እኔ ታመሰግኑት ዘንድ አነሣሣችኋለሁ። ይህ የሐዋርያት ውርስ የሆነ ልማድ ይቆም ይጠፋ ዘንድ እነዚህ የክርስቶስ ጠላቶችና መለያየትን የሚወዱ ወገኖች ይመኙ ነበርና። እግዚአብሔር ግን





ይህ ይሆን ዘንድ አልፈቀደም። በሐዋርያት በኩል የተሰጠ የተጠበቀ ልማድ ነውና። በአባቶቻችን ትውፊትና ትእዛዝ መሠረት በዓሉን በአንድነትና በፍቅር እንጠብቅ ዘንድ ነው። ይህንን በአግባቡ አስበን ባከበርን ጊዜ በእርሱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለማዊ ሕይወት የተገባን ሆነን እንቆጠራለን።

በእርሱም ለአብ ክብር ኃይል ይገባል አሜን ወአሜን። እርስ በእርሳችሁ በተቀደሰ አሳሳም ሰላም ተባባሉ። በተቀደሰ ጸሎታችሁ አስቡን። ሁላችሁ ወንድሞቼ ሰላም እላችኋለሁ። ዘወትር አስባችኋለሁ። የተወደዳችሁም ከሁሉ አብልጠን የምንወዳችሁ ወንድሞቻችን ሆይ! ሰላምም እንድትሆኑ እጸልያለሁ።

# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ዐሥራ አንድ

## ፍጹም ስለሆነው ሰማያዊው ዓለም

ቅዱስ ጳውሎስ ጽድቅና ትሩፋትን ታጥቆ ይኖር ነበር። ያመኑትን ወደ ጌታ ይጠራ ነበር። የሚያውቀውም ስለራሱ አልነበ ረም። ስለመልካም ሥራና ስለምስጋና ነው እንጂ። በፍቅርና በጽድቅ መንገድ ስለመኖር ነው እንጂ። በየጊዜውም በእነዚህ ነገሮች ያድግ ነበር። ወደ ሰማያዊውም ሥፍራ ተነጠቀ። ወደ ገነትም ተወሰደ። የመላእክትንም ቋንቋ ሰማ። ከሰዎችም በላይ ለመሆን በቃ። በተመ ለሰም ጊዜ ለሰዎች ሁሉ እንዲህ ብሎ ሰበከ «ከዕውቀት ከፍለን እናውቃለን፤ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለን፤...ዛሬስ ከዕውቀት ከፍዬ አውቃለሁ፤ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ አውቃለሁ» /1ኛ ቆሮ. 13፥9፤12/ በእውነትም በሰማይ ባሉ ቅዱሳን ዘንድ ሁሉ እንደራሳቸው ዜጋ የታወቀ ነበርና። ወደፊት ከሚገለጸውና ፍጹም ከሆነው ጋር ሲነጻጸር በዚህ ዓለም ሳለ የሚያውቀው ከፊል ነበር። ለእነዚያ ግን ሳደረጋቸው በጌታ ለታመነባቸው ነገሮች ፍጹም ነበር።

እርሱ ራሱ «እንግዲህ ፍጹማን የሆን ሁላችን ይህን እናስብ» እንዳለው /ፊል. 3፥15/ ወንጌል በእስራኤል ሕግ ለተደገፈው አገልግሎት ፍጻሜና እውነት ነው። የወደፊቱም ነገር አሁን ያለው ነገር ፍጻሜ ይሆናል። ስለዚህ ወንጌልም ይፈጸማል፤ ያመኑትም ቅዱስ ጳውሎስ «የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግስት እንጠባበቃለን» ብሎ እንደተናገረው ተስፋ ያደረጉትን አሁን በዓይናቸው ያላዩትን ይቀበላሉ። /ሮሜ. 8፥24/ ይህ ብፁዕ ሰው ይህን መልክ ተላብሷል። ሐዋርያዊ ጸጋ ለእርሱ ሆኖለታል። «ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁ» ብሎ እንደተናገረ /1ኛ ቆሮ. 7፥7/ ጸጋው ድንቅ ነው።





እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ የእልፍ አእላፋት ኅብረት የሆነችው መንግሥተ ሰማያትም ታላቅ ናት። ምንም እንኳ ሰው በጠባቡና በቀጥተኛዋ መንገድ አልፎ የሚገባበት ብትሆንም ዛሬም ድረስ ከሌላም ሥፍራ ሁሉ የላቀ የሚገባበት ሊሰፈር ሊመጠን የማይቻል ሥፍራ አለው። ወራሾችና የዓይን ምስክሮች የሆኑ እነርሱ «ወደ ወጥመድ አገባኸን» በማለት እንደተናገሩት ከተቀበሉት መከራ ጋር ሲያነጻ ጽሩት «ወደ ዕረፍትም አወጣኸን» አሉ። ዳግመኛም «በጭንቀቴም አሰፋኸልኝ» አሉ። /መዝ 62፣ 41/

ወንድሞቼ እውነት እላችኋለሁ። የቅዱሳን መንገድ ጠባብ ናት፤ «መኖሪያዬ የራቀ እኔ ወዮልኝ» /መዝ. 120፥5/ እንዳለ ወደፊት የሚመጡትን በመናፈቅ ይታመማሉና። ወይም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች «እንደገና ስመጣ በእናንተ ዘንድ አምላኬ እንዲ ያዋርደኝ አስቀድመውም ኃጢአት ከሠሩትና ስላደረጉት ርኵሰትና ዝሙት መዳራትም ንስሐ ካልገቡት ወገን ስለብዙዎች ምናልባት አዝናለሁ ብዬ እፈራለሁ» /2ኛ ቆሮ. 12፥21/ ብሎ እንደጻፈውና ነቢዩ ሳሙኤል ለሳዖል ጥፋት እንዳዘነው ኤርምያስም ስለወገኖቹ ምርኮ እንዳለቀሰው ለሌሎች ሰዎች መዳንም ይጨነቃሉ ይተጋሉና። ነገር ግን ከእነዚህ መከራዎችና የሐዘን የሰቆቃ ወራት በኋላ ከዚህ ዓለም ሲለዩ ሰማያዊ መከራ ስቃይና ሰቆቃ የሌለበት ደስታ ሐሴት እርካታን ይቀበላሉ።

## የቅዱሳንን ቃል ስለማክበር

ወንድሞቼ እኛም እንግዲህ በእንዲህ ያለ ሁኔታ /ዐውድ ውስጥ ያለን ስለሆንን በጽድቅ መንገድ ላይ በምናደርገው ጉዞ እንዛል። እነሆ «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» ሲል መከሮ ናልና። /1ኛ ቆሮ. 11፥1/ ነገር ግን «በእውነትም የአሕዛብ አስተማሪ» ሆኗል። /1ኛ ጢሞ. 2፥7/ በእነርሱ በኩል እኛንም ሁሉ ገሰጸን እንጂ። በአጭሩ ለመናገር ለእያንዳንዳቸው የጻፈላቸው ቃል ለሰዎች ሁሉ

የተሰጠ ትእዝዝ ነው፡፡ ለሮሜ፣ ለኤፌሶን ሰዎችና ለፊልሞና በጻፈው መልእክቱ የተለያዩ ሰዎችን በተማጽኖ ሲመክር ነበርና፡፡ በገላትያና በቆሮንቶስ ሰዎች እንዳደረገው አንዳንዶችንም በቁጣ ሲገስጽ ነበር፡፡

የቆላስያስና የተሰሎንቄ ሰዎችንም መክሯል፡፡ የፊልጵስዩስ ሰዎችንም አመስግኗል፤ በእነርሱም ደስ ተሰኝቷል፡፡ ለዕብራውያንም ሕግ ለእነርሱ ጥላ እንደነበር አስተምሯል፡፡ የተመረጡ ልጆች ጢሞቴዎስና ቲቶ በሩቀ ጊዜ እንዲያስታውሱ አብረውት ባሉ ጊዜ ትእዛዛትን ሰጣቸው፡፡ እርሱ ለሁሉም ሰው ሁሉን ሆኖ ነበር፡፡ ራሱንም ፍጹም አድርጎ፤ በነገር ሁሉ ያድናቸው ዘንድ ትምህርቱንም ለእያንዳንዱ እንዲስማማ አድርጎ አቅርቧል፡፡ ስለዚህ ቃሉ ሁሉ ያለፍሬ አልነበረም፡፡ በሁሉም ቦታ እስከ አሁንም ድረስ ፍሬ ያፈራ ነበር እንጂ፡፡

እንግዲህ ወዳጆቼ የሐዋርያውን ሐሳብ /መንገድ/ እንፈልግ ዘንድ የሚገባ ነው፡፡ በመልእክቶቹ መጀመሪያ ብቻ ሳይሆን በመካከልና በመዝጊያዎቹም ' ጭምር ምክርና ተግሳጽን የያዙ ነበሩ፡፡ በእናንተ ጸሎት የዚህን ቅዱስ ሰው አሳብ /ዕቅድ/ በምንም ምክንያት ቢሆን ሳልዋሽ ማቅረቤን እንደምታምኑ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እርሱ በእነዚህ ሰማያዊ ነገሮች የተካነ ነበርና፡፡ የሰማያዊውንም ቃል ምስጢር /ኃይል/ ያውቅ ነበር፡፡ ስለክርስቶስ የሚናገረው ቃል ስለእርሱም ያለው ምስጢር ይገለጥ ዘንድ፣ ከዚያም ደግሞ የሰዎችን ምግባር ጠባይ ልምድ ለማረቅ፤ ጌታ ያዘዛቸውንም ትእዛዛት ይፈጽሙ ዘንድ መሻቱ ያድርባቸው ዘንድ ይተጋ ነበር፡፡

## ከቃሉም በፊት የቃሉን ባለቤት ስለማወቅ

ወደ ሕግጋት የሚያደርሰው መሪ ካልታወቀ ማንም ቢሆን እነርሱን ወደማክበር ሊደርስ አይችልም፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴም ይህንን ዘዴ /መንገድ/ ተጠቅሟል፡፡ ከእግዚአብሔር የተሰጡትን ትእዛዛት ባወጀ ጊዜ አስቀድሞ እግዚአብሔርን ስለማወቅ ተናግሯልና፡፡ «እስራኤል ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው»





አለ፡፡ /ዘዳ. 6፥4/ እርሱን አስቀድሞ ከገለጠላቸው በኋላ፣ በእርሱም መጠን እንደሚገባቸው ካስተማራቸው በኋላ፣ እርሱ እውነተኛው አምላክ መሆኑን ካሳሰባቸው በኋላ ሰው እርሱን ደስ የሚያሰኝበትን ሕግ «አታመንዝር፣ አትስረቅ» እያለ ከሌሎች ትእዛዛት ጋር መናገሩን አስከተለ፡፡

በሐዋርያት ትምህርት መሠረትም «ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋን እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋል» /ዕብ. 11፥6/ እንግዲህ እርሱን መፈለግ መልካም ሥራ ነው፡፡ ነቢዩ «እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ ጥሩት ክፉም ሰው መንገዱን በደለኛም ሰው አሳቡን ይተው» እንዳለው፡፡ /ኢሳ. 60፥6-7/

እንዲሁም ደግሞ ኖላዊ ዘሄርማስ «ከሁሉም ነገር በፊት እነዚህን ሁሉ ነገሮች የፈጠረና ያጸናውን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ አንድ አምላክ እግዚአብሔር እንዳለ እመን!» ባለው የምስክርነት ቃሉ ሰው ባይቆጣ መልካም ነው፡፡ ከዚያ አልፎ የጌታን ቃል የጻፉልን ብፁዓን ወንጌላውያን በወንጌል መግቢያ አስቀድመው ስለመድኀኒታችን ጻፉልን፡፡ የሆነውን ሁሉ በተረኩልን ጊዜ ቀድሞ ጌታ ፈጣሪ እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ እናምንም ዘንድ ነው፡፡

ይህ ካልሆነ አስቀድሞ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር የነበረውንና ሌሎችንም ዓይነ ሥውራን ያበራው፣ ሙታንን ያነሣው፣ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ የለወጠው፣ ለምጻሞችን ያነጻውን እርሱን ሊያምኑት እንዴት ይችላሉ? እርሱ ፈጣሪ መሆኑን «በመጀመሪያው ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሐ-ር ነበረ» /ዮሐ. 1፥1/ ብለው ባያስተምሩ ኖሮ፣ እንደ ማቴዎስም ከዳዊት ዘር የተወለደው እርሱ አማኑኤል የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ባያስተምሩ እርሱን አይሁድና አርዮሳውያን ፊታቸውን ያዞሩበትን ጌታ እኛ ባልተቀበልነው ባላመለክነውም ነበር፡፡

ስለዚህ ሐዋርያውም ከሁሉም ወገን መልእክት ሲልክ

እንደሚያደርገው ይልቁንም ለተወዳጅ የመንፈስ ልጁ እንዲህ ሲል መክሮታል፤ «አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር» /2ኛ ጢሞ. 3÷14፣ 2÷8/ እነዚህን ነገሮች መናገር ለእርሱ ተሰጥቶታል:: ዘወትርም ያስታውስ ዘንድ «ይህን አሰብ ይህንም አዘውትር» በማለት /1ኛ ጢሞ. 4÷15/ ጽፎለታል::

ለጽኑ የጸሎት ትጋት /ተመስጦ/ እና ሰማያዊውን ቃላት ለማዘከር፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ለማጠንከር፣ ተረት ያልሆነና የ ጸና እርሱን መውደድን ለማፍራት እንችል ዘንድ፣ ይህንንም እናስብ ዘንድ ስለራሳችንም ስለሌሎችም በድፍረት እንናገር ዘንድ «ከእግዚ አብሔር ፍቅር የሚለየን ማነው?» ልንል ይገባል /ሮሜ. 8÷35/:: እንዲህ የሚሆኑ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ጽኑ የማይናወጽ እምነት ከያዙ፣ አንድ ልብም ከሆኑ እንደ ጽዮን ተራራ፣ የጸኑ ናቸው:: እልፍ አእላፍ መከራና ቁጣ ቢደርስባቸው በጽኑ ዐለት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፤ እርሱም ክርስቶስ ነው::

ዝንጉዎች በእርሱ ደስ አይሰኙም፤ በተጨባጭ ካሉት ከዚህ ዓለም ኃላፊ ነገሮች ሌላ ለእነርሱ የተሻለ ክብር አይታያቸውም፤ ስለእምነት ነገር የተገነዘቡና የተረጋጉ አይደሉም:: «የዚህ ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል» /ማቴ. 13÷22/ ወይም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ እንዳስተማረው በተነገራቸው ቃል አምነው ለጊዜው ቢቆዩም አይጸኑምና በስደት ጊዜ ስለቃሉም መከራ በመጣ ጊዜ ይሰናከላሉና::

## የክፉዎች ፍፃሜ ጥፋት ስለመሆኑ

ክፉን የሚያስቡ በእምነት ሐሰተኞች ናቸው፤ የሚያስቡት ጽድቅንም አይደለም በደልን ነው እንጂ:: በምላሳቸውም ሐሰትን መናገር የለመዱ ናቸው:: ክፋውን ያደርጋሉ ቢጸጸቱ እንኳን ሥራቸውን አያቆሙም:: ደስታቸውን በክፉ ሥራ ውስጥ ወስነዋልና ባለመመለስ በዚያው ጸኑ:: ስለባልንጀሮቻቸው የተሰጣቸውንም ትእዛዛት ረጋገጡ፣





ቅዱሱ «መከራዬን የሚፈልጉ ከንቱን ተናገሩ» በማለት እንደመሰከረ /መዝ. 38÷12/ በመውደድም ፈንታ ክፉን ያደርጉባቸዋል::

የዚህ ሁሉ ክፉ አሳብ ምክንያት ቃሉን በበቂ ያለመረዳት፣ ለመረዳትም ያለመፈለግ ነው:: በምሳሌ መጽሐፍም «የአባቱን ትእዛዝ የሚረሳ ክፉውን ቃል ያስባል» ተብሏል:: እንዲህ ያለ አሳብ ክፉ በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ቃላት ይወቅሳል:: በሌሎችም ቃላት ይገስጻል:: «እጃችሁ በደም ጣታችሁም በበደል ረክሳለች ከንፈራ ችሁም ሐሰትን ተናግሯልም፤ ምላሳችሁም ኃጢአትን አሰምቷል፤ በ ጽድቅ የሚጠራ በእውነትም የሚፈርድ የለም፤ በምናምንቴ ነገር ታምነዋል፤ ሐሰትን ተናግረዋል ጉዳትን ጸንሰዋል፣ በደልንም ወልደዋል፤ የእባብን እንቁላል ቀፈቀፉ፤ የሸረሪትንም ድር አደሩ፤ እንቀቁላላቸውንም የሚበላ ሰው ይሞታል፣ እንቁላሉም ሲሰበር እፉኝት ይወጣል» /ኢሳ. 54÷3-4/::

የዚህ ዓይነቱን ክፉ አሳብ ፍፃሜም «ጽድቅም አላገኘንም፤ ብርሃንን በተስፋ እንጠባበቅ ነበር፤ እነሆም ጨለማ ሆነ፤ ጸዳልን በተስፋ እን ጠባበቅ ነበር፤ ነገር ግን በጨለማ ሔድን፤ እንደ እውሮች ወደ ቅጥሩ ተርመሰመስን፤ በቀትር ጊዜ በድግዝግዝታ እንዳለ ሰው ተሰናከልን፤ እንደ ሙታን በጨለማ ሥፍራ ነን፤ ሁላችን እንደ ድቦች እንጮኻለን» በማለት ይገልጻል:: /ኢሳ. 54÷5/

ይህ እንግዲህ የክፋት ፍሬ ነው፤ እንዲህ ያለው ዋጋ በዚሁ ልማድ ላሉት የሚሰጥ ነው፤ የስሕተት አካሔድ ለሚኖርበት ሰው የሚያተርፍለት ምንም የለውም:: ስሕተትን የሚቃወም ግን ራሱን ያቆማል:: የስሕተትን ሥራም አስወግዶ ይጥላል፤ ይቀብራቸዋልም:: እነዚህ ነገሮች ለሚኖርባቸው ለእርሱ ወዮለት «በሁለት በኩል ከተሳለ ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ይሆናልና» /ዕብ. 4÷12/ እንደ መዝሙረኛው ገለጻ እንደበታቸው «ጥርሳቸው ጦርና ፍላጻ አንደበታቸውም የተሳለ ሾተል ነው::» /መዝ. 67÷4/

የሚደንቀው ነገር ግን በሰው ላይ ክፉ የሚያስብን ሰው የሚጎዳው ምንም ነገር የለም፤ በራሱ ጦር ይወጋል እንጂ። ሌሎች ዘንድ ሳይደርሱ በራሳቸው ውስጥ ንዴትን፣ ቁጣን፣ ተንኮልን፣ ጥላቻን፣ መመረርን ይዘዋልና። ምንም እንኳን እነዚህን በሌሎች ላይ ማምጣት ባይችል፥ ተመልሰው በራሳቸው ላይ ይሆናሉና እንዲህ ሲል እንደ ጻለየው «ሰይፋቸው ወደ ልባቸው ይግባ» /መዝ. 37÷15/ ዳግመኛም በምሳሌ «በኃጠአቱ ገመድ ይታሰራል» እንደተባለ /ምሳ. 5÷22/

አይሁድ በአሳባቸው በጌታ ላይ ለመነሣት በተስማሙ ጊዜ በራሳቸው ላይ ቁጣ ሊያመጡ እንደሚችሉ ዘነጉ። ስለዚህ በቃሉ አዘነላቸው «አሕዛብ ለምን ያጉረመርማሉ? ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ» አለ። /መዝ. 2÷1/ በእርግጥም የአይሁድ አሳብ በሕያው ቃል ላይ ሞትን ሊያመጡ ማሰባቸው ከንቱ ነበር። በአብ ቃል ላይ ምክንያታዊ ያልሆነ ክፋትን አደረጉ። ታድያ እነርሱ በተበተኑ ጊዜ ከተማይቱም በጠፋች ጊዜ የተመለከተ ሰው «በራሳቸው ላይ ክፉን ነገር ሠርተዋልና ለነፍሳቸው ወዮ የሥራቸውን ፍሬ ይበላሉና፤ ጻድቁን መልካም ይሆንልሃል በሉት» የተባለባቸውን ቃል ሳያስታውስ አይቀርም /ኢሳ. 3÷9-10/።

ወንድሞች ሆይ! ታድያ ይህ እውነት አይደል? ስለ መጻሕፍት ሐሳብ በሳቱ ጊዜ «ጉድጓድ የሚምስ ይወድቅበታል፤ ቅጥርንም የሚያፈርስ እባብ ትነድፈዋለች» የሚለውን ቃል አላወቁም ነበርና። /መክ. 10÷8/ ፊታቸውን ከጌታ ባይመልሱ ኖሮ በመዝሙር የተጻፈውን «አሕዛብ በሠሩት ጉድጓድ ወደቁ፤ በዚያችም በሸሸጓት ወጥመድ እግራቸው ተጠመደች» የሚለውን ቃል በፈሩ ነበር። /መዝ. 9÷15/ እንግዲህ እንዴትም «የማያውቁት ጉድጓድ እንደሚቀርባቸው፣ የሸሸጉት ወጥመድ እንደሚይዛቸው» ይህን ያስተውሉ ዘንድ ይገባ ነበር፤ ነገር ግን እነዚህን ነገሮች አላስተዋሉም፤ እንዲሁ አድርገዋልና «ዐውቀውትስ ቢሆን የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር» /1ኛ ቆሮ. 2÷8/





## ቅዱሳን በእግዚአብሔር ኃያል ስለመሆናቸው

ስለዚህ የመንግሥተ ሰማያት ደቀ መዛሙርት የሆኑ፣ ከእርሷም የተነሣ የአሁኑንና የቀደመውን ነገሮች ሁሉ ያፈሩ /ያመጡ/፣ የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር በቤታቸው ተቀምጠው፣ ተኝተው ወይም ተነሥተው፣ በመንገድም እየሔዱ የሚያስቡ፣ «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሔደ፤ በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ፤ በዋዘኞች ወንበር ያልተቀመጠ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፤ ሕጉንም በቀንና ሌሊት ያስባል» ተብሎ ከተሰጣቸው /መዝ. 1÷1/ መንፈሳዊ ቃል ኪዳን የተነሣ በተስፋ የሚኖሩ ጻድቅና ታማኝ የጌታ አገልጋዮች በእምነት ላይ ተመሥርተዋል፤ በተስፋ ደስ ይሰኛሉ፤ በመንፈስ የተቃጠሉ ናቸው። «አፌ ጥበብን ይናገራል የልቤም ሐሳብ ማስተዋልን» ለማለት ደፋሮች ናቸው። ዳግመኛም «ሥራህን ሁሉ አሰላሰልሁ፤ የእጅህንም ሥራ ተመለከትሁ» እንዲሁም «በመኝታዬ አስብሃለሁ በማለዳም እናገርልሃለሁ» ይላሉ። /መዝ. 49÷3፣ መዝ. 148÷5፣ መዝ. 68÷6/። በእርሱ በአምላካቸው በእግዚአብሔር በደፋርነታቸው /በጀግንነታቸው/ ያይላሉ «አቤቱ ረድኤት መድኃኒቴም» ይሉታል /መዝ. 19÷14/።

ራሳቸውን ለሚመረምሩ ለእነዚያ ልባቸውንም ለእግዚአብሔር ላስገዙ የሚገዳደራቸው አንዳች ነገር አይኖርም። በርግጥም በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው እምነት ልባቸው ብርቱ ነው። « በእግዚአብሔር የታመኑ እንደማይታወኩ ለዘላለም እንደሚኖር እንደ ጽዮን ተራራ ናቸው» ተብሎ እንደተጻፈ። /መዝ. 125÷1/። አሳቾች በትዕቢት ዘወትር በድፍረት ቢነሡባቸው፣ የቅድስናቸውን መዓርግ ለመሻር /ለመደምሰስ/ ቢጥሩም፣ በወንድሞች መካከል መለያየትን ቢያመጡ በዚህም ጊዜ ውስጥ ሁሉ ግን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ነው። የሚበቀልላቸውም ብቻ አይደለም፤ የሚያድናቸውም ነው እንጂ። ይህ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ነው። «እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል እናንተ ዝም ትላላችሁ» ብሏልና። /ዘጸ. 14÷14/ ከዚያ

በኋላም /መከራና ፈተና ላያሸንፋቸው «በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ» ባሉት /ሮሜ. 12÷12/ በቅዱሳን ሐዋርያት ቃል መሠረት የክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ልማድ ሆኗል።

ሕግንም በማሰብ እነርሱን በሚገዳደሯቸው ነገሮች ሁሉ ላይ ይነሣሉ። እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛሉ። «መከራና ችግር አገኙኝ፤ ትእዛዛትህ ግን ተድላዬ ናቸው» ተብለው የተጻፉትን ቃላት ይናገራሉ። /መዝ. 119÷143/

## በሐሳብ ስለሚሠራ መልካም ሥራ አስፈላጊነት

ይሁን እንጂ በሥራቸው ብቻ አይደለም፤ ሰዎች በሐሳብም ወደ መልካም ሥራዎች ይጓዛሉ። ስለዚህም አስከትሎ «ቃልህን አስብ ዘንድ ዓይኖቼ ለመማለድ ቀደሙ» ይላል። /መዝ. 119÷148/። ለፍጹማን መንፈሳዊ ሐሳብ ከሥራቸው ይቀድማል። መድኀኒታችንም ስለ ሕግ ሲያስተምር ስለ ኀልዮ ትኩረት ሰጥቶ ተናግሯል «ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል» ብሏል። ጻግመኛም «በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል» አለ። /ማቴ. 5÷28-22/ ቁጣ በሌለበት መግደል አይኖርምና፤ የፍትወተ ሥጋ ሐሳብ በሌለበት የአመንዝራነት ክስ አይኖርምና።

ወዳጆቼ ሕግን ማሰብ በሕግም መመሰጥ አስፈላጊ ነው። «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ» ከመልካም ሥራም ጋር ባለማቋረጥ በልብ መጫወት /በሐሳብ መነጋገር/ ይገባዋል። /2ኛ ጢሞ. 3÷17/ ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በላከው መልእክት ወስጥ «ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው...» /1ኛ ጢሞ. 4÷7-8/ በማለት ለጽኑ የመልካም ሐሳብ ልምምድ ይጠራል፤ ይጋብዛል።

ወንድሞቼ የመልካም ሥራ ባለቤት ለክብር /ለውዳሴ/ የተገባ የሚሆን ሰው ነው። ይህንንም በጢሞቴዎስም በኩል ለሁሉም ተናገረ። ከመልካምነት አስበልጦ ሌላ ምንም ነገር ማሰብ እንደማይገባ





ከምንም ነገር በላይ በእግዚአብሔር ላይ ላለን እምነት ታላቁን ሥፍራ መስጠትን አመለከተን።

ትእዛዛትን በመጠበቅ የሚያስመስል ቢኖር እንኳ ለክፉ ሰው ምን ጸጋ /ክብር/ አለው? ይልቁንም ኃጥእ ሰው ከሕግም ከፍሎ እንኳ ሊያከብረው /ሊጠብቀው/ አይችልም። መልካም ሥራን የሚሻው አስቀድሞ በሐሳቡ የፈቀደ ነውና። መንፈስም እንዲህ ያለውን ሰው በሚገስጽበት ቃሉ «ሰነፍ በልቡ አምላክ የለም ይላል» ብሏል። ከዚያም አስከትሎ ከሐሳብ ጋር እንደሚጣመር ሲገልጽ «በልቡ» ብሏል /መዝ. 14÷1፣2/።

ክፉ ሰው /ኃጥእ/ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ያጠፋል፤ ይሰርቃል፣ ያመነዝራል፣ ይረግማል፣ ይሰክራል፣ እንዲህ ያሉትንም ሁሉ ያደርጋል። ነቢዩ ኤርምያስ ስለእነዚህ ነገሮች እስራኤልን ሲወቅስ «ሕዝቤን እተዋቸው ዘንድ ከእነርሱም እለይ ዘንድ በምድረ በዳ የመንገደኞች ማደሪያን ማን በሰጠኝ ምላሳቸውን ስለ ሐሰት እንደ ቀስት ገተሩ፤ በምድር በረቱ፤ ነገር ግን ለእውነት አይደለም፤ ከክፋት ወደ ክፋት ይሔዳሉና እኔንም አላወቁም» እያለ ይጮኽ ነበር። /ኤር. 9÷2/ በዚህም በክፋትና በሐሰት ከበደል ወደ በደል የሚራመዱትን ገስጿል። ነገር ግን እግዚአብሔርን አያውቁምና እምነት አልባ ናቸውና በበደለኛነት ይከሳቸዋል።

## ስለመልካም ሥራና እምነት

እምነትና መልካም ሥራ የተጣመሩ ናቸው፤ እኅትማማች ናቸው። በእርሱ የሚያምን መልካምን ያደርጋል። መልካምም ሰው የበለጠ ያምናል። ስለዚህ በክፋት ውስጥ ያለ ማንም ያለ ጥርጥር ከእምነት መንገድ ወጥቶ ይባዝናል። ከመልካም ሥራ የተጣለ ሰውም ከእውነተኛ እምነትም የተጣለ ይሆናል።

ቅዱስ ጳውሎስም ደቀ መዝሙሩን ሲመክር በዚሁ ነጥብ ላይ ምስክርነትን ሰጥቷል «ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍ ራቅ፤ ኃጢአተኛነታቸውን ከፊት ይልቅ ይጨምራሉና፤ ቃላቸውም እንደ

ጭንቁር ይባላል፤ ከእነርሱም ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ናቸው፣ እነዚህም ትንሣኤ ከአሁን በፊት ሆኗል፤ እያሉ ስለ እውነት ስተው የአጠንዳንዶችን እምነት ይገለብጣሉ» /2ኛ ጢሞ. 2÷16፣17/

መከራን የሚቀበል መልካምነትን አያቆምም፣ ስለዚህ እምነትን እንዲይዝ «አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር» እያለ ይመክራል፡፡ /2ኛ ጢሞ. 3÷14/ ወንድም ወንድሙን ሲረዳው አንዱ ለአንዱ የጸና ግንብ ይሆናሉ፡፡ እምነትና መልካም ሥራም እንዲሁ ተያይዘው ያድጋሉ፡፡ በአንዱ ውስጥ የሚኖር ማንም በሌላው የግድ ይጠነክራል፡፡ ስለዚህ ደቀ መዝሙር በመልካም ሥራ ውስጥ እስከ ፍፃሜው የሠለጠነ እንዲሆን ቢመኝ «መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል» እንደተባለ ለእምነትም ይጋደላል /1ኛ ጢሞ. 6÷12/፤ ለእውነተኛ አምላክ ይገዛል፡፡ ቀጥሎም በእምነት እውነተኛ አምላክን የሚቃወሙትን ለመቃወም በእምነት ይጋደላል፡፡

እነዚህ ያነሣናቸው ሁለት ነገሮች እምነትና መልካም ሥራ፣ ተስፋቸውም አንድ ነው፤ እርሱም ዘላለማዊ ሕይወት፤ እርሱ «መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል...በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘላለምን ሕይወት ያዝ» ብሏልና፤ ዳግመኛም «እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው...» አለ፡፡ /1ኛ ጢሞ. 4÷7፣8/

በዚህም ምክንያት መንፈቀ አሪዮሳውያንና ከቤተ ክርስቲያን የወጡ የክርስቶስ ጠላቶች የሆኑ እነርሱ ራሳቸው የሚገቡበትን ያለማመን ጉድጓድ ቆፍረዋል፡፡ በክፉት ሥራ እያደጉ የሚሔዱ ናቸውና «ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ» /ሮሜ. 16÷18/ የእግዚአብሔርንም ልጅ ይሰድባሉ፤ እርሱን ፍጡር እንደሆነ፣ ካልነበሩ ነገሮች የተገኘ እንደሆነ ይላሉና፡፡ እንግዲህ እነዚህ የሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ተከታዮች ናቸውና፡፡ ሐዋርያው ግን «ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል፤ ደግሞም የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዐመፅ ይራቅ የሚለው ማኅተም ያለበት የተደላደለ የእግዚአብሔር መሠረት ቆሟል »በማለት ከክፉታቸው እንድንጠበቅ አስጠንቅቋል፡፡ /2ኛ ጢሞ. 2÷19/





## ፋሲካን በመልካምነት ስለማክበር

ስለዚህ ሰው ሁሉ በዓልን በአግባቡ ያከብር ዘንድ ከክፉት ቢለይ መልካም ነው፣ ከበደልም ሥራ ሁሉ፡፡ ምክንያቱም በክፉ ሥራ የረከሰ ማንም ቢሆን ለአምላካችን ለእግዚአብሔር የፋሲካን መሥዋዕት ይሠዋ ዘንድ አይቻለውምና፡፡ ሕዝቡም በግብጽ ሳሉ በግብፅ ለአምላካቸው እንዲሠው ፈርዖን ቢያዝም «ለእግዚአብሔር ለአምላካችን የግጠብፃውያንን ርኵሰት እንሠዋለንና እንዲህ ይደረግ ዘንድ አይገባም » በማለት ሙሴ መመለሱን እናስብ፡፡ /ዘጸ. 8÷26/ ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ ከፈርዖን አገልጋዮች ይርቁ ዘንድ ፈቃዱ ነበር፡፡ ከብረቱም አጥር ከክፉትም ሁሉ ይርቁ ዘንድ፣ በጥንቃቄም እንግዳ ከሆኑ ሐሳቦች ይጠበቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ዕውቀት መልካምንም ሥራ ይቀበሉ ዘንድ፡፡ ስለዚህ እንዲህ አላቸው «ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ፤ ርኩስንም አትንኩ» /2ኛ ቆሮ. 6÷17/ ካልሆነ ግን ከኃጢአት ሊርቅ በመልካምም ሥራ ሊጸና አይችልምና፣ ነገር ግን በመልካም ሥራ በሠለጠነ ጊዜ በእምነትም ለመጽናት ይፈቅዳል፡፡ ከዚያም ቅዱስ ጳውሎስ መልካሙን ተጋድሎ ከተጋደለ በኋላ ጻድቅ ዳኛ የሚሰጠውን፣ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን እርሱን ለመሰሉ ሁሉ ያዘጋጀውን የጽድቅን አክሊል ያገኛል፡፡

ስለዚህ ይህ መልካም ሐሳብና በመልካም ሥራ የመሠልጠን ነገር የቅዱሳን ሁሉ የዘወትር ኑሮ ነው፡፡ ለእኛ ደግሞ በዚህ በበዓል ጊዜ እጅግ አስፈላጊ ነው፤ በዚህ ሰልፍ ውስጥ ከሆንን ከእነርሱ ጋር በዓልን እናደርግ ዘንድ ሰማያዊው ቃል ያዘናልና፡፡

ታድያ በዓል ከዚህ ሌላ ምንድነው? እግዚአብሔርን በጽናት ማምለክ፣ መልካም ሥራን ማወቅ፣ ልባዊ የሆነ የማያቋርጥ ጸሎት አይደለምን? ቅዱስ ጳውሎስም ከዚህ ሰልፍ እስከዘላለም እንዳንወጣ «ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ሳታቋርጡ ጸልዩ በሁሉ አመስግኑ» በማለት ያዘናል፡፡ /1ኛ ተሰ. 5÷16-18/፡፡

ነቢዩ «እግዚአብሔርን አመስግኑ ስሙንም ባርኩ፤ ዕለት ዕለትም ማዳኑን አውሩ» ሲል እንዳነሣሣንም በዓሉን ሳንለያይ በአንድነት በጋራ እናክብር። /መዝ. 95÷1/ ስለዚህ ለዚህ ሰማያዊ ጥሪ የሚዘገይ፣ ጥሪውን የማያከብርስ ማነው? ሁሉን ትተን ወደዚሁ ወደ በዓል ጉባኤ በፍጥነት ልንጓዝ የሚገባ አይደለምን? በአንድ ቦታ ብቻ የሚሆን አይደለም፣ በዓሉ በአንድ ቦታ የሚከበር አይደለምና። ነገር ግን «ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ» /መዝ. 19÷4/ መሥዋዕቱም በአንድ ሥፍራ አይቀርብም ነገር ግን «በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፤ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ» /ሚል. 1÷2/

ይህ ሁሉ በዚህ መንገድ በሁሉም ሥፍራ ሲከወን ምስጋናና ጸሎት ወደ ባዕለጸጋውና ወደ መልካሙ አባት ወደ እግዚአብሔር ያርጋል። ወንድሞቼ በሁሉም ሥፍራ ያሉት ኵላዊት ቤተ ክርስቲያን በደስታና በሐሴት ለእግዚአብሔርም በሚቀርብ በአንድ አምልኮ በዓሉን ስታከብር፤ ሁሉም ሰዎች በጋራ የምስጋና መዝሙርን ባቀረቡ ጊዜ፤ አሜን ባሉም ጊዜ በዓሉ እንዴት የተባረከ አይሆን! ታድያ በዚያን ጊዜ በሚገባ የሚጸልይ ማነው? በዚያ ጊዜ የተገዳዳሪዎች ሁሉ ቅጽር ይልቁንም የኢያሪኮ ግንብ ይፈርሳልና የመንፈስ ቅዱስም ጸጋ በሰዎች ሁሉ ላይ ይወርዳል፤ የመንፈስ ቅዱስም መምጣትን የተረዳ ሰው ሁሉ «በማለዳ ምሕረትህን እንጠግባለን፤ በዘመናችን ሁሉ ደስ ይለናል፤ ሐሴትም እናደርጋለን» ይላል /መዝ. 90÷14/።

**መከራን ከመታገሥ ጋር በዓልን ስለማክበር**

እንግዲህ ይህ ከሆነ ከቅዱሳን ጋር እንጩኸ፤ በተለይም በዚህ ጊዜ በአውሳብዮስ ተከታዮች በክፋት የሚደርስብንን መከራና ፈተና ከምንም ባለመቁጠር በዚህ ነገር ከእኛ አንዳችንም አንጣል /አንውደቅ/። አሁንም እንኳን በእግዚአብሔር ረድኤት ስለሚሆን መልካም ሥራ ሁሉ ሊያቆስሉን ይወዳሉና። በክሳቸውም ሞታችንን ለማቅረብ ይወዳሉ። ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች በመከራ ጊዜ ሁሉ አዳኛችን





እንደሆነ እናውቃለን።

አስቀድሞ ጌታችን «ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ፤ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፤ ሐሴትም አድርጉ» በማለት ቃልኪዳን ሰጥቶናልና። /ማቴ. 5÷11፣12/ ይህ የቤዛችን የራሱ ቃል ነው። መድኀኒታችን የደረሰበት መከራ ዳግም እርሱን በሚፈሩት በቅዱሳን ወገኖች ላይ አሁንም ይደርሳል እንጂ በዚህ ዓለም ባሉ በሰዎች ሁሉ የሚደርስ አይደለም። ስለዚህ ጠላቶቻችን ብዙ በገፉን ቁጥር ብዙ ነጻነት አለን። ምንም እንኳን ቢሰድቡንና ቢነቅፉን በአንድነት እንቁም። እነርሱ አብዝተው ከመልካም ሥራ በራቁ መጠን እኛ ደግሞ በታላቅ ድፍረት «ይህ ሁሉ በእኛ ላይ ደረሰ አልረሳንህም» እያልን እንስበክ /መዝ. 44÷17/። እንጂ ያንተን /የጌታን/ ህላዌ ካልነበሩ /በኋላ ከተፈጠሩ/ ጋር እንደሆን ከሚናገሩ ከአርዮሳውያንና ከማኒ ወገኖች ጋር በክፋት አንተባበርም። ከዘላለም እስከ ዘላለም ከአብ ጋር የነበረ ቃል ከእርሱ ከራሱ ከአብ ጋር ነበርና።

ወገኖቼ እንግዲህ በዓልን እናክብር። በመጨነቅና በማዘን አይደለም፣ ከመልካም ሥራ የተነሣ በመጡብን ጊዜያዊ ፈተናዎች ምክንያት ከመናፍቃን ጋር ኅብረት በመፍጠር አይደለም። ደስታና ሀሴታችንን የሚያበዛ የምስጋና መሥዋዕት በማቅረብ በዚያም በመሳተፍ ነው እንጂ። እንደ ቃየንም ልባችን እንዳያዝን፤ እንደ ታማኝና መልካም የእግዚአብሔር አገልጋይ «ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» የሚለውን የምሥራች ቃል እንሰማ ዘንድ /ማቴ 25÷21/።

አንዳንዶች እንደሚያስቡት ይህንን የበዓለ ትንሣኤ ዕለት የሐዘንና የሰቆቃ ልናደርገው አይገባም፤ በደስታና በሐሴት ተሞልተን በዓሉን ልናከብር ይገባል። ይህን በዓል የአይሁድን የሐሰት ትምህርት አስበን ወይም ወልድን ከመለኮታዊ ክብሩ የለዩ፣ ከፍጡራንም ጋር የቆጠሩትን የአርዮሳውያንኝ ትምህርት መሠረት አድርገን አይጠ

ደለም። ከእርሱ ከጌታ የተቀበልነውን እውነተኛ የሃይማኖት ትምህርት እየተመለከትን እንጂ። የአይሁድ ስላቅ የአርዮሳውያንም ወሰን የለሽ ድፍረት /ጭካኔ/ የሐዘን ስሜት ይከስታል እንጂ ምንም አያመጣምና። እነዚያ አይሁድ አስቀድመውም ጌታን ሰቅለውታልና፤ እነዚህ አርዮሳውያን ግን እርሱ ፈጣሪ አይደለም ፍጡር እንጂ ብለው አይሁድ ወደ እርሱ ያቀረቡለትን ሞት የማረከበትን መዓርግ ሊነሱት ወደዱ እንጂ። እርሱ ፍጡር ቢሆን ኖሮ በሞት በተያዘ ነበር። እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ግን እርሱ ፍጡር ሳይሆን የፍጡራን ሁሉ ጌታ ነው፤ የዚህም ሕያው በዓል ባለቤት።

በሞት ላይ የሠለጠነ ጌታ ሞትን አስወገደ፤ ጌታ ነውና ጌትነቱን አሳየ። እኛም ሁላችን ከሞት ወደ ሕይወት ተሸጋገርን። ነገር ግን የአይሁድና የተረፈ አይሁድ ሐሳብ ከንቱ ነው። ውጤቱ /ፍፃሜው/ እንደ ሐሳባቸው አልነበረምና። ለእነርሱ የሚያሳፍራቸው ሆነ «በሰማይ የሚኖር እርሱ ይሥቃል፤ ይሣለቅባቸዋል» /መዝ. 2÷4/።

መድኀኒታችንንም ወደፊት ይዘውት በተጓዙ ጊዜ እያለቀሱ ይከተሉት ለነበሩ ሴቶች «ለእኔ አታልቅሱ» በማለት ከለከላቸው። /ሉቃ. 22÷28/ በዚህም ይህ የክርስቶስ ሞት የሐዘን ሳይሆን የደስታ ሁኔታ ነውና ስለ እኛ የሞተው እርሱ ሕያው መሆኑን እናስተውል ዘንድ ነው። እርሱ ከባሕርይ አባቱ ከአብ የተወለደ እንጂ ከእነዚያ ካልነበሩ ነገሮች /ከተፈጠሩ/ ነገሮች ያስገኘ /የተገኘ/ አይደለምና።

በእርሱ በሞት ላይ የተገኘ የድል ምልክትን ልናይ ችለናል። በክርስቶስም ሥጋ የእኛን ሕያውነት እናያለን፦ እርሱ በታላቅ ኃይል ተነሥቷልና። የእኛ የሁላችን ትንሣኤም ይኖረናል። የእርሱን ሥጋ ሙስና መቃብር አላገኘውምና የእኛም አለመጥፋት አይጠረጠርም። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ወደ ሰው ሁሉ አለፈ፤ በጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ደግሞ እኛ ሁላችን እንነሣለን። እርሱ እንዳለው «ይህ የሚበሰብሰው





የማይበሰብሰውን ሊለብስ፤ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና» /1ኛ ቆሮ. 15÷53/

ይህ የሆነው ስለ እኛ በሞተበት በመከራው ጊዜ ነው። «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና» /1ኛ ቆሮ. 5÷7/ ስለዚህ እርሱ ታርዷልና እኛ እያንዳንዳችን እርሱን እንበላ ዘንድ ሥጋውንና ደሙን ሰጠን። በታላቅ ፈቃደኝነትና በትጋት የእርሱን የሕይወት መዓድ እንሳተፍ። በለጋስነት /ቸርነት/ ለሁሉ ተሰጥቷል፤ በእያንዳንዱም ውስጥ «ለዘላለማዊ ሕይወት የሚፈስ የውኃ ጉድጓድ» /ምንጭ/ ነው። /ዮሐ. 4÷14/

## ስንብት

እንግዲህ በዚህ የፋሲካ ጊዜ ጌታን ራሳችንን በመግዛት፣ ራሳችንንም በማንጻት እናገልግል። የጌታም ብርሃን በላያችን በርቷል። ጌታም የተነሣበት ቅድስቲቱ ቀን በላያችን ታንጸባርቃለች። በበዓለ ሃምሳ ለመልካም ሥራ በሚያነሣሣ ሐሴት ደስ ሊለን ይገባል። «እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህቺ ናት፤ ሐሴትን እናድርግ በእርሷም ደስ ይበለን» እያልን አብን እናክብር። /መዝ. 118÷24/ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ለአብ ክብርና ኃይል ይገባል ለዓለም ዓለም አሜን። እርስ በእርሳችሁ በተቀደሰ አሳሳም ሰላም ተባባሉ። ከእኔ ጋር ያሉ ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። ጤና ሁኑ፤ ተወዳጅ ወንድሞቼ ሆይ እጸልያለሁ።

# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቀጥር ዐሥራ ሦስት

## መከራን ስለመቀበል

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ በዓመታዊ ልማዳችን መሠረት የድኅነት በዓላችንን ላስታውሳችሁ ዝግጁ ነኝ። ምንም እንኳን የክርስቶስ ተቃዋሚዎች መከራና ሰቀቀንን ከእኛ ጋር ቢያደርሱባችሁም ከእኛ ጋር አንድ ሆነን በምንኖርበት ሃይማኖት አማካኝነት እግዚአብሔር አሁንም ገና ያጽናናችኋል። እነሆ ከሮም ሆኜም ቢሆን እንኳን እጽፍላችኋለሁና።

በዚህ /በሮም/ ሳለሁ ከወንድሞች ጋር በዓሉን እንደምናከብር ከእናንተም ጋር በመንፈስና በፈቃድ አንድ ሆነን እናከብራለን፤ እኛ ሁላችን ካለንበት ጸሎታችን ወደ እግዚአብሔር ይደርሳልና። የተ ጠራችሁት «ስለእርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ፤ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም» /ፊል.1÷29/። እኛ የተጨነቀን /የተቸገረን/ ቢሆንም እስከ አሁን ከእናንተ ጋር ነንና። እኛን ራሳችንን እንድናጽናና፣ ሌላውንም ለመልካም ነገር ለማነሣሣት መልእክት እንድንጽፍ ቀሰቀሰን። /ዕብ. 10÷24/ በርግጥም በቤተ ክርስቲያን ላይ ያነጣጠረው እጅግ ብዙ መከራ መራራ ስደትም በእኛም ላይ እየደረሰ ነውና።

መናፍቃን በአእምሮአቸው በእምነትም የሚደርስባቸው ፈተና የለም። ራሳቸው በእውነት ላይ ይነሣሉና። ቤተ ክርስቲያንንም በጽኑ ያሳድዳሉ። ወንድሞችንም ያሰቃያሉ። አንዳንዶች ተገርፈዋል፣ ሌሎች ተወግተዋል፣ ተቆርጠዋል። ጭካኔያቸው ከሁሉ የከፋ ነው፤ ስድብና ተሳልቆአቸው እስከ ጳጳሳትም ደርሷል።

ይሁን እንጂ እንዲህ ስለሆነ በዓላችንን ልንተው ልንዘነጋ አይገባም። ስለዚህ ከጊዜ ጊዜ እርሱን መዘከርን ሳንረሳ በዓላችንን ልንዘክር ይገባል። የማያምኑ ወገኖች በዓል እንዳለ አያስቡም፣ ምክንያቱም ሕይወታቸውን ሁሉ በሳቅ ስላቅ በፌዝ ያሳልፋልና።





የሚያከብሩትም በዓል የሐዘን እንጂ የእውነተኛ ደስታ በዓል አይደለም። ለእኛ ግን የአሁኑ በዓል ታላቅ ጊዜያችን ነው። የጸናና ወደ ሰማያት የሚያደርሰን መንገድ ነው።

እነዚህ ነገሮች የክርስቶስ ምርጥ አገልጋዮች፣ ቀናኢና የቅዱሳን ተከታዮች መሆናችን ይረጋገጥ ዘንድ እንደ ልምድ የሚያገለግሉ ናቸው። /ቆላ. 1÷12/ ለዚህም ኢዮብ «በምድር ላይ የሰው ሕይወቱ ብርቱ ሰልፍ አይደለምን?» /ኢዮ. 7÷1/ ብሏል። ይሁን እንጂ በዚህ ዓለም ሳለ በመከራ፣ በስቃይ በሰቀቀን እስከ ፍፃሜው በጽናት መሔዱ የተረጋገጠ እርሱ በነቢዩ «ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ፤ እፈትናለሁ» እንደተባለ /ኤር. 17÷10/ ከእግዚአብሔር የተዘጋጀላትን ዋጋ ይቀበላል።

እርሱ አስቀድሞ የሰውን ነገር ሁሉ ያውቅ የለምን? ነገር ግን እርሱ መልካምና ቸር በመሆኑ ምክንያት እያንዳንዱ ጻድቅ ይሆን ዘንድ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ዋጋው እንዲሰጠው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። ዳግመኛም ነቢዩ «ኩላሊትንና ልብን የምትመለከት» ብሏል። /ኤር. 20÷12/ በዚህም ምክንያት እያንዳንዳችንን ይፈትናል፤ አንድም ስለ ኢዮብ «አንተስ ጻድቅ ትሆን ዘንድ በእኔ ትፈርዳለህን» ተብሎ እንደተነገረው /ኢዮ 40÷8፣9/ ለሚያውቁት ለእነርሱ በመልካም ሥራ በጸደቁ /በጸኑ/ በእነርሱ የሚገለጥ ነው። ወይም ሰዎች ሥራቸው ምን እንደሆነ በተረዱ ጊዜ እነርሱ ማን እንደሆኑ ማወቅ ይችላሉ። አንድም ስለ ክፉ ሥራቸው ንስሐ ይገባሉ፤ ወይም መልካም እንደሆን በሃይማኖት ጸንቶ ይገኛል።

ቅዱስ ጳውሎስ በመከራ፣ በስደት፣ በረሃብ፣ በጥም በተጨነቀ ጊዜ «በሚወደን በእርሱ ከአሸናፊዎች ሁሉ እንበልጣለን» አለ፤ ዳግመኛም ስለ ክርስቶስ በድካም በመንገላታትም በችግርም በስደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛል፤ ስደክም ያንጊዜ ኃይለኛ ነኝና» /2ኛ ቆሮ. 12÷9/ ብሏል።

ሌሎችንም በእግዚአብሔር የሚተማመኑ ቅዱሳን ኢዮብ

«የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን» እያለ የፈተናውን ጊዜ እንደ ተቀበለ የመከራ ጊዜያቸውን በደስታ ይቀበላሉ:: /ኢዮ. 1÷21/ ነገር ግን መዝሙረኛው «አቤቱ ፍተነኝ መርምረኝም፤ ኩላሊቴንና ልቤን ፍትን» /መዝ. 26÷2/ ብሏል:: ስለዚህ ተፈትኖ ጥንካሬው ሲረጋገጥ ሰነፎችን ያሳምናል፤ የንጽሕናን ነገር ከሰማያዊው አምሳካዊ እሳት /ፈተና የተነሣ የሚገኘውን ጸጋ ይረዳሉ፤ እንደዚህ በፈተናዎች ምክንያት ተስፋ አይቆረጡም፤ በዚያ ነገር ደስ ይሰኛሉ እንጂ:: በሆኑት ነገሮች ሁሉ ፍጹም አይጎዱም:: ሕይወታቸው በእሳት እንደተፈተነ ወርቅ የበለጠ እያበራ ይታያል እንጂ:: «ልቤን ፈተንኸው በሌሊትም ጎበኘኸኝ ፈተንኸኝ ምንም አላገኘህብኝም፤ የሰውን ሥራ አፌ እንዳይናገር ፈቃዴ ነው» እንደተባለም /መዝ. 17÷3፣4/ በሥርዐት ትምህርት ቤት እንደተፈተነ ያለ ነው::

•ነገር ግን እነዚያ ሥራቸው በሕግ ያልታረቀ /ያልተገደበ/፣ ከመብላት፣ ከመጠጣትም ከመሞት ባሻገር የማያስቡ ሰዎች ፈተናን እንደ አደጋ ይቆጥሩታል:: በእምነት ያልተፈተኑ ይሆኑ ዘንድ በዚያም ይሰናከላሉ:: ለማይገባ አእምሮ ተሰጥተዋል:: ለይምሰል እንኳ መልካም ነገሮችን አያደርጉም /ሮሜ. 1÷28/::

ስለዚህ አስቀድሞም ራሱን የፈተነ እኛንም እንዲህ ባለ ልማድ እንድንመላለስ የሚያነቃቀን ቅዱስ ጳውሎስ «በድካም በመንገላታትም በችግርም በስደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛል፤...እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለመድ» ብሏል:: /2ኛ ቆሮ.12÷10፤ 1ኛ ጢሞ. 4÷7/ በመልካም ሥራ /በጽድቅ ሥራ/ ሊመላለሱ በሚወዱ፣ ተወዳጅ ደቀ መዛሙርት የሚደርሰውን መከራ ያውቃልና ወደ ፈተና እንዳይገቡ ተግተው እንዲጸልዩ ይነግራቸው ነበር:: በእነዚህ ነገሮች ልምድ /ዕውቀት/ ኣላቸውና ፈተና በመጣ ጊዜ ስደትም በተነሣ ጊዜ በምስጋና /በቀላሉ/ ሊቀበሉት ይቻላቸዋል::

ስለእነዚህ ነገሮች በልቡ የሚያመላልስ ማንም ቢሆን በቀላሉ





የተሰወረ ልባዊ ደስታን ገንዘብ ያደርጋል:: በዚህም መንገድ ቅዱሳን ሰማዕታት አስቀድመው ስለመከራ ሕይወት ያስባሉና በክርስቶስ ፍ ጹማን ይሆናሉ:: የሚመጣውን ዕረፍት እያሰቡ የሥጋን መከራ ይቀበላሉ::

ነገር ግን እነዚያ ሁሉ «ርስታቸውን በስማቸው ይጠራል » እና እንጨት፣ ሣርና አገዳ በሐሳባቸው ያላቸው /1ኛ ቆሮ. 3÷12/ ለመከራና ለጭንቀት እንግዶች የሆኑ እነዚያ ለመንግሥተ ሰማይም ባዕድ ይሆናሉ:: እንደማያሳፍር «መከራ ትዕግስትን እንዲያደርግ ትዕግስትም ፈተናን፤ ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ» የሚያውቁ ቢ ሆን ሳያፍሩ ይኖራሉ:: ዳግመኛም «ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ» ያለውን ቅዱስ ጳውሎስን ምሳሌ ወስደው ራሳቸውን በዚህ ውስጥ ባስለመዱ ነበር:: እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከጠላቶች የተነሣ የሆኑ ግርፋት ስድብ፣ ዘለፋ ቢሆኑም እንኳን የእግዚአብሔርን ርኅራኄ በሚያምኑ ላይ የሚያመጣው አንዳች ነገር የለም:: እነዚህ ነገሮች ጊዜያዊ ናቸውና ፈጥነን ከእነርሱ እንድናለን፤ እግዚአብሔር ግን ሁልጊዜም ቸር ባዕለ ጸጋ ነውና በሚወዱት ላይ ምሕረቱን /ርኅራኄውን/ ያፈሳል::

## በመከራ ስለሚገኝ ክብር

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ እነዚህን ጊዜያዊ ነገሮች ልንመለከት አይገባም፤ ትኩረታችንን ሁሉ ዘላለማዊ ነገሮች ላይ እናጸናለን:: ምንም እንኳን መከራ ቢመጣ ፍጻሜ ግን አለው፤ ዘለፋና ስደትም ይኖራል፤ ነገር ግን ለእኛ ካለን ተስፋ አንጻር ግን ምንም ናቸው:: ወደፊት ካለን ተስፋ ጋር ስናነጻጽራቸው አሁን ያለው ነገር ሁሉ ርባና ቢስ ነው:: /ሮሜ. 8÷18፣ 2ኛ ቆሮ. 4÷17/ ከመንግሥተ ሰማይ ጋር የሚነጻጸር ነገር ምንድነው? ከዘላለማዊ ሕይወት ጋር የሚነጻጸር ሌላ ምን አለ? ስለዚህ ወዳጆቼ ስደትና መከራን ማሰብ ተገቢ አይደለም፤ ስለተቀበልነው መከራ የተዘጋጀልንን ርስት እንጂ::

እነሆ የአባታችን የይሳኮርን ምሳሌ ከቅዱሳት መጻሕፍት ብንወስድ ሊያሳምነን ይችላል። «ይሳኮር አጥንተ ብርቱ አህያ ነው፤ በበጎች ጉረኖም መካከል ያርፋል፤ ዕረፍትም መልካም መሆኗን አየ፤ ምድሪቱም የለማች መሆኗን፤ ትከሻውን ለመሸከም ዝቅ አደረገ፤ በሥራም ገበሬ ሆነ» /ዘፍ. 49፥14/

በጫጉላ እንዳሉ ሙሽሮች በሰማያዊ ፍቅር የተያዘ እርሱ ከቅዱሳት መጻሕፍት በረከትን ይሰበስባል፤ አእምሮው በብሉይ ባረጀው ነገር ብቻ የተማረከ አይደለም፤ በሁለቱም ውርሶች ነው እንጂ። ክንፎቹንም እንዲዘረጋ በሩቅ በሰማይ ዕረፍትን ያደርጋል፤ ይህቺ ምድር እንኳ ያማሩ ሥራዎች ያሉባት ናት፤ የሰማይ ሀገራችንማ እንዴት የላቀው አይኖራት! አዲስና የማያረጅ ነው'ና። ይህቺ ምድር ስታልፍ ጌታ እንደተናገረ ቅዱሳንን ሊቀበል የተዘጋጀው ያኛው ዓለም ግን ሕያው ነው።

ይሳኮር ይህን ባስተዋለ ጊዜ በመከራው፣ በስቃዩ በመመካት መከራውን ሊሸከም ትከሻውን ዝቅ ዝቅ አደረገ። እርሱን ሊዘልፉት ከቀረቡት ጋር አልተከራከረም፤ በዘለፋቸውም አልታወከም። ነገር ግን እንደ ጽኑ ሰው በእነዚህ ነገሮች አሸናፊ ሆነ እንጂ፤ እጅግ አብልጦ ከልቡ ምድሩን /ርስቱን/ አረሰ እንጂ። ከእርሷም የበረከትን ፍሬ አገኘ። ፍሬን ያገኘ ዘንድ ይልቁንም መቶ እጥፍ ያገኝ ዘንድ ቃል ዘርን ዘራ፤ በትጋትም ፍሬውን ሰበሰበ።

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ይህ ማለት ምንድነው? ጠላቶች ፍላጻን በወነጨፉብን እኛም በመከራችን ልንከብር ይገባል። /ሮሜ. 5፥3/ በተሰደድን ጊዜም ተስፋ ልንቆርጥ አይገባም፤ ለመቺዎቻችን ሌላውን ጉንጭ ልንሰጥ ይገባል። ይልቁንም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የላይኛው /ከፍ ያለው/ አክሊል ሊጠራን አይገባምን? በተሰደብን ጊዜ አለመታወክ ለጠላቶቻችን ሌላውን ጉንጭ ልንሰጥ አይገባምን?

ደስታን ግን ለሚወዱ፣ ጠላትነትን ለሚያፈቅሩ ቅዱስ ያዕቆብ ሐ





ሐዋርያ «እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳበና ሲታለል ይፈተናል» እንዳለው የተፈተኑ ናቸው። /ያዕ. 1፥14/ ስለዚህ ስለ እውነት መከራ እንደምንቀበል እንወቅ። እነርሱ ጌታን የሚክዱት ግን ያሳድዱናል። የተወደዳችሁ ወንድሞቼ እንደ ሐዋርያው ያዕቆብ ቃል ይህንን ሁሉ «እንደ ደስታ ቁጠሩት።» «የእምነታችሁ መፈተን ትዕግስትን እንዲያደርግላችሁ አወቃችሁ» /ያዕ. 1፥2/ በዓሉን እንደምናከብር ሆነን ደስ ይበለን፤ መዳናችን በመከራችን ጊዜ የታዘዘ መሆኑን አታውቁምን። መድኀኒታችን ባለመሥራት ያዳነን አይደለም፤ ስለእኛ መከራን በመቀበል ሞትን አጠፋው እንጂ። ይህንንም ስለ እኛ ከመሆኑ በፊት አስቀድሞ «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ» አለን። /ዮሐ. 16፥33/ ይህን ስለሁሉም ሰው የተናገረው አይደለም በታማኝነትና በደስታ ለእርሱ መልካሙን አገልግሎት ለሚሰጡ ነው እንጂ። አስቀድሞም እንደሚታወቀው በእርሱ ፊት መልካም የሆኑ፣ የጽድቅ ሥራን የሚሠሩ ሁሉ ይሰደዳሉ።

«ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች እያሳቱና እየሳቱ በክፉት እየባሱ ይሔዳሉ» /2ኛ ጢሞ. 3፥13/ ስለዚህ ሕልም ፈቺዎችና እና ሐሰተኛ ነቢያት ምልክት ሰጪዎች፣ በወይን ሳይሆን በክፋታቸው ምክንያት ዕውቀት ያጡ ሰካሮች እንደ ካህን ሊያገለግሉ የሚሰለፉ ከሆነ፣ ክብራቸው በነውራቸው ከሆነ አትመኗቸው። እኛ ግን የተፈተንን ነንና ራሳችንን ዝቅ እናድርግ፤ በእነርሱም አንወሰድ።

ስለዚህም እግዚአብሔር በባርያው በሙሴ አማካኝነት ሕዝቡን ያስጠነቅቃል «በመካከልህም ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቢነሣ፤ ምልክት ተአምራትም ቢሰጥህ፤ እንደ ነገረህም ምልክቱ ወይም ተአምራቱ ቢፈጸም፤ እርሱም ሔደን የማታውቃቸውን ሌሎች አማልእክት እንከተል እናመልካቸውም ቢልህ አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ በፍጹም ነፍሳችሁ ትወዱት እንደሆነ ያወቅ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ነውና የዚያን

ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ አትስማ» /ዘዳ. 13÷1-3/ ስለዚህ እኛ በእነዚህ ነገሮች በተፈተንን ጊዜ ራሳችንን ከእግዚአብሔር ፍቅር እንለይ። ነገር ግን ወዳጆቼ በዓልን እናድርግ፤ እንደ መከራ ቀን አድርገን እንግለጠው። ሁልጊዜ በምንደክምለት በክርስቶስ የሆነ ደስታ እንጂ።

በበዓለ ፋሲካ መሥዋዕት የሆነውን እርሱን እናስብ፤ እርሱን እናከብራለንና። ምክንያቱም ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና። /1ኛ ቆሮ. 5÷7/ እርሱ ሕዝቡን ከግብጽ ያወጣ አሁን ደግሞ ሞትን የሞትንም ኃይል ዲያብሎስን አስወግዷልና። /ዕብ. 2÷14/ ወደ እፍረትም አደረሰው፤ ሌትና ቀን ወደ እግዚአብሔር ለሚጮኹ ለተጨነቁትም ረድኤትን ሰጠ /ሉቃ. 18÷7/።

## ስንብት

ስለዚህ ዘወትር እንዘምር፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከጠላቶቻችን ድነናልና። በእርሱም ለአብ ክብር ኃይል ዕዘዝ ይሁን። ለዓለም ዓለም አሜን። እርስ በእርሳችሁ በተቀደሰ ሰላምታ ሰላም ተባባሉ። ከእኔ ጋር ያሉት ሁሉም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። ተወዳጅ ወንድሞቼ በጌታ ጤና እንድትሆኑ እጸልያለሁ።





# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ዐሥራ አራት

## በዓሉ እግዚአብሔርን በመገዛት የምናመልክበት ስለመሆኑ

ወንድሞቼ የበዓላችን ደስታ ቀርቧል፤ ሊያከብሩት ለሚመኙ ሁሉ አይቀርም። ስለ እኛ ሁሉን የሆነ ዘወትር ከእኛ ጋር ሊሆን «እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ብሎ /ማቴ. 28÷20/ ቃል ኪዳንን የሰጠን አካላዊ ቃል እርሱም ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቧልና። እርሱ ለእኛ እረኞችን፣ ሊቀ ካህናችን፣ መንገድና ሕይወታችን በአንዴ ሁሉንም የሆነልን ነውና። ሐዋርያው «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና» እንዳለ /1ኛ ቆሮ. 5÷7/ እርሱ በዓላችንና የበዓል ቀናችን ሆኖ ይገለጣልና። የሚጠበቀው /ተስፋ ያደረግነው/ «ነፍሴን ከጭንቀት አድነኀታልና» ባለው /መዝ. 31÷7/ በመዝሙረኛው ጸሎት ላይ የሚያበራ ከክፉትም መዳኛ እርሱ እውነተኛ ደስታ እውነተኛም ፋሲካ ነው።

ቅዱሳንም በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በበዓል እንደሚደሰቱ ሰዎች ሆነው ኖረዋል። በሌሊት አንዴ ብቻ ሳይሆን ሰባት ጊዜያት እንደሚነሣ እንደ ክቡር ዳዊት በጸሎት ዕረፍትን ያገኛሉ። ሌላው ደግሞ በፈርዖንና በባለሟሎቹ ላይ ድል ባገኘ ጊዜ የምስጋና መዝሙር እንደዘመረ እንደሙሴ በምስጋና መዝሙር ክብርን ይሰጣል። ሌሎች ደግሞ ያንን የተጋድሎ አኗኗር ፈጽመው በሰማይ በዓልን የሚያደርጉ ናቸው። አስቀድመው በጥላው፣ እውነትንም በሚገልጡ ምሳሌያት የተማሩትን እንደ ታላቁ ሳሙኤል እና እንደ ኤልያስ በማያቋርጥ ትጋት አምልኮን ይፈጽማሉ።

እንግዲህ በዓሉን ስናከብር የምንረጨው ነገር ምንድን ነው? ወደዚህ በዓል የሚመራን የሚያንደረድረን ማነው? ወዳጆቼ ይህን ማድረግ ለሌላ ለማንም አይቻለው። እርሱ ከእኔ ጋር የተጠራችሁበት

«መንገድም እኔ ነኝ» ያለው በእነ ቅዱስ ዮሐንስ ምስክርነትም «የዓለምን ኃጢአት ያስወገደ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።» /ዮሐ. 14÷6፣1÷29/ ነቢዩ ኤርምያስ «በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ በእርሷም ላይ ሒዱ ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ» ብሎ የተናገረለት ነው /ኤር. 6÷16/።

እርሱም ነፍሶቻችንን አነጻ። በብሉይ ዘመን የኮርማዎች፣ የፍየሎች ደምና የጊደር አመድ በረከሱት ወገኖች ላይ ይረጭ ነበር። ሥጋንም ለማንጻት ይሆን ነበር። /ዕብ. 9÷13/ አሁን ግን በእግዚአብሔር ቃል ጸጋ ሰው ሁሉ ፍጹም ነጽቷል። ከእርሱም በኋላ እኛ በዚህ ያለን በላይኛይቱ ኢየሩሳሌም ቅጽር ላይ እንዳለን ሆነን ከዘለዓለማዊ ከዚህ በዓል አስቀድመን ቅዱሳን ሐዋርያት በአንድነት መሪያቸውን መድኀኔዓለምን እንደተከተሉ እኛም «ሁሉን ትተን ተከተልንህ» /ማር. 10÷28/ እያልን በዚያ ጸጋ መምህራን ሆንን።

**በዓሉ በመልካም ሥራ የሚገለጥ ስለመሆኑ**

ጌታን መከተል፣ የጌታም በዓል በእንደበት ብቻ የሚፈጸም አይደለም። በሥራም የሚገለጥ እንጂ፤ የታወጀም ሕግ ሁሉ ትእዛዛትም ሁሉ የራሱ የሚገለጥ ሥራ አለውና። ታላቁ ሙሴ በተቀደሱ በእነዚያ ሕጎች ሲመራ በገቡት ቃልኪዳን መሠረት መፈጸምን እንዳይዘነጉ፣ ቢዘነጉም እንደ ሐሰተኛ ይከሰሱ ዘንድ ከሕዝቡ ቃልኪዳንን ይቀበል ነበር። እነሱንም በመፈጸም እንዲያከብሩ ያደርግ ነበር /ዘጸ. 19÷8/።

በበዓለ ፋሲካ ክብርም ላይ የሚነሣ ጥያቄ የሚሰጥም መልስ የለም፤ እንድናከብር ቃሉ በተሰጠን ጊዜ ከዋኔውም አብሮ ይከተላል እንጂ፤ «የእስራኤልም ልጆች ሁሉ ፋሲካን ያከብራሉ» ተብሏልና። /ዘጸ. 12÷47/ ትእዛዛት አፈጻጸምን ያመለክታሉና ለዚህም ትእዛዝ የተዘጋጀ ክዋኔ /ግብር/ እንዳለው በማሰብ ነው። እነዚህን ነገሮች ስለ ማክበር፣ ለትእዛዛቱም ለመኖር ስለመትጋታችሁ እተማመንባችኋለሁ።





ይህን ነገር በጦማሮቻችን ሁሉ ሳንጠቅስ አላለፍንም።

አሁን ግን ከሁሉም ነገር በላይ አስፈላጊ ነው። ለእኔና ለእናንተ ማስታወስ የምሻው ነገር አለ። ይህ ትእዛዝ ያለ ዝግጅትና ኢ-ሃይማኖታዊ ሆኖ የመጣ አይደለም፤ ትምህርተ ሃይማኖታዊ እና የምስጢራት መነሻ ያለው በሃይማኖት ታሪክ ጽሑፎችም እንደምንረዳው «ይህ የፋሲካ ሕግ ነው ከእርሱ እንግዳ ሰው አይብላ፤... ያልተገረዘ ሁሉ ግን ከእርሱ አይብላ» /ዘጸ. 12÷43-18/ ተብሎ የታዘዘ ነው። በተገኘው ቦታና ቤት የሚበላ አይደለም፤ በፈርዖንና በባለማሎቹ እስራት ተይዘን ከማዘናችን ከማጉረምረማችን በፊት በፍጥነት እንዲሆን የታዘዘም ነው።

በቀደመው ጊዜ የእስራኤል ልጆች በዚህ መንገድ ባደጉ ጊዜ ስለ አማናዊው ስለዚህ በዓል ይደረግ የነበረውን ምሳሌውን ለመቀበል የተገቡ ነበሩ። አሁን ግን በዓሉ ምሳሌ አይደለም፤ አማናዊ ነው እንጂ። የአብ ቃል ጌታችንም ለቅዱሳን ሐዋርያቱ ስለዚህ ነገር «ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህን ፋሲካ ልበላ እጅግ እመኝ ነበር» አላቸው። /ሉቃ. 22÷15/ ይህ ድንቅ ቃል ነው፤ በዚያን ጊዜ የነበረ ሁሉ ቂጣን በፍጥነት ጋግሮ በልዩ ሥነ ሥርዐት ሊያሽብሽብ የመዝሙር ዕቃውን እና መጫሚያዎቹንም ያነሣል።

እነዚህ በቀደመው ዘመን የሆኑ ነገሮች ምሳሌዎች ነበሩ። አሁን ግን አማናዊው ወደ እኛ ደርሷል። «የማይታየው አምላክ» /ቆላ. 1÷15/ ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው ብርሃን፣ በዘንግም ፈንታ የእኛ በትረ መንግሥት የሆነ በቂጣ ምትክ /ፈንታ/ ከሰማይ የወረደ እንጀራ /ኅብስት/፣ በነጠላ መጫሚያዎች ምትክ በወንጌል ዝግጅት ያስጌጠን /ኤፌ. 6÷15/ በአጭሩ በእነዚህ ሁሉ ወደ አባቱ የመራን ነው።

ስለዚህ ጠላት መከራ ቢያደርስብን ቢያሳድደን እርሱ ግን ምሳሌው በሆነ በሙሴ ፈንታ አማናዊው እርሱ በተሻለ የቃሉ ኃይል

እንስጥ። እንግዲህ በውድድር ሜዳ እንደሚሮጡ በጸሎት በመትጋት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ፣ ለድሆች በመመጽወት፣ ከጠላቶቻችን ጋር ፍቅርን በመመሥረት ·/1ኛ ቆሮ. 9፥24-27/ ጾሙን እንቀድስ ዘንድ አንዳችን ከአንዳችን ጋር እንሽቀዳደም።

እኛም ሁላችን በአፍአ የተቡተንን እንሰብስብ፣ ትዕቢትን እናስወግድ፤ በሐሳባችን ትሑት ወደ መሆን እንመለስ፣ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም እንኑር፤ ወንድሞችን ለፍቅር እንነቃቃ። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስም በጾምና በትጋት በማስተዋል ለወንድሞች አርአያ ለመሆን የፈቀደ ነበር። ክቡር ዳዊትም በጾም ራሱን ዝቅ ዝቅ ያደርግ ነበር፤ በወኔም «አቤቱ አምላኬ እንዲህስ ካደረግሁ ዐመፃም በእጄ ቢኖር ክፉን ላደረጉብኝም ክፉን መልሼላቸው ቢሆን ጠላቶቼንም በከንቱ ገፍቼአቸው ቢሆን ጠላት ነፍሴን ያሳድዳት ያግኛትም» አለ። /ሮሜ. 9፥3፣ መዝ. 7፥3/ እኛም እንዲህ ብናደርግ ሞትን እንማርካለን፤ የመንግሥተ ሰማይንም በረከት /ጸጋ/ ገንዘብ እናደርጋለን።

### ስንብት

በዓሉን በመንፈስ እናክብረው፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱና ከእርሱ ጋር ለአብ ክብር እና ኃይል ይገባል ለዓለም ዓለም አሜን።





## መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ዐሥራ ዘጠኝ

### ስለ በዓሉ ታላቅነት

«የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ይባረክ» /ኤፌ. 1፥13/ ይህ የመግቢያ ቃል በተለይም በሐዋርያት ቃል ለጌታ ምስጋና በሚቀርብበት በዚህ ጊዜ ለመልእክቱ የሚስማማ ነው። ምክንያቱም እርሱ ከሩቅ አመጣን፤ የፋሲካን የበዓል ጠማር እንደልማዳችን ለእናንተም በግልጽ /በይፋ/ እንድንልክ አድሎናልና።

እንግዲህ ወዳጆቼ ይህ የበዓል ጊዜ ዳግመኛ በመለኮት የሚታወጅ አይደለም፤ ታሪክ እንደመዘገበው አንዴ የታወቀ ሆኗል እንጂ፤ ስለ እኛ መከራን በተቀበለ፣ በሞተ፣ ዳግመኛም ሞትን ድል አድርጎ በተነሣ በመድኀኒታችን ወደ እኛ ቀርቧል። ቅዱስ ጳውሎስ ሲሰብክ «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና» እንዳለው።

የፋሲካ በዓል የእኛ እንጂ የመጻተኞች አይደለም፤ ከእንግዲህ የአይሁድም አይደለም። የጥላዎች ዘመን አልፏልና፤ የቀደሙ ነገሮች ቀርተዋል፤ አሁን ሰው ሁሉ በዓልን ሊያደርግ የሚገባበት፣ «አምላክህ እግዚአብሔር በሌሊት ከግብፅ ስላወጣህ የአቢብን ወር ጠብቅ፤ የአምላክህንም የእግዚአብሔርን ፋሲካ አድርገበት» ያለውን እሱንም በማክበር የምንቆምበት /ዘዳ. 16፥1/ አዲስ ዘመን ቀርቧልና።

ሰነፎች እንኳ በዓልን በዓመት ያደርጋሉ፤ አይሁድም በግብዝነት ያንን ለማድረግ ያስመስላሉ። የሰነፎች በዓል ግን እንደ መከራ /የሐዘን/ እንጀራ ነው። ከአይሁድ በዓልም ፊቱን መልሷል «መባቻችሁንና በዓላቶቻችሁን ነፍሴ ጠልታለች፤ ሸክም ሆነውብኛል፤ ልታገሣቸው ደክሜያለሁ» ብሎ አስወግዶታልና። /ኢሳ. 1፥14/

ሕግን የሚጠብቁ መምሰል መልካም አይደለም፤ ምንም እንኳ ሕግን እንደፈጸሙ ቢሆኑም እያስመሰሉ በሚቀርቧቸው በእነዚያ በግብዝነት ሥራዎቻቸው ይከሰሳሉ። ስለዚህ ምንም እንኳ መሥዋዕት

ለማቅረብ ቢያስመስሉም አሁንም ገና «ይህን የመቅደሴን አደባባይ መርገጣችሁን የሚሻ ማነው?» ይላቸዋል።

እግዚአብሔር ከሰው ምንንም አይሻም፤ ለእርሱ ንጹሕ የሆነ ነገር የለምና። በነቢዩ ኢሳይያስ «ጠግቤያለሁ» ተብሎ እንደተመሰከረው /ኢሳ. 1፥2/ ከእነርሱ አንጻር ስለ እነሱ እርሱ ፍጹም ነው። አሁን ግን ስለ እነዚህ ነገሮች ሕዝቡን ለማስተማር ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች «እምነትም ሳይመጣ ይገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር፤ እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኗል» እንዳለው። /ገላ. 3፥23፣24/ የሚመጣውንም አስቀድሞ ለማወቅ፣ ለመሣል ሕግ ተሰጥቷል።

## የአይሁድ የፋሲካ በዓል ከንቱ ስለመሆኑ

አይሁድ ግን አያውቁም፤ አላስተዋሉምም፤ ስለዚህ በቀን ሳሉ በሌሊት እንደሚራመዱ /እንደሚጓዙ/ ሆኑ። በሕግ ያለውን እኛ የያዝነውን እውነት ሊነኩት ሊደርሱበት አልቻሉም። ለፊደል እንጂ ለመንፈስ አልተገዙምና። ሙሴ ፊቱን በጋረደላቸው ጊዜ እርሱን ተመለከቱ፤ ፊት ለፊት በግልጽ ባዩት ጊዜ ግን ፊታቸውን ከእርሱ መለሱ። የሚያነቡትን አያውቁትምና በስሕተት ሥራ ግን አንዱን ነገር ለሌላው ለወጡ /ተኩ/። ነቢዩ በእነርሱ ላይ «ሐሰትና አለማመን በእነርሱ ወስጥ ነው» ብሎ ጮኸ። ስለዚህ እግዚአብሔርም ስለእነርሱ «በጆሮ ሰምተው ተገዙልኝ፤ የባዕድ ልጆች ደለሉኝ» አለ። /መዝ. 18፥44፣45/

ጻግመኛም «ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር እርሱ ስለእኔ ጽፏልና» ብሎ እንዴት በታላቅነት እንደገሰጻቸው እናስተጠውል። /ዮሐ. 5፥46/

ነገር ግን እምነት የለሽ በመሆናቸው በሐሰት ወደ ሕግ ቀረቡ፤ መጻሕፍት በማወቅ ሳይሆን ከራሳቸው ምኞት በተነሣ ነገሮችን ይረዳሉ። ከዚያም አልፈው በመጻሕፍት ነጠላ ቃል ትርጉም ተደግፈው በግብዝነት ሕ





ይወት በማስመሰል ይመላለሳሉ። በዚህም ይተማመናሉ። ስለዚህ በእነርሱ ላይ ተቆጣ «ከእጃችሁ የሚሻ ማነው?» አለ። /ኢሳ. 1፥12/ እጅግ ደፋሮች ናቸውና በኤርምያስም «ለሌላ መሥዋዐታችሁ የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን ጨምሩ፤ ሥጋውንም ብሉ፤ ከግብፅ ምድር ባወጣኋችሁ ቀን ስለሚቃጠል መሥዋዕትና ስለሌላ መሥዋዕት ለአባቶቻችሁ አልተናገርሁምና» /ኤር. 7፥21፣22/ ሲል ገሰጻቸው። ተገቢውን አያደርጉምና ቅናታቸውም ከሕግ የተነሣ ሳይሆን ይልቁንም የራሳቸው ምኞት ከመሻት ነውና ነቢዩ ገሰጻቸው።

ነቢዩ እንደከሰሳቸው የእነርሱን ጠባቂዎቻቸውን መቱ፣ ከዐመፀኞችና ከጠበኞች ጋር ራሳቸውን ደመሩ፣ ትሑታኑን በጡጫና በእርግጫ አዋረዱ። ለራሳቸው ደስታና እርካታ ብቻ በማዘንበል ነገርን ሁሉ አደረጉ።

በዚህም ምክንያት እስከ ፍፃሜው ያለ በዓል መኖርን ቀጥለዋል፤ ምንም እንኳን ከቦታውና ከጊዜ ውጪ ሥጋ መብላት ቢያደርጉም በሕግ ከተናገረው ጠቦት ሌላ ለበዓል መሥዋዕትን ማድረግ ተምረዋል። በአማናዊው ቂጣ የሕይወት እንጀራ ፈንታ «ለሰማይ ንግሥት እንጎቻ እንዲያደርጉ ለሌሎችም አማልእክት የመጠጥ ቁርባን እንዲያፈሱ፤ ልጆች እንጨት ይሰበስባሉ፤ አባቶችም እሳት ያነድዳሉ፤ ሴቶችም ዱቄት ይለውሳሉ፤ እኔን ያስቆጣሉን? ይላል እግዚአብሔር» /ኤር. 7፥18/።

ፋሲካን እንደሚያከብሩ ይመስላሉ፤ ኤርምያስ ግን «ከይሁዳ ከተሞችና ከኢየሩሳሌም አደባባይ የእልልታን ድምፅና የደስታን ድምፅ፤ የወንድ ሙሽራን ድምፅና የሴት ሙሽራን ድምፅ አጠፋለሁ» እንዳለው /ኤር. 7፥34/ ደስታና ሐሴት ከእነርሱ አፍ ተወስዷል። ስለዚህ አሁን «በሬን የሚያርድልኝ ሰውን እንደሚገድል ነው፤ ጠቦትንም የሚሠዋ የውሻን አንገት እንደሚሰብር ነው፤ ቁርባን የሚያቀርብ የእርያን ደም እንደሚያቀርብ ነው፤ ዕጣንን የሚያጥን

ጣዖትን እንደሚባርክ ነው» /ኢሳ. 66፥3/ ብሏልና እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔርን አያስደስቱም። ስለዚህ «እነዚህ የገዛ መንገዳቸውን መረጡ፤ ነፍሳቸውም በርኵሰታቸው ደስ ይላታል» አላቸው። /ኢሳ. 66፥3/።

**የመሥዋዕት ሕጉ ጊዜያዊ ሆኖ ስለመኖሩ**

እንግዲህ ወንድሞቼ ይህ ማለት ምንድነው? ይልቁንም ሐሳባቸውን በሕግ ላይ በተቃርኖ ስላነሡ መናፍቃንም የነቢዩን ቃል ልንመረምር የሚገባ ነው። በሙሴም በኩል እግዚአብሔር የመ ሥዋዕትን ትእዛዝ ሰጠ። ዘሌዋውያን የተባለውም መጽሐፍ እነዚህን ነገሮች ሊያቀና የተሰጠ ነው። ስለዚህ በነቢያት በኩል እነዚህን ትእዛዛት የሚንቅን ሁሉ «ከእጃችሁ የሚሻ ማነው?» «ለሌላ መሥዋዕታችሁ የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን ጨምሩ፤ ሥጋውንም ብሉ፤ ከግብፅ ምድር ባወጣኋችሁ ቀን ስለሚቃጠል መሥዋዕትና ስለሌላ መሥዋዕት ለአባቶቻችሁ አልተናገርሁምና» በማለት ትእዛዙትን እንደማያከብሩ ዐማፅያን ከሰሰ። /ኢሳ. 1፥12፣ ኤር. 7፥22/። ስለዚህም አንዳንዶች መጻሕፍት እርስ በእርስ አይስማሙም ወይም ትእዛዛቱን የሰጠው እግዚአብሔር ሐሰተኛ ነው የማለት የራሳቸው አስተያየት መስጠት ጀመሩ። ነገር ግን አንዳች አለመስማማት የለም፤ እውነት የሆነው አብም አይዋሽም። ቅዱስ ጳውሎስ እንደመሰከረው «እግዚአብሔር ሊዋሽ የማይችል» ነውና። /ዕብ. 6፥18/። ነገር ግን በቅንነት ለሚያስቡ በእውነትም የሕግን ቃል ለተቀበሉ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግልጽ ናቸው።

እነሆ እግዚአብሔር ለእኔ እንደተገለጠ ለእናንተም ያድላችሁ፤ በእግዚአብሔር ረድኤት እነዚህ አሳቦችን አስቀድሜ ያነሣሁት ከእውነት እንዳይርቁ እንጂ አስቀድሞም ትእዛዙትና ሕጉ መሥዋዕትን የሚመለከት አይደለም። ሕጉን የሰጠው የእግዚአብሔርም ሐሳብ አይደለም። ስለ ተቃጠለ መሥዋዕትም አይደለም፤ በእነርሱ ተለይተው ስለታወቁ አስቀድመው ስለታዩት ነገሮች ነው እንጂ። «ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና »፤ «እነዚህ





እስከመታደስ ዘመን ድረስ የተደረጉ...» እንደተባለ። /ዕብ. 10፥1፣ 9፥10/።

ስለዚህ ሕግ ሁሉ መሥዋዕትን አይመለከትም። ምንም እንኳን መሥዋዕትን የሚመለከት ትእዛዝ በሕግ ውስጥ የነበረ ቢሆንም። በእነዚያም አማካኝነት ሰዎችን ለማስተማር ይጀመር ዘንድ፣ ከጣዖታትም መለየት ይቻል ዘንድ ወደ እግዚአብሔርም ማቅረብ ይቻል ዘንድ፣ ለዚያ ለነበረው ጊዜ ይማሩ ዘንድ ነው። ስለዚህ በመጀመሪያም ሕዝቡ ከግብፅ በወጣ ጊዜ ስለመሥዋዕትና ስለተቃጠለ መሥዋዕት አላዘዘም። ወደ ሲና ተራራም በደረሱ ጊዜ እንደዚያው። ስለእነዚህ ነገሮች ይጠነቀቅ ዘንድ እግዚአብሔር እንደሰው አይደለም፤ እውነተኛ አምላክ የሆነውን እርሱንና ቃሉን ያውቁ ዘንድ እነዚያን ሳይሆኑ ግን የሚመስሉ ሐሰተኛ አማልክትን ይንቁ ዘንድ ነው። ስለዚህ እነርሱን ከግብፅ በማውጣት ባሕረ ኤርትራን ለመሻገራቸው ምክንያት ሆኖ ለእነርሱ የታወቀ ሆነ።

ነገር ግን በኣልን/ጣዖትን/ ለያገለግሉ በመረጡ ጊዜ ህላዌ /ሕይወት/ ለሌላቸው ለእነርሱም መሥዋዕትን ሊያቀርቡ በደፈሩ ጊዜ ስለእነርሱ በግብፅ የሆኑትን ተአምራት ረስተው ዳግም ወደዚያ ለመመለስ ባሰቡ ጊዜ የመሥዋዕት ትእዛዛት ከሕጉ መሰጠት በኋላ እንደ ሕግ ተሾሙ።

በእነዚያ ባልሆኑት ምሳሌያዊ ነገሮች ተመስጠው /በተመስጦ/ ቆይተው በኋላ ወደ እውነተኛው ወደ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ይመለሱ ዘንድ ነው። አስቀድመው መሥዋዕትን አልተማሩም ፊታቸውን ከጣዖታት ይመልሱ ዘንድ እግዚአብሔር ባዘዘው ይጸኑ ዘንድ ነው እንጂ። «ለሌላ መሥዋዕታችሁ የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን ጨምሩ፤ ሥጋውንም ብሉ፤ ከግብፅ ምድር ባወጣኋችሁ ቀን ስለሚቃጠል መሥዋዕትና ስለሌላ መሥዋዕት ለአባቶቻችሁ አልተናገርሁም» ባለ ጊዜ ወዲያውም «ቃሌን ስሙ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ፤ ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ፤ መልካምም ይሆንላችሁ ዘንድ ባዘዝኋችሁ መንገድ

ሁሉ ሐዱ» የሚል ቃልን ጨምሮ ተናገረ። /ኤር. 7፥22፣23/ ስለዚህ ከመማርና ከመታዘዝ በፊት ከእግዚአብሔር ሌላ ማንንም እንዳያገለግሉ ተምረዋል። ወይፈኖች የመንጋው ጠቦትና ፍየሎች ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የማይሆኑበት የቀሳው ዘመን የሚያበቃበት ጊዜ መቼ እንደሆነና በፊታቸው ያለውን ጊዜ አለመርሳትን ወደ ማወቅ ደረሱ።

እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግን በፍጹም መንፈሳዊ አኳኋን ተፈጽመዋል። በጽኑ ጸሎትም። በአምላካዊ ቃላትም በመነጋገር። እንደ ዳዊት ዝማሬ «ቃሌ ለእርሱ ይጣፍጠው፤ እኔም በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል» እንዳለ /መዝ. 104፥34/፤ /መዝ. 141፥2/። በእርሱ ውስጥ ያለ መንፈስም «ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት ሠዋ፤ ለልዑልም ስእለትህን ስጥ» በማለት ስለታላቁ መሥዋዕት ያዛል። /መዝ. 50፥ 14፤ 45/

ታላቁ ነቢዩ ሳሙኤል «ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል» በማለት ሳኦልን በይፋ ገሰጸው /ነገ. 18፥17/ በዚህ ሳቢያ /ትእዛዛትን በመስማት/ ሰው ሕግን ይፈጽማል፤ «ምስጋናን የሚሠዋ ያከብረኛል» እንደተባለም እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል። ሰዎችም «ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትን አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ተማሩ።» /መዝ. 50፥23፤ ሆሴ 6፥6፤ ማቴ 9፥13/ በተገዳዳሪዎቹ አልፈርድም። ለማወቅ /ለማስተዋል/ የታወከ ለማወቅ አእምሯቸው የታወከ ሆኗልና፤ የሚነፍሱበትን አቅጣጫ ለወጡ፤ ወደ ስሕተት ተጓዙ። «አውቀውትስ ቢሆን የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበርና» /1ኛ ቆሮ. 2፥8/ ስለዚህ ፍፃሜያቸው ምንድነው? ነቢዩ አስቀድሞ ጮኸ «በራሳቸው ላይ ክፉን ነገር ሠርተዋልና ለነፍሳቸው ወዮ የሥራቸውን ፍሬ ይበላሉና፤ ጻድቁን መልካም ይሆንልሃል በሉት» /ኢሳ.3፥9፣10/ አለ።

ጌታችን «መጻሕፍትን አታውቁምና ትስታላችሁ» ብሎ እንደገሰጻቸው ለዚህ መጣላቸው ምክንያት ምንም አልነበረም፤ ስሕ





ተት እንጂ/ማቴ 22፥29/። ከተገሰጹም በኋላ እንኳ ወደ አእምሯቸው ሊመለሱ ሲገባቸው ይልቁንም በክፉት ንግግራቸው እየባሱ ሐደው «እኛ ግን የሙሴ ደቀመዛሙርት ነን፤ እግዚአብሔር ሙሴን እንደተናገረው እናውቃለን» በማለት ተናገሩ። /ዮሐ. 9፥28-29/ በዚህም ቃላቸው በሐሰት ይቀርቡና ራሳቸውንም ይከሱ ነበር። የሚሰሙትን እርሱን አምነው ቢሆን ኖሮ በሙሴ የተመሰከረለትን እርሱን ባመኑት ነበር። «በእውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህኔ» በተባለ ጊዜ /የሐዋ. 8፥30/ ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የምናገኘው በጃንደረባውስ ይህ የሆን አልነበረምን? እርሱ ግን ባለማወቁ አላፈረም፤ ይማርም ዘንድ ፈጥኖ ጠየቀ። ስለዚህ ለእርሱ ለመማር ለተዘጋጀው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተሰጠው፤ ባለማወቃቸው የጸኑ አይሁድ ግን በምሳሌ «ሞት ይምጣባቸው... የስንፍና ሐሳብ ኃጢአት ነው» ተብሎ /መዝ 55፥15፤ ምሳ. 24፥9/ እንደተናገረ ሆነባቸው።

**ስለመናፍቃን**

መናፍቃንም እንደ እነዚህ ናቸው፤ እውነትን ከመምረጥ የወደቁ ለራሳቸው ኢ-አማኒነትን የፈጠሩ ናቸው። «ሰነፍ በልቡ አምላክ የለም ይላል፤ በሥራቸው ረከሱ ጎሰቀሉ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም» /መዝ. 14:1/ ተባሉ። በሐሳባቸው ሰነፎች፣ በሥራቸው ክፉዎች ናቸው። «ክፉዎች ስትሆኑ መልካም ለመናገር እንዴት ትችላላችሁ» /ማቴ. 12፥34/ እንደተባለ ክፉዎች ናቸውና ክፋትን ያስባሉ። አእምሯቸው በማታለል የተሞላ እነርሱ እውነትን ማድረግ እንዴት ይቻላቸዋል? ለፍቅረ ንዋይ ያጎበደደ እርሱ እንዴት ይራራል? ሴትን ባየ ቁጥር ለፍትወተ ሥጋ በመመኘት የተያዘ እርሱ ንጽሕናን ጠብቆ እንዴት ይገኛል? «ከልብ ክፉ አሳብ መግደል ምንዝርነት ዝሙት መስረቅ በውሸት መመስከር ስድብ ይወጣልና » /ማቴ. 15፥19/።

ሰነፍ በባሕር ማዕበል እንደተመታ ሆኖ በእነዚህ ይጠፋል፤ በሥጋ ደስታቸው ተመርተውና ተስገብግበው ይጠፋሉ። «ሰነፍን የሚቀጥር ግን መንገድ አላፊውን እንደሚቀጥር ነው» ተብሎ ተጽፏልና።

/ምሳ. 26፥10/ ራሱን በዳንኪራ በሁከት ያስያዘ ነውና ሰሎሞን «ሰነፎችና ደንቆሮዎች በአንድነት እንዲጠፉ ገንዘባቸውንም ለሌሎች እንዲተዉ አይቶአል» እንዳለ ታውኮ ይጠፋል። /መዝ. 49፥10/

በእነርሱ መካከል የሚመራቸው የተስተካከለ አእምሮ ያለው አንድ እንኳ የለምና በእነዚህ ነገሮች ይሰቃያሉ። ጥበብ ባለበት ሁሉ ነፍስን የሚመራት ቃል አለ። «አስተዋይ መልካም ምክርን ገንዘቡ ያደርጋል» /ምሳ. 1፥5/ ነገር ግን መሪ የሌላቸው እነሱ እንደ ቅጠል ይረግፋሉ። ስለ ትንሣኤና ስለ እምነት ክፉ ሐሳብ የነበራቸው ሄሜኒዎስና ፊሳጦስ በማዕበሉ ተመተው አልወደቁምን?

ከሀዲው የአስቆሮቱ ይሁዳም ከመሪው ተለየ፤ ከአይሁድም ጋር ጠፋ። ደቀመዛሙርቱ ግን ጠቢባን ነበሩና ከጌታ ጋር ጸኑ፤ ምንም እንኳ ባሕሩ ቢናወጽ፣ መርከቧም በማዕበሉ ብትሸፈን፣ ነፋሱ ተገዳዳሪ ቢሆን አልወደቁም። ከእነርሱ ጋር ይጓዝ የነበረውን አካላዊ ቃልን ቀሰቀሱት። ወዲያውም በጌታው ትእዛዝ ባሕሩ ጸጥ አለ። እነርሱም ጸኑ። እነርሱም በዚያው ጊዜ መምህራንና ሰባክያን ሆኑ። ከመድኃኒታችን ተአምራት የተነሣ እነርሱን እንመስል ዘንድ አስተማሩን። እነዚህ ነገሮች እነርሱን የቀደሳቸውን ጌታ እናውቅ ዘንድ ስለእኛ ለእኛ ጥቅም ተጽፈዋል።

## ዓለም ማዕበል የተሞላች ባሕር ስለመሆኗ

እንግዲህ በደቀመዛሙርቱ እምነት ውስጥ እንሁን፤ ከጌታችን ጋር አዘውትረን መነጋገርን እናጽና። ዓለም ለእኛ እንደ ባሕር ነውና፤ ወንድሞቼ «ይህች ባሕር ታላቅና ሰፊ ናት፤ በዚያ ስፍር ቁጥር የሌለው ተንቀሳቃሽ ታላላቆችና ታናናሾች እንስሳት አሉ፤ በዚያ ላይ መርከቦች ይሔዳሉ፤ በዚያም ላይ የፈጠርኸው ዘንዶ ይጫወትበታል» ተብሎ እንደጻፈ /መዝ. 104፥25/ ከነፋስ ጋር ባለ በዚህ ባሕር ላይ በፈቃዳችን እየተንሳፈፍን ነው እያንዳንዱም ሰው እንደፈቃዱ ጉዞውን ይመራል።

ካልሆነም በእግዚአብሔር ቃል መሪነት ይመራል። ስለዚህ ዕረፍት





ያገኛል። ካልሆነም በሥጋ ደስታ ይያዛል። በማዕበሉ ይሰቃያል፤ በማዕበል ይመታል። እንግዲህ በውቅያኖስ ማዕበልና ንውጽውጽታ እንዳለ ሁሉ በዓለምም ብዙ መከራና ፈተና አለ። ስለዚህ የማያምኑ ጌታ እንዳለው «መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላሉ» /ማር. 4፥17/ በእምነት አይጸኑም። ስለዚህ በጊዜያዊ ነገሮች ሐሳቡ ተይዟልና ከመከራ የሚመነጭ ጭንቀትን ሊቋቋም አይችልም። ሰነፍ በድቡሽት ላይ እንደሠራው ያለዕውቀት ታንጿልና ጎርፍ በጎረፈ፣ ነፍሳት በነፈሱ ጊዜ እንደወደቀ በተፈተነ ጊዜ ይወድቃል።

በእምነት የጠነከሩ ቃሉን ያስተዋሉ ቅዱሳን ግን በፈተና አይደክሙም። ከጊዜ ጊዜ የታላላቅ ፈተናዎች ሁኔታ በእነርሱ ላይ ተለዋውጦ ቢመጣ ታምነው መኖርን ያጸናሉ። ከእነርሱ ጋር ያለ ጌታን ይቀሰቅሱታል፤ ይድናሉም። በእሳትም ይሁን በውኃ ውስጥ ቢያልፉ ሰላምና ዕረፍት ያገኛሉ በዓልንም ያደርጋሉ። ጸሎትን መሥዋዕት አድርገው ከምስጋና ጋር ለቤዛቸው ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ።

እንደ አብርሃም ተፈትነው ወይም እንደ ኢዮብ መከራን ተቀብለው ወይም እንደ ዮሴፍ ተጨቁነው በሐሰት ተከሰው በትዕግሥት የጸኑ ናቸው። የተሰደዱ ቢሆኑ በእግዚአብሔር የተጻፉ እነሱ አልተጣሉም። ወንድሞችን ከሚከፋፍሉ ከሚለያዩ ከእውነትም ከሚያርቁ፣ የክፋት «ቅጥርን ይዘላሉ» /መዝ. 18፥29/ በዚህ ሁኔታ ቅዱስ ጳውሎስ በስደት፣ በጭንቀት፣ ስድብ፣ በደል እየደረሰበት እንኳ ደስተኛ ነበር፤ እኛም ሁላችን እንዲሁ እንድንሆን «ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ በሁሉ አመስግኑ» በማለት መከረን። /1ኛ ተሰ. 5፥18/

## ስለበዓሉ አከባበር

ታድያ ለበዓሉ የሚገባው ከክፋት መመለስ፣ መልካም አኗኗር፣ ትጋት ያለማቋረጥ ከምስጋና ጋር ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ጸሎት አይደለምን? ስለዚህ ወንድሞቼ በሰማይ የሚሆን ዘለዓለማዊ ደስታን ወደ ማድረግ እንመልከት፤ በዚህም ሳለን በዓሉን እናክብር፤ በጊዜያቱ ሁሉ እንደሰት። በጸሎትና በነገር ሁሉ ለጌታ ምስጋናን እናቅርብ።

እኔም እግዚአብሔር ላደረጋቸው ሌሎችም ድንቅ ነገሮች ምስጋናን አቀርባለሁ። ላደረገልንም ረድኤት ሁሉ ከነበርንበት ሩቅ ሥፍራ አመጣን። ከምድር ዳርቻ ከእናንተም ጋር ዳግም አንድ አደረገን። በዓሉን ባሰብኩ ጊዜ ሁሉ የታላቁን የትንሣኤ በዓልን ለማብሰር እጓጓለሁ። እኛ ሁላችን በጋራ ፋሲካን እንበላ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም እንድንጓዝ፤ ተለያይተን አይደለም፤ በአገር ቤት። /ዘዳ. 12÷8፣9፣46/ የፋሲካ በግ በውኃ የራሰ እንደሆነ የእግዚአብሔርን ቃል በማውረድ፤ አጥንቱንም በመስበር የወንጌልን ቃል በማጥፋት አይደለም። በእሳት እንደበሰለ ከምሬትም ጋር እንደሆነ በመንፈስ የነቃን ሆነን፣ በማስተዋልና በጾም፣ በትሕትና ዝቅ ዝቅ ብለን፣ በጸጸትና በምስጋናና በዓሉን እናክብር።

ማንም አርባ ጾምን በቸልታ ያለፈ፣ የተቀደሱ ነገሮችን ያለ ንጽሕና የረገጠ በዓለ ትንሣኤውን ሊያከብር አይችልም። በተጨማሪም እርስ በእርሳችን እንተሳሰብ፤ ቸልተኛ እንዳንሆን አንዱ ሌላውን ያንቃው። በተለይ ጾሙን ልንጾም ይገባናል። ጾም በዓሉን በስኬት እንድንቀበለው፣ ጀምረንም በአግባቡ እንድንፈጽመው ይረዳናል። ከበዓሉም በኋላ ያሉትን ሰባት የተቀደሱ ሳምንታት አንዱን ከአንዱ ቀጥሎ እንጨምር። በዚያም እግዚአብሔርን እናመስግን እንደሰት። በእነዚህ ነገሮች አስቀድሞ በሰማይ ለእኛ የተዘጋጀ፣ በክርስቶስም በእውነት ለሚያምኑ ሁሉ ዘለዓለማዊ ደስታ ዕረፍት እንዳለን አሳውቆናልና።

### ስንብት

• በእርሱ ለአብ ለመንፈስ ቅዱስም ክብር ምስጋና ይገባል፤ ለዓለመ ዓለም አሜን። እርስ በእርሳችሁ በተቀደሰ ሰላምታ ሰላም ተባባሉ። ከእኔ ጋር ያሉ ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።





## መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ

### በዓሉን ለማክበር ስለመሰብሰብ

እንግዲህ ወንድሞቼ ጌታችን ለቅዱሳን ሐዋርያት ባሳሰበው መሠረት በዓሉን እናክብር። እርሱ አስቀድሞ አይሁድ ጌታን አሳልፈው የሚሰጡበትን ጊዜ «ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንዲሆን ታውቃላችሁ» ብሎ አሁንም ይነግረናልና። /ማቴ. 26÷2/ እኛ ግን ሞቱን እንደ በዓል እናከብረዋለን። ደስም እንሰኝበታለን። ተበትነን የነበርን እኛ ዕረፍት አግኝተንበታልና።

አሁን በአንድ ላይ ለመሰብሰብ ትጉሃን ነን፤ ቀድሞ ጠፍተን፣ ተበትነን የነበርነው ተገኝተናልና። እኛ በሩቅ ተጥለን የነበርን አሁን ቀረብን። እርሱ የተሰቃየ፣ በመስቀል ላይ የተቸነከረ፣ ነቢዩ እንደ ተናገረው በደላችንን የተሸከመ፣ ስለ እኛ ሕማማትን የተቀበለ ነውና። ከእኛም ሐዘን ስቃይና ሰቆቃን አስወገደ። በተጠማን ጊዜ እርሱ በበዓሉ ቀን ራሱ ቆሞ «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ» ብሎ እየጮኸ ያረካናል።

### ቅዱሳን ጌታን በመፈለግ የሚኖሩ ስለመሆናቸው

የቅዱሳንም የዘወትር ፍቅር የሚነሣው ከዚህ ነው። ለአንድ አፍታም የማይገታ ፍቅር የማይቋረጥ የጸና መሥዋዕትን ለጌታ ያቀርባሉ እንጂ። ዘወትር እርሱን ይጠማሉ፤ ክቡር ዳዊት «አምላኬ አምላኬ ወደ አንተ እገሰግሳለሁ። ነፍሴ አንተን ተጠማች፤ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች። እንጨትና ውኃ በሌለበት በምድረ በዳ» እንዳለውም ያጠጣቸው ዘንድ ይማጸኑታል። /መዝ. 63÷1፣2/ ነቢዩ ኢሳይያስም «ነፍሴ በሌሊት ትናፍቅሃለች» አለ። /ኢሳ. 26÷9/ ዳግመኛም «ነፍሴ ሁልጊዜ ፍርድህን ናፈቀች...፤ በፍርድህም ታምኛለሁና...፤ ሁልጊዜም ሕግህን እጠብቃለሁ» አለ። /መዝ. 119÷20፣43፣44/ አሁንም

ዳግመኛ «ዓይኖቼ ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ናቸው» አለ። በሌላም ሥፍራ እንዲህ ሲል ይጮኻል «የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን» /መዝ. 25÷15፣ 19÷14፡ ቅዱስ ጳውሎስም አክሎ «ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ ሳታቋርጡ ጸልዩ» በማለት መከረ /1ኛ ተሰ. 5÷17/

እነዚያ ዘወትር ታምነው ያሉት ጌታን ፍጹም ይጠብቁታል «እግዚአብሔርን እንከተል ወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን፤ እንደ ዝናብ ምድርን እንደሚያጠጣ እንደ መጨረሻ ዝናብ ይመጣል» እንደተባለ /ሆሴ. 6÷3/ በማለዳ የሚያረካቸው ብቻ አይደለም፣ እንደጠየቁት ያህል የሚጠጡትን የሚሰጣቸው ብቻ አይደለም፣ እንደተትረፈረፈ የርኅራኄ ፍቅሩ እጅግ አብዝቶ ዘወትር የመንፈ ስን ጸጋ ይሰጣቸዋል እንጂ። «በእኔ የሚያምን» ብሎ እንደ መጽሐ ፈ ምሳሌ ቃል ስለተጠሙት ነገር እርሱ ወዲያው አክሎ ይናገራል። /ዮሐ. 7÷38/ «የቀዘቀዘ ውሃ ለተጠማች ነፍስ ደስ እንደሚያሰኝ» ለእነዚያ በእግዚአብሔር ለሚያምኑ የመንፈስ መምጣት ከሁሉም ደስታና መታደስ ሁሉ የላቀ ነው። /ምሳ 25÷25/

በዚህ በፋሲካ ቀናትም ይህ በእኛም ይሆናል፤ ከቅዱሳን ጋር በማለዳ እንነሣ፤ እኛ አስቀድመን በጠጣን ጊዜ፣ ከእርሱ በሚመነጭ በእነዚህ መለኮታዊ ውኃዎች በተሞላን ጊዜ በሰማይ ከቅዱሳኑ ጋር በአንድ ማዕድ እንቀርብ ዘንድ በዚያ ያለ የደስታን ድምፅ የሕ ይወትን ቃል እንሰማ ዘንድ ከነፍስና ከሥጋ ንጽሕና ጋር በእምነትና በንስሐም ወደ ጌታ እንቅረብ።

**ኃጥአን ግን መልካምነትን የማይሹ ስለመሆናቸው**

ኃጥአን ግን ከዚህ የተጣሉ ናቸው «የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ» የሚለውንም ድምፅ /ቃል/ ይሰማሉ /ማቴ. 22÷12/ በእርግጥ ኃጥአን ይጠማሉ፤ የመንፈስን ጸጋ ግን አይደለም፤ እነርሱ በክፋት ነደዋል። በሥጋ ደስታ ፍጹም እሳት ውስጥ ተቀምጠዋል። መጽሐፈ ምሳሌ «ኃጥእ ቀኑን ሁሉ ምኞትን ይመኛል» እንዳለው /ምሳ. 21÷26/ ነቢዩም በእነርሱ ላይ እንዲህ እያለ ይጮኻል





«ስካርን ለመከተል በጥዋት ለሚማልዱ የወይን ጠጅም እስኪ ያቃጥላቸው እስከ ሌሊት ድረስ ለሚዘገዩ ወዮላቸው» /ኢሳ. 5÷11/ እንደ አውሬ ያደባሉ፤ የሌሎችን ጥፋትም ይጠማሉ።

አስቀድመውም የሐሰትና ያለመታመን ውኃን ጠጥተዋልና፤ በነቢዩ «ቁስሌስ ስለምን የማይፈወስ ሆነ? ስለምንስ አልሽርም አለ? በእውኑ እንደ ሐሰተኛ ምንጭ እንዳልታመነች ውኃ ትሆነኛለህን?» ተብሎ ተነግሮባቸዋል /ኤር. 15÷18/ ዳግመኛም ከባልንጀሮቻቸው ጋር በጠጡ ጊዜ ወደ ጥፋት ይመራሉ፤ መልካሙን አመል ያጠፋሉ። የዋሁንም ከመልካም ነገር ይለዩታል። ስለዚህ ነገርም ነቢዩ የጮኸው ምንድነው «ኃፍረተ ሥጋውን ለማየት ባልንጀራውን ለሚያጠጣ ክፉንም ለሚጨምርበት ለሚያሰክረውም ወዮለት!» በማለት ነው /ዕን. 2÷15/።

ነገር ግን እነዚያ እውነትን ያጠፋሉ፣ ይሰውሩታል። ልባቸ ውን ያቀዘቅዛሉ። እነዚህን ነገሮች አስቀድመው ጠጥተዋልና በመጽሐፈ ምሳሌ «የስርቆት ውኃ ይጣፍጣል የተሸሸገም እንጀራ ደስ ያሰኛል» እንደተባለ። እነርሱን ወደ ማለት ይሔዳሉ። /ምሳ. 9÷17/ በስውር እንክርዳድን ይዘራሉ፤ ምክንያቱም መልካሙን የማድረግ ነጻነት የላቸውም። በደጆች ላይ ራሷን የምታመሰግን በጎዳና ላይ የመናገር ነጻነት ያላት በሰገነትም ላይ የምትሰብክ የጥበብ ድፍረት የላቸው ምና /ምሳ. 8÷2/።

በእምነትና በሥጋ ደስታ መካከል ምርጫ ቢቀርብላቸው የእውነትን ጣፋጭነት ይሰርቃሉ /ይሰውራሉ/ የራሳቸውን መራራ ውኃ ግን በግልጽና በፍጥነት ከሚመጣባቸው ከክፋታቸው ክስ ያመልጡ ዘንድ እውነት አስመስለው ያቀርባሉ። ስለዚህም ለምድ የለበሰ ተኩላ በእብን በረድ /ኖራ/ ውጪው የተጌጠ የመቃብር ሐውልት ናቸው፤ ያም ሰይጣን ነው።

## መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ ሁለት

### ጌታችን ከምድር ከፍ ብሎ ስለመሰቀሉ

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእኛ ስለሁላችን የሞተው እጆቹን የዘረጋው የት ነው? ከምድር በታች ባለ ሥፍራ አይደለም። ከፍ ብሎ በአየር ላይ ነው እንጂ፤ በመስቀል ላይ የማዳኑ ሥራ በየሥፍራው ላሉ ለሁሉም ሰዎች /ወገኖች/ ይታይ /ይገለጥ/ ዘንድ፤ በአየር ላይ ይሠራ የነበረ ዲያብሎስን ያጠፋ ዘንድ፤ ወደ ሰማይ የሆነ መንገዳችንን ባርኮ ነጻ ያደርግልን ዘንድ ነው።

## መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ ሦስት

### ጠላት ስለመውደቁ

ግብፅን አቋርጠው በሔዱ በዚያን ጊዜ ጠላቶቻቸው የባሕር ሲሳይ ነበሩ። አሁን ግን ከምድር ወደ ሰማይ ስንሻገር ሰይጣን ራሱ እንደ መብረቅ ከሰማይ ይወድቃል።

## መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ ሰባት

### ጌታ መካር ስለመሆኑ

የእኛ ደስታና ትምክህት ማነው? ስለ እኛ መከራን የተቀበለው በእርሱ አብ የተገለጠበት /የታወቀበት/ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? እርሱ ሌላ አይደለም፤ አስቀድሞ በነቢያት የተናገረው ራሱ ነው እንጂ። አሁንም ሰዎችን ሁሉ «የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ» አለ፡ /ዮሐ. 4፥26/ ይህ ቃል እንዴት መልካም ነው፤





አንዴ ደግሞ አይናገርምና በሌላ ጊዜ ዝም ይላል። ነገር ግን ዘወትር በሁሉም ጊዜያት ከመጀመሪያም ጀምሮ ያለማቋረጥ ሰዎችን ሁሉ ያነሣሣል፤ ለእያንዳንዱም በልቡ ውስጥ ይናገረዋል።

## መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ ስምንት

### መንግሥቱን ለሚያምኑት ስለማዘጋጀቱ

እርሱ ለእኛ መሥዋዕት ስለሆነ በእውነት ቃሉ አደግን፤ የእርሱን ሕያው ቃለ ሃይማኖት ተሳተፍን፤ ከቅዱሳንም ጋር የመንግሥተ ሰማይን ደስታ እንቀበላለን። ደቀመዛሙርቱን በጠራበት በዚያ በሰገነት ከእነርሱ ጋር እኛን ሁላችንን ወደማይጠፋው ወደ ዘላለማዊው ግብዣ ጠራን። በዚህ ዓለም ስለ እኛ መከራን ተቀበለ፤ በዚያ ግን ጥሪውን ለሰሙ ለተቀበሉ፣ ከዓላማቸው ለደረሱ የታላቁን ጥሪያቸውን ሽልማት ለሚሹ ለግብዣው የሚታደሙበትን ሰማያዊቷን ድንኳን ያዘጋጃል። በዚያም ሰማያዊ አክሊልና የማይጠፋ ደስታ አለ። ምንም እንኳ እንደ ሰው ቃል ሲነገር የሚታደሙበት ጉዞ ድካም ከባድ ቢሆንም አሁንም ግን መድኀኒታችን ራሱ ቀላልና ምቹ ያደርገዋል።

ከመድኀኒታችን የወይንን አትክልት ሥፍራ የተቀበላችሁ ለሰማያዊ ግብዣ የተጠራችሁ ወንድሞቼ ሆይ! እንግዲህ በዓሉ ቀርቧልና ኃጢአትን ድል መንሣታችሁን የምታበስሩበትን የዘንባባ ዝንጣፊ ያዙ። በዚያም ሰማያዊ ሥርዐት ከመድኀኒታችን ጋር እንደሚገናኙ እንደ እነዚያ ቅዱሳን እንሁን፤ እርሱ በመጣ ጊዜ እንድንገናኘው ከእርሱም ጋር እንድንገባ ሕያው ማዕድን እንድንሳተፍ ከዚያም ለዘለዓለም በሰማያት እንድንኖር በሥራችን ሁሉ ራሳችንን እናዘጋጅ።

## መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር ሃያ ዘጠኝ

### ተአምራትን በአምላክነቱ ስለመፈጸሙ

ጌታችን በጀልባ ውስጥ ተኝቶ በነበረ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ፈተናቸው። በተለይም ክፋን ለማሳፈር በማሰብ በተአምራቱ ተነሥቶ ባሕሩን ገሰጸልና፣ ማዕበሉንም ጸጥ አድርጓልና። በዚህም ሁለት ነገሮችን በግልጽ አሳየ። የባሕሩ ማዕበል ከነፋሱ አልነበረም፣ ከእርሱ ላይ ሊራመድ የሚቻለውን ጌታ በመፍራት እንጂ። እንዲሁም እርሱን የገሰጸው ጌታ ፍጡር አለመሆኑ ተገልጧል። ፍጡር በባሕሪው ለሌላ ፍጡር በቃል የሚታዘዝ አይደለምና ይልቁንም የእርሱ ፈጣሪ መሆኑን ገለጸ።

ምንም እንኳ ባሕረ ኤርትራ በሙሴ ፊት የተከፈለ ቢሆን አሁንም ግን ሙሴ በባሕሪው ያደረገው አይደለም። እርሱ ስለተናገረ አይደለም፣ እግዚአብሔር ስላዘዘ ነው እንጂ። በገባዖን ፀሐይ፣ ጨረቃም በኤሎን ሸለቆ የቆመችው አሁንም በነዌ ልጅ ሥራ አይደለም፣ ጸሎቱን በተቀበለ በእግዚአብሔር እንጂ። ባሕሩን የገሰጸው በመስቀል ላይ ሳለ ፀሐዩን ያጨለመው ግን እርሱ የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው።

## ** ተቆንጽሎ የተገኘ **

### ሥጋችን ስለመክበሩ

ሰው ኅልፈት ያለበት መጨረሻ ያለው ቢሆንም እርሱ ሥጋው ቃል ግን ይህ የለበትም። በዚህም ምክንያት በሞት ተይዘን በነበረ ጊዜ ባሕርያችን ደካማ ሆኖ ሳለ እርሱ ግን አነሣን። ከምድርም ወደ ሰማይ መራን።





## ** ተቆንጽሎ የተገኘ **

### ቅዱሳን መካናትን የተነጠቁ አማኞችን ስለማጽናናት

እግዚአብሔር ያጽናናችሁ። በእርግጥ ይህ ነገር ብቻ እንደማያሳዝናችሁ አውቃለሁ። ሌሎች በኃይላቸው /በጉልበታቸው/ አብያተ ክርስቲያናትን ስለወሰዱ እናንተንም ከሥፍራችሁ አስወጥተው ስለጣሏችሁ እንጂ። አይሏችሁ እነሱ ቦታዎቻችሁን ይዘዋል፣ እናንተ ግን የቅዱሳን ሐዋርያትን ሃይማኖት ይዛችኋል። እርግጥ ነው እነርሱ በመካናቱ ቅጽር ይገኛሉ፣ ነገር ግን ከእውነተኛ ሃይማኖት ቅጽር ውጪ ናቸው። በእርግጥ እናንተ ከመካናቱ በአፍአ ውላችኋል፣ ሃይማኖት ግን በውስጣችሁ ነው፤ አስቡት ታላቁ ነገር የትኛው ነው። ሃይማኖት ወይስ መካናት? ሃይማኖት መሆኑ ግልጽ ነው፣ ታድያ የጎደለበት ማነው? የሞላለትስ ማነው? መካናትን የያዘው ወይስ ሃይማኖትን?

መካናት ቅዱስ የሚሆኑት የቅዱሳን ሐዋርያት ሃይማኖት በተሰበከባቸው ጊዜ ብቻ ነው፣ ቅዱስ የሚሆኑት አንዱ ቅዱስ /አምላካችን/ ሲያድርበት ብቻ ነው። እናንተ ግን ብፁዓን ናችሁ። አሁንም በያዛችሁት ሃይማኖት ምክንያት ያላችሁት በቤተ ክርስቲያን ነው። በሃይማኖትም መሠረት ላይ ትኖራላችሁ። ፍፁምም እርካታና የማይናወጽ ታላቅ እምነት በውስጣችሁ አላችሁ።

የቅዱሳን ሐዋርያት ውርስ /ትውፊት/ ወደ እናንተ ወርዷልና። የክፉዎች ቅናት ግን እንዲደጸና ይመኛል፣ ነገር ግን አይቻለውም። በአንጻሩ ይህን ባደረጉ ጊዜ ራሳቸው ተቆርጠው ይቀራሉና። «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ» ተብሎ እንደተጻፈ /ማቴ. 16፥16፣17/ ጴጥሮስ በእግዚአብሔር ረድኤት ተናገረ። «በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ» ያለውን ቃል እናስብ።

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ! ማንም በእምነታችሁ ላይ ሊሠለጥን ሊያይል አይችልም:: እግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናቱን እንዲመለሱ ፈቃዱ ይሁን፤ ባይመለሱም እንኳ እምነታችሁ ምሉዕ ነው:: እንግዲህ በመጻሕፍት ቃል ተመሥርቼ አጥብቄ እላችኋለሁ:: ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ተመለሱ:: አስታውሱ! ቤተ መቅደሱ በኢየሩሳሌም ነበር፤ የመቅደሱ ሥፍራ ግን ባዶ አልነበረም፤ ባዕዳን ወረሩት:: ቤተ መቅደሱ በኢየሩሳሌም ሳለ ግን እነርሱን ይፈትን ያቀናቸውም ዘንድ ስደት ወደ ባቢሎን እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ /ፍርድ/ ነበር::

በእነርሱ ድንቁርና ምክንያት ደም በጠማቸው ጠላቶቻቸው ተቀጡ:: በእርግጥም የመቅደስን ሥፍራ ባዕዳን ያዙት:: የሥፍራውን ባለቤት /ጌታ/ ግን አያውቁም ነበር:: ስለዚህ በዚያ ስፍራ ቢሆንም የሰጣቸው /መካን/ ለእነርሱ ምን ትርፍ ነበረው? እነሆ የቦታው ባለቤቶች የነበሩት እነዚያ በእነርሱ ተቀጡ:: ፍቅር የሆነ እግዚአብሔር ያ ቦታ የወንበዴዎች ዋሻ እንዲሆን ፈቀደ:: በአብደትም ሥራ በዚያ ሊገቡ የማይገባቸው እነርሱ ያንን የተቀደሰ ሥፍራ የንግድ የመገበያያ ሥፍራ አደረጉት::

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ! በዚህና ከዚህም በከፋ ምክንያት ከዚያ ከመጡት የሰማነው ነው:: ቤተ ክርስቲያንን የያዙ ይመስላቸዋል እንጂ በእውነት እላችኋለሁ፤ እጅግ በከፋ ሁኔታ ከቤተ ክርስቲያን የተጣሉ /የወጡ/ ናቸው:: ለእነርሱ ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ይመስላቸዋል፤ ነገር ግን የተሰደዱ ናቸው፤ በምርኮም ተይዘዋል:: ስለዚህ መካናቱን በመያዛቸው ብቻ መልካም የሆነላቸው ይመስላቸዋል::





# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ክቁጥር ሠላሳ ዘጠኝ ተቆንጽሎ የተገኘ

## ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት

እነርሱ የተፈጠሩ መጻሕፍት «የገበታ /የማዕድ/ መጻሕፍት» ብለው የሚጠሯቸው መጻሕፍት አሏቸው:: ኮከብን የሚቆጥሩባቸው ሆነው ሳሉ ለእነርሱ የቅዱሳንን ስም ይሰጣሉ:: በዚያ ውስጥ እውነት የሚሉትን ለጻፏቸው ለእነዚያ በራሳቸው ላይ መንታ ስድብ የሚያደርሱ ናቸው:: እነርሱ በዚያ በተናቀ የሰው የጥበብ ሐሳብና በማታለል የተካኑ የበቁ ናቸውና:: የማያውቁና የዋሃኑን ከእውነት፣ ከጸናው በእግዚአብሔርም ህላዌ ቀጥተኛ ከሆነው ሃይማኖት አስወጥተው ወደ ጥፋት ይጠሯቸዋል::

እንግዲህ መናፍቃን ሙታን እንደሆኑ ጠቀስንላችሁ:: እኛ ግን ለድኅነታችን አምላካውያት መጻሕፍትን ይዘናልና፤ ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንደጻፈው አንዳንድ የዋሃን ሌሎች አምላካውያት ያልሆኑ መጻሕፍትን በማንበብ ከንጽሕናቸው ከየዋሀነታቸው በአንዳንዶች ማታለያ እንዳይታለሉ እፈራለሁ:: ከእውነተኛዎቹ መጻሕፍት ጋር በስም ይመሳሰላሉና ወደ ጥፋት ያመራሉ:: ስለዚህ በትዕግሥት እንድትመላለሱ እለምናችኋለሁ:: ከእንግዲህ የምጽፍ ከሆነ ልታውቁት የሚገባውን ጉዳይ ሁሉ በማስታወስ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅምና ፍላጎት ተገድጄ እጽፍላችኋለሁ::

እነዚህን ነገሮች ለመጥቀስ ስነሣ ያደረግሁትን ለመግለጽ ቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ ያቀረበበትን መንገድ ወስጄ እኔም «የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን» እላለሁ:: /ሉቃ.1÷1/ አምላካውያት መሆናቸው ያልተረጋገጡ መጻሕፍትን ደረጃ ለመስጠት ከአምላካ ውያት መጻሕፍትም አዛምዶ ለማየት እኛንም ለማሳመን ቀድመው እንደነበሩት የዓይን ምስክሮችና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑ እነሱ ለአባቶች

እንዳስረከቡ እንዲሁ እኔም በእውነተኛ ወንድሞች ተነሣሥቼ በቀናና የተካተቱ አምላካውያት እንደሆኑ የተመሰከረላቸውና ከአባቶች የተቀበልናቸውን መጻሕፍት በፊታችሁ ዘርዝሬ ለማቅረብ መነሣቴ መልካም ይመስለኛል። በውጤቱም ወደ ጥፋት የተመራና ወደ ስሕተት የወደቀ ወደ ጥፋት የመሩትን ያወግዛል። በጽናት በንጽሕና መመላለሱን አጽንቶ የነበረ ደግሞ ዳግመኛ ደስ ይለኛል። እነዚህን ነገሮች ወደ ማጤን ያመጡታልና።

በብሉያት ውስጥ ሃያ ሁለት መጻሕፍት አሉ። እንደሰማሁትና በትውፊትም እንደደረሰን ስማቸውና አቀማመጣቸው የቀደም ተከተል ሥርዐታቸው እንደሚከተለው ነው። የመጀመሪያው ዘፍጥረት ነው፤ ከዚያም ዘጸአት ቀጥሎም ዘሌዋውያን ከዚያ በኋላ ዘኍልቁና ዘዳግም ይሆናሉ። ከእነዚህ በኋላ ኢያሱ መሳፍንትና ሩት በየተራ ይቀርባሉ። ከእነዚህ በኋላ ደግሞ አራቱ የነገሥታት መጻሕፍት በሁለት ተከፍለው ይቀርባሉ። የመጀመሪያውና ሁለተኛው እንደ አንድ መጽሐፍ፤ ሁለተኛውና ሦስተኛው እንደ ሌላ አንድ መጽሐፍ ይዘረዘራል። ከዚያም ቀዳማዊና ካልዓይ ዜና መዋዕልም እንደ አንድ መጽሐፍ ይታሰባሉ። በተመሳሳይ የዕዝራ አንደኛና ሁለተኛ መጽሐፍም እንደ አንድ ይወሰዳሉ። ከእነዚህ በኋላ መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፈ ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልየ ዘሰሎሞን ተከታትለው ይጠራሉ። ከዚያም ኢዮብ ተከትሎ የዐሥራ ሁለቱ የነቢያት መጻሕፍት እንደ አንድ ይታሰባሉ። ከዚያም ኢሳይያስ አንድ መጽሐፍ፣ ኤርምያስ ከባሮክ ጋር፣ ሰቆቃና መልእክት /epistle/ እንደ አንድ መጽሐፍ ከዚያም ሕዝቅኤል እና ዳንኤል እያንዳንዳቸው እንደ አንድ መጽሐፍ ናቸው። እስከ አሁን ያሉት ብሉያትን ይይዛሉ።

ዳግመኛም ስለሐዲሳት መጻሕፍት መናገርም የሚገባ ነው። እነዚህም አራቱ ወንጌላት የማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ/ ከዚያም የሐዋርያት ሥራ ተከትለውም መልእክታት ማለትም የሁሉም መልእክታት የሚባሉት፣ ከዚያም ሰባቱ ማለትም የያዕቆብ አንድ፣ የጴጥሮስ ሁለት፣





የዮሐንስ ሦስት፣ የይሁዳ አንድ ናቸው። ከዚያም ዐሥራ አራቱ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ማለትም ወደ ሮሜ፣ ሁለቱ ወደ ቆሮንቶስ፣ ወደ ገላትያ፣ ወደ ኤፌሶን፣ ወደ ፊልጵስዩስ፣ ወደ ቆላስያስ፣ ከእነዚህ በኋላ ሁለቱ ወደ ተሰሎንቄ ከዚያም ወደ ዕብራውያን ሰዎች ከዚያም ሁለቱ ወደ ጢሞቴዎስ፣ አንድ ወደ ቲቶና አንድ ወደ ፊልሞና የተጻፉ መልእክታት ናቸው። በተጨማሪም የዮሐንስ ራእይ አለ።

እነዚህ የድኅነት ምንጮች ናቸው። የተጠሙ ሁሉ ከጥማቸው በያዙት ሕያው ቃል ይረካሉ። መልካሙን ቃለ ሃይማኖት የያዙት መጻሕፍትም እነዚህ ናቸው። ማንም ቢሆን በእነዚህ ላይ አይጨምር፤ ከእነዚህም ላይ አይቀንስ። ስለዚህ ነገር ጌታችን ሰዱቃውያንን በተናገረ ጊዜ «መጻሕፍትን አታውቁምና ትስታላችሁ» አለ አይሁድንም «እነርሱን ትመረምራላችሁ እነርሱም ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው» በማለት ገስጻቸው። /ማቴ. 22፥29፤ ዮሐ. 5፥39/

ሌሎችም በተጨማሪ የሚነበቡ አስፈላጊ መጻሕፍት አሉ። በቀኖናው ያልተካተቱ በአባቶች ግን አዳዲስ አማንያን እንዲያነቧቸው የታዘዙ ለምክርና ለተግሳጽ የሚጠቅሙ ናቸው። የሰሎሞን ጥበብ፣ ሲራክ፣ አስቴር፣ ዮዲት፣ ጦቢት እንዲሁም ትምህርተ ሐዋርያትና ኖላዊ ዘሄርማስ ናቸው።

ወንድሞቼ የቀደሙት በቀኖናው የተካተቱ ናቸው፤ ቀሪዎቹ ግን እንዲነበቡ ብቻ የታዘዙ ናቸው። በእነዚህ ውስጥ መናፍቃን የሚጠቅሱዋቸው ሌሎች መጻሕፍት በዝርዝሩ የሉም። ስለዚህ የእነርሱ የፈጠራ ድርሰቶች ናቸው። ታድያ የመረጧቸውን መጻሕፍት ማን ጻፈላቸው? እነርሱ ግን ጥንታውያን ናቸው እያሉ የራሳቸውን ጊዜ ይሰጧቸዋል። ይህ ግን የዋሃንን ወደ ጥፋት የሚመሩበት ነው።

# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አርባ

## በንጽሕና በመዘጋጀት ለመንግሥቱ ስለመታደም

«እናንተ በፈተናዎቼ ከእኔ ጋር ጸንታችሁ የኖራችሁ ናችሁ፤ አባቴ እኔን እንደሾመኝ እኔ ደግሞ በመንግሥቴ ከማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ በዐሥራ ሁለቱም በእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በዙፋኖች ትቀመጡ ዘንድ ለመንግሥት እሾማችኋለሁ» /ሉቃ. 22፥28-30/ እንግዲህ በተዘጋጀው በዚያ ሰገነት ለታላቅ ሰማያዊ እራት የተጠራን ሆንን:: ስለዚህ «ራሳችንን እናንጻ» ሐዋርያው እንዳነሣሣን «በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ» ተጠብቀን በውስጥና በአፍአ እንከን የለሽ ንጹሕ እንሁን /2ኛ ቆሮ. 7፥1/:: በአፍአ ራስን መግዛትን እውነተኛነትን በመልበስ፤ በውስጥም በመንፈስና የእውነትን ቃል በማስተዋል «ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» የሚለውን ድምፁን እንሰማለን /ማቴ. 25፥21/::

# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አርባ ሁለት

## ለፋሲካ ማዕድ ስለመጠራት

ወንድሞቼ ለፍጥረት ሁሉ ወደሚበቃ ወደ ታላቁና ሰማያዊው ራት ማለቴ ክርስቶስ ወደ ተሠዋበት /ወደታረደበት/ ወደ ፋሲካ ወንጌላዊ በሆነችው መጽሐፈ ምሳሌ መሠረት ጥበብ በጋራ ጠርታናለች:: «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና» እንግዲህ እነዚያ ለዚህ ጥሪ የተዘጋጁት «ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» የሚለውን ቃሉን ይሰማሉ:: /ማቴ. 25፥21/





# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አርባ ሦስት

## መድኀኒታችን የገነትን ደጅ እንደከፈተልን

እንግዲህ ፋሲካው የእኛ ነው ጥሪውም ከላይ ነው፤ «እኛ አገራችን በሰማይ ነውና» ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለ /ፊል. 3፥20/ «በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን» ከእንግዲህ ወደፊት እንመልከት፤ በዓሉን በአግባቡ እናክብር በእውነት መንግሥተ ሰማይ ታላቅ ናት:: ርቀቷም የሚሰፈር አይደለም:: «ሰማየ ሰማያት» እንዳለ «የጌታ ናት» /መዝ. 115፥116/ ነገር ግን ወደ እርሱ መድረስ የማይቻል መስሎን የምንዘናጋ ሳይሆን ይልቁንም ቀናኢ መሆን ይገባናል:: በእነዚህ በቀደሙት ሰዎች ከምሥራቅ ተወግደው በሰናዖር ደልዳላውን አግኝተው ግንብ መሥራት እንደጀመሩት እኛስ በእሳት ጡብ መጋገር /መተከል/ እንፈልጋለን፤ ጭቃው እንደ ዝፍት፤ጡቡም እንደ ድንጋይ እንዲሆን እንፈልጋለን? እነርሱ ቋንቋቸው ተደባልቋል፤ ሥራቸውም ወድሟልና::

ለእኛ ግን ጌታ መንገዱን በደሙ ባርኮልናል፤ ምቹም አደረገው:: ስለ ርቀቱም መንገዱን ያደላደለልን ብቻ አይደለም፤ ስለዚያ መጣ፤ እንዲ ተዘግቶ የነበረውን በር ከፈተልን:: በእርግጥም አዳምን ከገነት ደስታ ካስወጣው ጊዜ ጀምሮ ተዘግቶ ነበርና:: ኪሩቤልንና የነበልባል ሰይፍን አስቀመጠ:: ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ይጠብቅ ዘንድ፤ አሁን ግን በሰፊው ተከፈተ:: እንግዲህ ታላቁን ጸጋና የፍቅርን ርኅራኄ ይዞ በኪሩቤል ፊት የሚቆም ማንም ከእኛ ቀድሞ አምኖ እንደገባው ወንበዴ ለሁሉ ወደተከፈተች ገነት በራሱ ይመራናል::

ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ «ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ» ይላል /ፊል. 3፥14/:: ወደ ሦስተኛው ሰማይ የተወሰደበትን፣ በላይ በሰማይ ያሉ ነገሮችን ያየበትን፣ ከዚያም የተመለሰበትን በዕብራውያን መልእክቱ «ሊዳሰሰ

ወደሚችል ወደሚቃጠልም እሳት ወደ ጭጋግም ወደ ጨለማም ወደ ዐውሎ ነፋስም ወደ መለከት ደምፅም ወደ ቃሎችም ነገር አልደረሳችሁምና... ነገር ግን ወደ ጽዮን ከተማ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፤ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት በሰማያትም ወደተጻፈ ወደ በኩራት ማኅበር » እያለ በማስተማር ያበስረናል። /ዕብ. 12÷18-23/ በዚህ ታላቅ ኅብረት /አንድነት/ ውስጥ ገብቶ ደስ መሰኘት የማይፈልግ ማን አለ? ወደ እነዚህ ማኅበራት ታድሞ ከእነርሱ ጋር «እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ» ሲ ባል ለመስማት የማይመኝ ማነው? /ማቴ. 25÷34/





# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አርባ አራት

## ክርስቶስ ማየ ሕይወት ስለመሆኑ

ስለዚህ የሊቃነ ካህናቱና የጸሐፍት አገልጋዮች የነበሩት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ» ሲል በሰሙ ጊዜና ነገሮችንም ሁሉ ባዩ ጊዜ /ዮሐ. 7÷37/ እንደ እነርሱ ዕሩቅ ብእሲ አለመሆኑን ተረዱ። እርሱ በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረለት ለቅዱሳን የሕይወት ወኃን የሚሰጠው ነው እንጂ። እርሱ በእውነት የሚማርክ ብርሃን፣ የአብም ቃል ነውና። ከምንጭ እንደሚፈልቅ ወንዝ ጉትን አጠጣ። አሁን ግን ለሰው ሁሉ የመንፈስን ጸጋ ሰጠ። «የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ» አለ። ዳግመኛም «የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈል ቃል» አለ። /ዮሐ. 7÷37/ ይህ ሰው ሊለው የማይገባ ቃል ነው፤ በእውነት የሕይወት ብሥራት የሆነና መንፈስ ቅዱስን የሚሰጥ ሕያው እግዚአብሔር የሚናገረው እንጂ።

# መልእክት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ቁጥር አርባ አምስት

## በዓሉ ሰማያዊ በዓል ስለመሆኑ

እንግዲህ መሥዋዕታችንን እንውሰድ፣ ድሆችንም እናሳትፍ፣ ስለእኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ» ተብሎ እንደተጻፈ /ዕብ. 6÷20፣ 9÷12/ ወደ ቅድስቲቱም ሥፍራ እንግባ። ይህ ታላቅ ማስረጃ ነው እንግዶ ችና መጻተኞች ብንሆንም ባለሟሎች ተብለን ተጠርተናል፤ ቀድሞ ባዕዳን ብንሆንም አሁን ግን ከቅዱሳን ጋር ዜጎች ወራሾች ሆነናል፤ ሰሎሞን ምሳሌዋን የሠራላት የታላቂቱ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ልጆች ተብለን ተጠርተኗል። አስቀድሞ ሙሴ ተራራው ላይ ባየው አምሳል የታዘዘውን እንዳደረገ በድንኳኒቱ የሆነው ሁሉ ጌታ

እንግባበት ዘንድ ያዘጋጀው የሰማያዊው ምስጢር ምሳሌ እንደነበር ግልጽ ነው። ሁሉም የቀደመው ነገር ሁሉ ለአዲሱ ምሳሌ እንደነበር አሁን የምናከብረውም በዓል በላይ ያለው የታላቁ ደስታ ምሳሌ ነውና በመዝሙር፣ በማኅሌት በዓሉን ማድረግ እንጀምር።

**ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ለዘላለሙ አሜን**

በእርግጥም በአንድ ኃጢአተኛ
ንስሓ በሰማይ ታላቅ ደስታ
የሚደረግ ከሆነ ስለሁላችን
ኃጢአት መደምሰስ ስለሙታን
ትንሣኤማ እንዴት የበለጠ
አይሆን! አቤት! በሰማይ
የሚደረግ በዓል ምን ዓይነት፣
እንዴትስ ታላቅ ይሆን?!
ዘወትር በምስጋና የሚተጉ
የሰማይ ሠራዊት በእኛ ጉባኤ
የሚደሰቱ ወደ እኛም የሚያዩ
ከሆነ በተለይ በበዓለ ትንሣኤ
ደስታና ፈንጠዝያቸው እንዴት
የግድ አይሆን!

ዋጋ ብር 30.00

Printed By Biniyam 0930 01 28 13